ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 129 ጥር 9 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!












# ስምምነቱ ኢትዮጵያ የወጪና የገቢ ንግዷን ያለከልካይ እንድታከናውን የሚያስችል ነው

ገጽ 4

## ባለሚዛኖቹ ለጋ ሕፃናት

ማህሌት ብዙነህ

ዜና ሐተታ

በለጋ ሕፃናት ዕድሜያቸው በየጎዳናው ሚዛን ከፊታቸው አስቀምጠው "ተመዘኑ---- ተመዘኑ" ሲሉ ይውላሉ። እነዚህ ሕፃናት ከቤተሰባቸው ተነጥለው ወደ ከተማ ከመጡ በኋላ ከትምህርት ገበታ ርቀው ብርዱ፣ ጸሀዩ

ባለሚዛኖቹ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



## «ኤግዚቢሽኑ ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ የነበራትን ሚና የሚያሳይ በመሆኑ ወጣቶች ሊጎበኙት ይገባል»

- አምባሳደር ዘነበ ከበደ
በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአውሮፓና አሜሪካ ጀነራል ዳይሬክተር

ገጽ 4

# የጥምቀት በዓል በሰላምና ፍጹም ክርስቲያናዊ በሆነ ሥነ ምግባር ማክበር ይገባል

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- የጥምቀት በዓል ፍጹም ክርስቲያናዊ በሆነ ሥነ ምግባር ማክበር እንደሚገባ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ሄኖክ ገለጹ።

የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብጹዕ አቡነ ሄኖክ በዓለ ጥምቀትን አስመልክተው ትናንት ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፣ የጥምቀት በዓል ሰላምን በመንከባከብና በመተግበር ፍጹም ክርስቲያናዊ በሆነ ሥነ ምግባር ማክበር ይገባል።

የጥምቀት በዓል ከኢየሱስ ክርስቶስ ዓበይት በዓላት መካከል አንዱ በመሆኑ በቤተክርስቲያን ዘንድ በልዩ ድምቀት ይከበራል ያሉት ብጹዕ አቡነ ሄኖክ፣ ለበዓሉ ጃንሜዳ ባህረ ጥምቀትን ጨምሮ በሀገረ ስብከቱ በ78 የጥምቀት በዓል ማክበሪያዎች ተዘጋጅተዋል ብለዋል።

የጥምቀት በዓል በሰላም እንዲከበር ከሚመለከተው የመንግሥት አካል ጋር ሰፊ ውይይት ተደርጎ ጥሩ መግባባት ላይ መደረሱን ገልጸው፣ በዓሉ የአደባባይ በዓል

የጥምቀት በዓል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ብጹዕ አቡነ ሄኖክ









አቶ ሺሰማ ገብረስላሴ

# ማህበራት በገበያ ውስጥ ያላቸውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ እየተሠራ ነው

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- የኅብረት ሥራ ማህበራት በገበያ ውስጥ ያላቸውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ እየተሠራ መሆኑን የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ምክትል ኮሚሽነር አቶ ሺሰማ ገብረስላሴ አስታወቁ።

አቶ ሺሰማ ገብረስላሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኅብረት ሥራ ማህበራት ቁጥር ከፍተኛ ቢሆንም በገበያ ውስጥ ያላቸውን አስተዋጽኦ ለማሳደግ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

ማህበራት በግብይት ዘርፉ ያላቸውን ተሳትፎ ለማሳደግ ያላቸው ካፒታል ዝቅተኛ በመሆኑ የፋይናንስ አቅማቸውን ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን ጠቁመው፤ በማህበራቱ አማካኝነት ሰፊ የሥራ ዕድል ለመፍጠር ኮሚሽኑ ማቀዱን ገልጸዋል።

በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ ጥረት ብቻ የሀገርን ኢኮኖሚ ማሳደግ አይቻልም ያሉት ምክትል ኮሚሽነሩ፤ ማህበራት ያላቸውን አቅምና ዕድል ተጠቅመው ይበልጥ መስራት ይኖርባቸዋል ብለዋል።

መንግሥት ለኅብረት ሥራ ማህበራት የሚሰጣቸው የተዘዋዋሪ ፈንድ ድጋፍ በጊዜው እንዲደርስና ምርቶች ተገዝተው ለገበያ እንዲቀርቡ በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ሺሰማ ገለጻ፤ አርሶ አደሮችንና ዩኒየኖችን በማገናኘትና የሦስተኛ ወገን ጣልቃ ገብነት በማስቀረት የማህበራትን የፋይናንስ አቅም የማጎልበት ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

በኅብረት ሥራ ማህበራት ላይ ያለውን መሰረታዊ ችግሮች ለመፍታት የሚረዳውን ሪፎርም ውጤታማ ለማድረግ በግብርና ሚኒስቴር የሚመራና ስድስት ባለድርሻ አካላትን ያካተተ ኮሚቴ ተዋቅሮ ወደ ሥራ መገባቱንም አስረድተዋል።

ሪፎርሙ የማህበራትን የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ለማሻሻል፣ አማራጭ የፋይናንስ አቅርቦት ሥርዓትን ለማመቻቸት፣ ማህበራት ከተደራጁ በኋላ የሚመሩበት መንገድ የተሻለ ለማድረግ የሕግ ማዕቀፍ የማዘጋጀትና የቁጥጥር ሥራውን ቀልጣፋ ለማድረግ የሚያግዝ መሆኑን ጠቁመዋል።

በግብርና ዘርፍ ምርታማነትን ለማሳደግ የሚረዱ ግብዓት አቅራቢና የተመረተውን ምርት በተገቢው መንገድ ለገበያ የሚያቀርቡ ማህበራት መኖራቸውን አቶ ሺሰማ አስረድተው፤ በቀጣይ ለሌሎች ሀገራት ጭምር ተምሳሌት የሚሆኑ ማህበራትን የማፍራት ሥራ በሀገር አቀፍ ደረጃ ይሠራል ሲሉ አመላክተዋል።

በኢትዮጵያ 23 ሺህ የብድርና ቁጠባ ማህበራት፣ 29 ሺህ ሁለገብ የገበሬዎች ኅብረት ሥራ ማህበራት፣ አምስት ሺህ የሸማች ማህበራት፣ 400 ዩኒየኖችና አምስት ፌዴሬሽኖች በተለያዩ ዘርፎች ላይ ተሰማርተው እየሰሩ መሆኑን አስታውቀው፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ 105 ሺህ በላይ ማህበራት እንደሚገኙ አመላክተዋል።

# በኦሮሚያ በኅብረተሰብ ተሳትፎ ከ4 ሺህ በላይ ትምህርት ቤቶች ደረጃ ተሻሽሏል

## - ከ5ሺህ በላይ የመምህራን መኖሪያ ቤቶች ተገንብተዋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በኦሮሚያ ክልል በኅብረተሰቡ ተሳትፎ ከአራት ሺህ በላይ ትምህርት ቤቶች ደረጃ እንዲሻሻል መደረጉን የክልሉ ትምህርት ቢሮ አስታወቀ። ከአምስት ሺህ በላይ የመምህራን መኖሪያ ቤቶች መገንባታቸውም ተገልጿል።

የኦሮሚያ ክልል ትምህርት ቢሮ እቅድ ዝግጅት ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክተር አቶ ሀሰን እንድሪስ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤በክልሉ በ2016 በጀት ዓመት በኅብረተሰቡ ተሳትፎ ከ4ሺህ በላይ ትምህርት ቤቶች የደረጃ ማሻሻያ ተደርጓል።

በክልሉ ከደረጃ በታች የሆኑ ሦስት ሺህ 410 ትምህርት ቤቶችን ወደ ደረጃ ለማሳደግ ታቅዶ እንደነበር የገለጹት አቶ ሀሰን፤ እስካሁን አራት ሺህ 418 ትምህርት ቤቶች ደረጃቸው እንዲሻሻል መደረጉን አመላክተዋል።

የአዳዲስ ትምህርት ቤቶች ግንባታ ከማከናወን በተጨማሪ ለመማር ማስተማር ሂደቱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን የማዳረሱ ስራ ተጠናክሮ መቀጠሉን አስረድተዋል።

እድሳት የሚያስፈልጋቸውን መማሪያ ክፍሎች ማደስ፣የተማሪዎች መቀመጫ ወንበር፣ቤተ መጻሕፍት፣መጸዳጃ ቤቶች፣የውሃ አቅርቦት፣የአጥር ግንባታና ሌሎች አስፈላጊውን መሰረተ ልማቶች የማሟላት ሥራ መሠራቱን ገልጸዋል።

በትምህርት ቤቶች ደረጃ መመዘኛ መሰረት በደረጃ አንድና ሁለት የሚገኙ ትምህርት ቤቶች ከደረጃ በታች መሆናቸውን ጠቁመው፤ ትምህርት ቤቶች ቢያንስ ደረጃ ሦስትና አራት መስፈርትን እንዲያሟሉ ከኅብረተሰቡ ጋር



በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

በክልሉ የትምህርት ቤቶች እድሳት በዘንድሮው ዓመት ትኩረት ተሰጥቶት በንቅናቄ መልክ እየተሰራበት ነው ያሉት ዳይሬክተሩ፤ የትምህርት ቤቶች የደረጃ ማሻሻል ፣የመምህራን ቤቶችና የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ግንባታ ቀጣይነት ባለው መልኩ በኅብረተሰብ ተሳትፎ እየተሰሩ መሆኑን ገልጸዋል።

በንቅናቄው በኅብረተሰቡ ተሳትፎ ለመምህራን መኖሪያ ቤት ለመገንባት ታቅዶ እየተሰራ መሆኑን ጠቁመው፤ አራት ሺህ የመምህራን መኖሪያ ቤት ለመገንባት ታቅዶ አምስት ሺህ 369 የመምህራን መኖሪያ ቤቶች መገንባታቸውን አስታውቀዋል።

በክልሉ የቅድመ መደበኛ ትምህርትን ለማስፋት ባለፉት ሁለት ዓመታት በኅብረተሰቡ ተሳትፎ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን የተናገሩት አቶ ሀሰን፤ ባለፉት ወራት ሶስት ሺህ 764 የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ ይገኛል ብለዋል።

የትምህርት ቤቶች እድሳት፣የመምህራን መኖሪያ ቤቶች፣የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ግንባታ ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን አመልክተው፤ በገንዘብ፣በጉልበትና በሙያውና በቁሳቁስ ድጋፍ 16 ቢሊዮን ብር ያህል ድጋፍ መደረጉን አስረድተዋል።

# የትግራይን ቱሪዝም

## ከነበረበት በላይ ለማሳደግ እየተሠራ ነው



**በሪሁ አረጋ**

መቐለ፡- በትግራይ ክልል የሰፈነውን አንፃራዊ ሰላም በመጠቀም ሙሉ በሙሉ ተቋርጦ የከረመውን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ወደ ነበረበት ለመመለስ ብቻ ሳይሆን ከነበረበትም በላይ ለማሳደግ እየሠራ መሆኑን የቱሪዝም ሚኒስቴር ገለጸ። ክልሉ በአሁኑ ጊዜ ፍፁም ሰላማዊ የሆነና መጎብኘት በሚቻልበት ቁመና ላይ እንዳለም ተመላክቷል።

የክልሉን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ዳግም ለማስጀመር በቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ የተመራ ቡድን በትግራይ ክልል የቱሪዝም መዳረሻ ቦታዎች ጉብኝት አድርጓል።

ሚኒስትር ዴኤታው በዚሁ ወቅት እንደገለጹት፤ ቱሪዝም ሚኒስቴር ከኮረና ወረርሽኝ መከሰት ጀምሮ እስካሁን የተቋረጠውን የክልሉን የቱሪዝም እንቅስቃሴ ከነበረበትም አስበልጦ ለመስራት እንቅስቃሴ ላይ ነው።።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ገለጻ፤ ተቋማቸው የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ከተደረገ በኋላ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ያሉበትን ደረጃ በተመለከተ በከፍተኛ ባለሙያዎች በተከታታይ ጥናት እንዲደረግ ሥራዎች ተሰርተዋል።

ሚኒስቴሩ በክልሉ አስፈላጊ የሆኑ የተለያዩ ጥናቶችን የመዳረሻ ልማት ሥራዎችና ቅርሶች ያሉበትን ደረጃ እንዲሁም በቱሪዝሙ ላይ ያለውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ሂደት ሲከታተለው ቆይቷል ብለዋል።

አቶ ስለሺ ቱሪዝም ለሰላም የላቀ አስተዋጽኦ እንዳለው በመግለጽ፤ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በክልሉ ላለፉት ስድስት ወራት በአክሱም፣ በገራልታ፣ በመቐለና ለቱሪስት መዳረሻ ናቸው በሚባሉ አካባቢዎች ጥናት ማድረጉን አመልክተዋል። በዚህም መሰረት አስፈላጊ የሆኑ እንደ የትራስፖርት አገልግሎት፣ የሚጎበኙ ቦታዎች የሚገኙበት ደረጃ እንዲሁም አገልግሎቱን ለመስጠት ያለውም አጠቃላይ የሰው ሀብትና የተቋማት ዝግጅት የማጥናት ሥራ እንደተከናወነ ተናግረዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው አያይዘውም፤ ወደ ፊት የውጭ ሀገር አምባሳደሮች ያደረጉትን የጉዞ ክልከላ ለማንሳት በአካባቢው መጥተው ያለውን ነባራዊ የዘርፉን እንቅስቃሴ በመመልከት የጉዞ ክልከላዎችን እንዲያነሱ የማድረግ ሥራም እንደሚሠራ ገልጸዋል።


በተጨማሪም ሚዲያዎች አጠቃላይ በክልሉ ያለውን የቱሪዝም እንቅስቃሴ በማየት ግንዛቤ እንዲፈጥሩ፣ የገፅታ ግንባታ እንዲያደርጉና አካባቢውን እንዲያስተዋውቁ የማድረግ ሥራ እንዲሠሩ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

የትግራይ ክልል በአሁኑ ጊዜ ፍፁም ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ ጎብኚዎች ከውጭም ከሀገር ውስጥም መጥተው ሊጎበኙ የሚችሉበት ደረጃ ላይ ነው የሚገኘው ሲሉ ገልጸዋል። በመዳረሻዎች ላይ ቱሪስቶች ከምንም አይነት ስጋት ውጪ ጥሩ ነገር አይተው ጎብኝተው አትርፈው መሄድ እንደሚችሉም አስረድተዋል።

የክልሉ የቱሪዝም ቢሮ ኃላፊ ዶክተር አፅብሃ ገብረእግዚአብሔር በበኩላቸው፤ ቱሪስቶች ድንበር አልባ በመሆናቸው ወደ ክልሉ ከመጡ በኋላ ትግራይን ብቻ እንዲጎበኙ ሳይሆን ወደ አጎራባች ክልሎች ጉብኝት እንዲደረግ ስለመሰራቱ አመላክተዋል።

በተለይ ወደ አማራና አፋር ክልሎች በመሄድም እንዲጎበኙ ለማድረግ ከክልሎች ጋር በቅንጅት እየሰራን ነው ሲሉም አክለዋል።

ዘርፉ ዓለም አቀፋዊ እንደመሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለመወዳደር እየሠራን ነው ያሉት ኃላፊው፤ ኢኮኖሚው ላይ ያለውን የጎላ ሚና እንዲጫወት ለማድረግም በቁርጠኝነት እንደሚሠሩ አብራርተዋል።



# የሉሲ ቅሪተ አካል

## የተገኘበት 50ኛ ዓመት በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ይዘከራል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የሉሲ ወይም ድንቅነሽ ቅሪተ አካል የተገኘበት 50ኛ ዓመት በልዩ ልዩ ዝግጅቶች እንደሚዘከር በአሪዞና ስቴት ዩኒቨርሲቲ የሰው ዘር አመጣጥ ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ፕሮፌሰር ዮሐንስ ኃይለስላሴ ገለጹ። ቅሪት አካሏን ያገኙት ፕሮፌሰር ዶናልድ ጆሀንሰንን ጨምሮ ከአሜሪካ የመጡ ከ25 በላይ ጎብኚዎች ብሔራዊ ሙዚየምን ትናንት ጎብኝተዋል።

ፕሮፌሰር ዮሐንስ ኃይለስላሴ በጉብኝቱ ወቅት እንዳሉት፤ ሉሲ ወይም ድንቅነሽ ስለሰው ልጅ አመጣጥ የምናውቃቸውን አብዛኛውን መረጃዎች የሰጠች ቅሪት አካል ናት። በመሆኑም የተገኘችበት 50ኛ ዓመት በመላው ዓለም በደማቅ ሁኔታ እንዲከበር እየተሠራ ነው።

በኢትዮጵያ ከዛሬ ስድስት ሚሊዮን ዓመት ጀምሮ የሰው ዘርያ እንዴት አሁን ላይ እንደደረሰ መረጃ የሚሰጡ የተለያዩ የሰው ልጅ ቅሪተ አካላት ኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛሉ ያሉት ፕሮፌሰር ዮሐንስ፤ ይህም ኢትዮጵያ የሰው ልጅ ምንጭ እንድትባል አስችሏታል ነው ያሉት።

ሉሲ የኢትዮጵያ ስም በመላው ዓለም የምታስጠራ ትልቅ ሀብት ናት ያሉት ፕሮፌሰሩ፤ የተገኘችበትን 50ኛ ዓመት እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ከተለያዩ ዓለማት የሚመጡ ጎብኚዎችን መሳብ ይጠበቅብናል። ጎብኚዎች ሲመጡም ከሉሲ ባለፈ የተገኘችበትን ቦታ ጨምሮ ሌሎችንም የቱሪስት መስህቦችን ማስጎብኘት እንደሚገባም ጠቁመዋል።ለዚህም ተገቢውን የማስተዋወቅ ሥራ መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል።

የሉሲ ቅሪት አካል 50ኛ ዓመት መታሰቢያ ከአሁን ጀምሮ እስከ ቀጣይ ዓመት ህዳር ወር እንደሚቀጥል ጠቁመው፤ ሲምፖዚየሞች፣ የፎቶግራፍ አውደ ርዕይን ጨምሮ በልዩ ልዩ ዝግጅቶች የሚዘከር መሆኑን አመልክተዋል።

ሉሲ ቅሪተ አካል የተገኘበትን 50ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ በኢንስቲትዩቱ አስተባባሪነት ወደ ኢትዮጵያ የመጡ ከ25 በላይ ጎብኚዎች በትናንትናው ዕለት ብሔራዊ ሙዚየምን የጎበኙ ሲሆን፤ በቀጣይም ሉሲ የተገኘችበትን አፋር በሚገኘው ሀዳር ጨምሮ የተለያዩ አካባቢዎችን እንደሚጎበኙ ገልጸዋል።

ቅሪት አካሉን ያገኙት ተመራማሪ ፕሮፌሰር ዶናልድ ጆሀንሰን በበኩላቸው፤ የሉሲ መገኘት የዘርፉን ጥያቄዎች በመመለስ በኩል ትልቅ ድርሻ እንደነበረው ገልጸዋል።

በአፍሪካ የተለያዩ አካባቢዎች በተለይም በኢትዮጵያ የተገኙ ቅሪተ አካላት የአህጉሪቱን ብሎም የኢትዮጵያን የሰው ልጅ ምንጭነት ያረጋገጡ ናቸው።

50ኛ ዓመቱን በልዩ ልዩ ዝግጅቶች ለመዘከር እየተሠራ መሆኑንም ጠቁመው፤ ጉብኝቱም የዚሁ አንድ አካል ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል መሆኑን ጠቅሰዋል።

ሉሲ ወይም ድንቅነሽ 3 ነጥብ 2 ሚሊዮን ዓመት ያላት የሰው ልጅ ቅሪት አካል ስትሆን፣ እንደ አውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር ህዳር 24 ቀን 1974 አፋር ውስጥ በሚገኘ ሀዳር የተባለ ቦታ መገኘቷ ይታወቃል።

# ከተራና ጥምቀት በሰላም እንዲከበር ዝግጅቱን አጠናቆ ወደ ሥራ መግባቱን የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ ኃይል አስታወቀ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- የ2016 ዓ.ም የከተራና ጥምቀት በዓል በሰላም እንዲከበር ዝግጅቱን አጠናቆ ወደ ሥራ መግባቱን የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ ኃይል አስታወቀ። ባለድርሻ አካላትና የከተማዋ ነዋሪዎች የተለመደ ትብብራቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ግብረ ኃይሉ ጥሪ አቅርቧል።

የጋራ ግብረ-ኃይሉ በዓላቱ ያለ አንዳች የፀጥታ ስጋት እንዲከበሩ ሊከናወኑ በሚገባቸው ተግባራት ላይ ትናንት ውይይት አካሂዷል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ በማይዳሰስ ቅርስ የተመዘገበው የጥምቀት እና የከተራ በዓላት በሰላም እንዲከበሩ መላው የፀጥታ አካላት ዝግጅታቸውን አጠናቀው ወደ ሥራ መግባታቸውን አስታውቀዋል። የጥምቀት በዓል ከከተራ ዕለት ጀምሮ ባሉ ተከታታይ ቀናት በልዩ ልዩ ፕሮግራሞች የሚከበር ሃይማኖታዊ በዓል ነው።

የፌዴራል ፖሊስ ወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ ኃላፊ ምክትል ኮሚሽነር ጀነራል መላኩ ፋንታ፤ ፀረ-ሰላም ኃይሎች የፀጥታ አካሉን ትኩረት ለማዛባትና የበዓሉን አከባበር ድባብ ለማደፍረስ ሃይማኖትን ሽፋን በማድረግ ግጭት ቀስቃሽ ይዘት ያላቸው መረጃዎችን እያሰራጩ መሆኑን ተናግረው፤ የሀገር ውስጥም ሆኑ ሌሎች የሽብር ቡድኖች አለን ለማለት ያላቸውን አቅም በመጠቀም ጉዳት ለማድረስ ወደ ኋላ እንደማይሉ አስገንዝበዋል።

ይሁን እንጂ የፀጥታ አካሉ ዋና ግብ በሕግ የበላይነት ሰላምና ፀጥታን በማረጋገጥ በዓሉ በሰላም እንዲከበር ማስቻል በመሆኑ ሁሉም አመራርና አባል ይህን ተገንዝቦ ኃላፊነቱን እንደ ከዚህ ቀደሙ በብቃት ሊወጣ እንደሚገባ መመሪያ ሰጥተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ በበኩላቸው፤ ሕዝባዊ ኃይሉ ከፀጥታ አካሉ ጋር ተቀናጅቶ እንዲሰራ መመሪያ መሰጠቱን ጠቁመው፤ በዓሉ በሰላም እንዲከበር ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ለማስቻል ከማህበረሰቡ፣ ከሃይማኖት አባቶች እና የበዓሉ ጉዳይ ከሚመለከታቸው አደረጃጀቶች ጋር መድረክ ተዘጋጅቶ ውይይት መደረጉን ተናግረዋል።

የበዓሉ በሰላም መከበር ለሀገር ገፅታ የሚኖረው ሚና ከፍተኛ ስለሆነ በየእርከኑ የሚገኙ የከተማ አስተዳደሩ አመራሮች ተግባሩን በቅርበት እየተከታተሉ ከፀጥታ አካላት ጋር በጋራ እየሰሩ መሆኑን ወይዘሮ ሊዲያ ጨምረው ገልጸዋል። በዓሉ ካለምንም የፀጥታ ችግር በሰላም እንዲከበር የከተማ አስተዳደሩ ለፀጥታ አካሉ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግም ተናግረዋል።

በ2016 ዓ.ም ሕዝብ በስፋት ወደ መስክ በመውጣት ያከበራቸው ሃይማኖታዊ በዓላት እና ሌሎች ልዩ ልዩ ኩነቶች በሰላም መከበራቸውን የአዲስ አበባ ፖሊስ ኮሚሽነር ጌቱ አርጋው አስታውሰው፤ በዓላቱ በሰላም እንዲከበሩ ማድረግ የተቻለው የፀጥታ አካላት ተናበው በመስራታቸው እና ሰላም ወዳድ ዜጎች የድርሻቸውን በመወጣታቸው እንደሆነ ገልጸዋል።

ባሳለፍነው ሳምንት በተዘጋጁ የሕዝብ መድረኮች ፖሊስ በሕገ-ወጦች ላይ የጀመረውን ተግባር አጠናክሮ እንዲቀጥል ሕዝቡ ያቀረበውን ጥሪ ተከትሎ ርምጃው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ኮሚሽነሩ ተናግረው፤ ኅብረተሰቡ በዓሉን ያለስጋት እንዲያከብር የፀጥታ አካላት በቴክኖሎጂ ታግዘው ወደ ተግባር መግባታቸውን አስታውቀዋል።

በበዓሉ አከባበርም ሆነ በማንኛውም ወቅት ብሔርን ከብሔር፣ ሃይማኖትን ከሃይማኖት፣ የሚያጋጩ ጭፈራዎች ፣ አልባሳቶች ፣ ፅሁፎች እና በአጠቃላይ ግጭት ቀስቃሽ ተግባራትን የማይታገስ መሆኑን የፀጥታና ደኅንነት የጋራ ግብረ-ኃይሉ ገልጿል።

የጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ጥሪን ተቀብለው በርካታ ቁጥር ያላቸው የሁለተኛ ትውልድ የዲያስፖራ ማኅበረሰብ ወደ ሀገር ቤት እየገቡ ባሉበት በአሁኑ ወቅት የጥምቀት በዓል መከበሩ ለበዓሉ ድምቀትም ሆነ የሀገርን ገፅታ በመልካም ለማስጠራትና የተዛቡ አስተያየቶችን ለማረም የሚኖረው ሚና በቀላሉ የማይታይ በመሆኑ መላው የፀጥታ አካላት ትስስራችንን እና የመረጃ ልውውጣችንን ይበልጥ በማጠናከር የሕዝብን ሰላም የማስጠበቅ ግዴታችንን ልንወጣ ይገባል የሚሉ ሃሳቦች ተነስተው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

የሀገር መከላከያ፣ የፌዴራል ፖሊስ፣ ብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት፣ የአዲስ አበባ ፖሊስ ፣ የሸገር ከተማ አስተዳደር ፖሊስ፣ የሰላምና ፀጥታ እንዲሁም የሌሎች የፀጥታ ተቋማት ከፍተኛ አመራሮች በውይይቱ ላይ ተሳትፈዋል።

# ፋውንዴሽኑ ለኢትዮጵያ እያደረገው ያለው የልማት ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አቶ ደመቀ መኮንን ጠየቁ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የቢል እና ሜሊንዳ ጌትስፋውንዴሽን ለኢትዮጵያ እያደረገው ያለው የልማት ድጋፍ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ጠየቁ።

በዳቮስ ስዊዘርላንድ እየተካሄደ በሚገኘው የዓለም ኢኮኖሚ ፎረም ላይ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን እየተሳተፉ ነው።

ለ54ኛጊዜ እየተካሄደ የሚገኘው የዘንድሮው ጉባኤ ጭብጥ "መተማመንን ዳግም መገንባት" የሚል ሲሆን፤ ቁልፍ በሆኑ ዓለም አቀፍ የልማት ፣ የቴክኖሎጂ ፈጠራ፣ አየር ንብረት ለውጥ እና ወቅታዊ የደህንነት ጉዳዮች ላይ ፎረሙ ትኩረቱን አድርጓል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ በጉባኤው ላይ እያደረጉት ካለው ተሳትፎ ጎን ለጎን ከሀገራት መሪዎች እና ከተቋማት ኃላፊዎች ጋር ውይይት አድርገዋል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ከቢል እና ሜሊንዳ ጌትስ መስራች እና ሊቀ መንበር ቢል ጌትስ ጋርም ትናንት ተወያይተዋል።

በዚህም ወቅት ቢል እና ሜሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን በጤና፣ በግብርና እና በሰው ሀብት ልማት በኢትዮጵያ እያደረገ ለሚገኘው ድጋፍ አቶ ደመቀ ምስጋና አቅርበዋል።

የምጣኔ ሀብት እድገትን በዘላቂነት ለማረጋገጥ መንግሥት ለሚያደርገው ጥረት ፋውንዴሽኑ የሚሰጠውን ድጋፍ አጠናክሮ እንዲቀጥል አቶ ደመቀ ጠይቀዋል።

የቢል እና ሚሊንዳ ጌትስ ፋውንዴሽን መስራች እና ሊቀ መንበር ቢል ጌትስ በበኩላቸው፤ ፋውንዴሽኑ የዜጎችን ህይወት ለመለወጥ የሚያስችሉ የልማት ሥራዎችን አጠናክሮ መስራት እንደሚቀጥል ተናግረዋል።



ፋውንዴሽኑ ላለፉት ሁለት አስርት ዓመታት ገደማ መንግሥት ቅድሚያ በሚሰጣቸው የልማት ዘርፎች የሰዎችን ኑሮ የለወጡ ሥራዎችን በኢትዮጵያ በማከናወን ተጠቃሽ አስተዋፅኦን በማበርከት ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በሌላ በኩል አቶ ደመቀ ከታንዛኒያ ምክትል ፕሬዚዳንት ፊሊፕ ምፓንጎ ጋር በነበራቸው ውይይት ፤ የዓባይ ግድብ ግንባታ ስለሚገኝበት ወቅታዊ ሁኔታ ገለፃ ያደረጉላቸው ሲሆን ፥ የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ሥራ የማጠናቀቂያ ምዕራፍ ላይ እንደሚገኝ ገልጸውላቸዋል።

የታንዛኒያ ፕሬዚዳንት ፊሊፕ ምፓንጎ በበኩላቸው፥ በዓባይ ውሃ ሀብት ላይ ፍትሐዊ አጠቃቀም በተፋሰሱ ሀገሮች መካከል እንዲሰፍን ታንዛኒያ የምታደርገውን ጥረት እንደምትቀጥል ተናግረዋል።

በዓባይ ግድብ ዙሪያ ያሉ ልዩነቶች በውይይት እንዲቋጩ ሲያካሂድ የነበረው የሦስትዮሽ ድርድር ሊቀጥል እንደሚገባም ተናግረዋል። የሁለቱ ሀገራት የጋራ ኮሚሽን ስብሰባን በቅርቡ ለማካሄድ ተስማምተዋል።

አቶ ደመቀ ሌላው ውይይት ያደረጉት አእምሮአዊ ንብረት ጥበቃ ድርጅት ዋና ዳይሬክተር ዳረን ታንግ ጋር ሲሆን ፤ ኢትዮጵያ ከድርጅቱ ጋር ያላት ትብብር ሊጠናከር በሚችልባቸው ጉዳዮች ላይ ተነጋግረዋል።

አቶ ደመቀ ኢትዮጵያ ከድርጅቱ ጋር ያላትን ትብብር ለማጠናከር ዝግጁ መሆኗን ተናግረዋል። ዋና ዳይሬክተሩ ኢትዮጵያን እንዲጎበኙ ክቡር አቶ ደመቀ ያቀረቡላቸውን ጥሪ ተቀብለዋል።

ዋና ዳይሬክተር ዳረን ታንግ የዓለም አእምሮአዊ ንብረት ጥበቃ ድርጅት ለኢትዮጵያ የሚሰጠውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል አረጋግጠዋል።

ለ54ኛ ጊዜ በዳቮስ ስዊዘርላንድ እየተካሄደ ከሚገኘው የዓለም ኢኮኖሚ ፎረም ጎን ለጎን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ከዓለም ኢኮኖሚ ፎረም ፕሬዚዳንት ቦርግ ብሬንድ ጋር ውይይት አካሂደዋል።

በውይይታቸውም የኢንቨስትመንት ፍሰትን ለማሳደግ መንግሥት መሰረታዊ ማሻሻያዎችን ማድረጉን አስረድተዋል።

የመሠረተ ልማት አውታሮችን ለማስፋፋት መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ ኢትዮጵያ በራስ አቅም የገነባችውን የዓባይ ግድብን በማሳያነት ጠቅሰዋል።

የአገልግሎት ዘርፉን ተደራሽ ለማድረግ፣ የፋይናንስ ተቋማትን ለማሻሻልና የግሉን ክፍለ-ኢኮኖሚ ድርሻ ለማሳደግ መንግሥት የጀመራቸውን ሥራዎች አጠናክሮ እንደሚቀጥልም አረጋግጠዋል።

ቦርግ ብሬንድ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በየዓመቱ በሚካሄደው የዓለም ኢኮኖሚ ፎረም ጉባዔ ላይ ለዓመታት ሳታቋርጥ ለቀጠለችው ተሳትፎ ምስጋና አቅርበዋል።

ፎረሙ በቀጣይ ከኢትዮጵያ ጋር ያለውን ግንኙነት አጠናክሮ መቀጠል እንደሚፈልግ ፕሬዚዳንቱ መናገራቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል።

# ስምምነቱ ኢትዮጵያ የወጪና የገቢ ንግዷን ያለከልካይ እንድታከናውን የሚያስችል ነው

**መዓዛ ማሞ**

አዲስ አበባ፡- ከሶማሌላንድ ጋር የተደረገው የባህር በር ስምምነት ኢትዮጵያ የወጪ እና የገቢ ንግዷን ያለከልካይ እንድታከናውን ትልቅ ዕድል የሚፈጥር መሆኑን ምሁራን ተናገሩ።

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁርና የውሃ ፖለቲካ ተመራማሪው ያዕቆብ አርሳኖ (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የባህር በር ስምምነቱ ሶማሌላንድና ኢትዮጵያ የወዳጅነትና የመጠቃቀም ሀሳብ ይዘው የተነሱበት ነው።

ኢትዮጵያና ሶማሌ ላንድ ያደረጉት የባህር በር ስምምነት ኢትዮጵያ የወጪ እና የገቢ ንግዷን ያለከልካይ እንድትጠቀም እንደሚያስችላት ገልጸው፤ ስምምነቱ የንግድ እንቅስቃሴውን ከሽብርተኞች ለመከላከል እንደሚያስችልም ተናግረዋል።

ስምምነቱ ሽብርተኞች እና ሌሎች ተጻራሪ ኃይሎች የወደብ እንቅስቃሴውን እንዳያደናቅፉ ኢትዮጵያ የባህር ኃይሏንም እንድትጠቀም የሚያስችል ውል በመሆኑ ለኢትዮጵያ መልካም እድል የሚፈጥር መሆኑንም ጠቁመዋል።

ከሶማሌላንድ ጋር ለተደረገው የሁለትዮሽ ስምምነት ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ድጋፍ እንዲያደርግ ኢትዮጵያ የማሳመን ሥራ እንደሚጠብቃት የተናገሩት የፖለቲካል ሳይንስ እና የውሃ ፖለቲካ ተመራማሪው፤ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ጠንካራ የዲፕሎማሲ ሥራ ይጠበቅባታል ብለዋል።

የፖለቲካል ሳይንስ መምህርና ተመራማሪ የሆኑት ሙሉጌታ ደበበ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በጉዳዩ ላይ ያላቸውን ሃሳብ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ከሶማሌላንድ ጋር የተደረገው የባህር በር ስምምነት ለኢትዮጵያ እጅግ አስፈላጊና ወሳኝ ነው።

ኢትዮጵያ በርካታ ቁጥር ያለው ህዝብ ይዛ ያለወደብ መቀጠል ከባድ መሆኑን ተናግረው፤ ይሄ የባህር በር ለማግኘት በኢትዮጵያ በኩል የተደረገ ትልቅ ታሪካዊ ርምጃ መሆኑን ገልጸዋል።

ኢትዮጵያውያንና የሶማሌላንድ ዜጎች በስምምነቱ መደሰታቸው ለስምምነቱ ተግባራዊነት ትልቅ ርምጃ መሆኑን አመልክተው፤ ለተፈጻሚነቱም ሁሉም በጋራ መቆም እንዳለበት ተናግረዋል።

የባህር በር ስምምነቱ ኢትዮጵያ ወደ ውስጥ የምታስገባቸውን ዕቃዎች በነጻነት ለማስገባት እንደሚያስችላት የተናገሩት የፖለቲካል ሳይንስ ምሁሩ፤ እንደ ሀገር ለመገንባት እየታሰበ ያለውን ግዙፍ ኢኮኖሚ ዓላማንም ለማሳካትም ትልቅ ሚና ይጫወታል ብለዋል። ስምምነቱ ከሶማሌላንድ ሕዝቦች ጋር ያለውን ጥሩ ግንኙነት በማሳደግ ጠንካራ ትስስር ለመፍጠር እንደሚያስችልም አስገንዝበዋል።

ስምምነቱን የተፈራረሙት ኢትዮጵያ እና ሶማሌላንድ ፍላጎት እስካላቸው ድረስ ሌሎች ሀገራት በጉዳዩ ላይ በሚኖራቸው ቅሬታ የሚቀር ነገር አይኖርም ያሉት የፖለቲካል ሳይንስ ምሁሩ፤ ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲያዊ መንገድ አፈጻጸሙን መጨረስ እንዳለባትም ጠቁመዋል።

የባህር በር ስምምነቱ ሀገራዊ ጥቅምን የሚያስከብር መሆኑን ገልጸው፤ ምሁራን እና ፖለቲከኞች ስምምነቱ ተፈጻሚ እንዲሆን ከመንግሥት ጎን መቆም እንዳለባቸው ተናግረዋል።

# የጥምቀት በዓል በሰላምና ፍጹም ክርስቲያናዊ በሆነ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እንደመሆኑ ሰላም የመጠበቅ የሁሉም ድርሻ መሆኑን ገልጸዋል።

በዓሉ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ላይ ተጠሪነቱ ለሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ የሆነ ግብረ ኃይል ተቋቁሟል ያሉት ብጹዕነታቸው፤ በሁሉም የባህረ ጥምቀት ማክበሪያ ቦታዎች ላይ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ምዕመናን ይታደሙበታል ብለዋል።

ሰላም የአምላክ ድንቅ ስጦታ በመሆኑ ሁሉም አጽንቶ ሊይዘው እንደሚገባ በመግለጽ፤ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ሰላምን በማጥበቅና ዘብ በመቆም ቀዳሚ መሆኗ እንደሚታወቅ ተናግረዋል።

ለሰላም የተሰጠውን ጸጋ መጠበቅ የእያንዳንዱ አማኝ ግዴታ መሆኑን የገለጹት አቡነ ሄኖክ፤ በዓሉን ቤተክርስቲያንን በሚመጥን መልኩ በሰላማዊ መልኩ ማክበር ያስፈልጋል ብለዋል።

በዓሉ ሲከበር ሰላም በመንከባከብ በመተግበር ፍጹም ክርስቲያናዊ በሆነ ሥነ ምግባር ሊሆን እንደሚገባም ጠቁመዋል።

በበዓሉ አለባበስና አካሄድ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንን ማዕከል ያደረገ፣ወጣቶች ከካህናት አባቶች የሚሰጡ መመሪያዎችን በመቀበል እንደሚገባ ጠቅሰው፤ በዓሉ ከጥር 10 ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ድረስ በተቀመጠው መርሀ ግብር መሰረት እንደሚካሄድ አመልክተዋል።

በዓሉ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ሁሉም በሕግና በሥርዓት ሊያከብረው እንደሚገባ ገልጸው፤ ምዕመናን እራሳቸውን ከሁከትና አላስፈላጊ ነገሮች በማራቅ በትእግስትና ሆደ ሰፊነት በዓሉን ሊያከብሩ ይገባል ብለዋል።

በመጨረሻም በዓለ ጥምቀትን ስናከብር በፍጹም ወንድማዊ ፍቅር የተራቡትን በማብላት፣የተጠሙትን በማጠጣት፣የታረዙትን በማልበስ፣ከቀያቸው የተፈናቀሉ ወገኖችን በመርዳት፣ በመተሳሰብና በመደጋገፍ ሊሆን እንደሚገባም አሳስበዋል።

# ባለሚዛኖቹ ለጋ ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እየተፈራረቀባቸው በሚዛን ሥራ ሲሠሩ ይውላሉ።

ዛሬ በአዲስ አበባ ከተማ በየቦታው በአማካይ ከስድስት እስከ 12 ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሕፃናት በየመንገዱ ሚዛን ተመዘኑ፣ ተመዘኑ----- ሲሉ ይውላሉ። በአዲስ አበባ ከተማ በሚዛን ማስመዘን ሥራ ላይ የተሰማራው ሕፃን አማኑኤል አበበ ገና የ10 ዓመት ልጅ ቢሆንም የትውልድ ቦታውን ጥሎ፣ከትምህርቱን እና ከቤተሰቦቹ በመለየት ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ሚዛን ሥራ ላይ ተሰማርቷል።

ሕፃን አማኑኤል እንደሚናገረው ከትውልድ ቦታው ወላይታ አረጋ አካባቢ አዲስ አበባ ደርሰው የተመለሱ ሰዎች አዲስ አበባ በቀላሉ ገንዘብ እንደሚገኝ ይሰማል። እሱም አዲስ አበባ መሄድን ተመኘ። መመኘት ብቻ አይደለም ከወንድሙ ጋር በመነጋገር እሱና ወንድሙ ትውልድ አካባቢያቸውን ጥለው ወደ አዲስ አበባ መጡ።

በአሁኑ ጊዜም በመሀል አዲስ አበባ ሚዛን በማስመዘን ሥራ ላይ ተሰማርቷል። ወንድሙ በሊስትሮነት እሱ ደግሞ አላፊ አግዳሚውን ሚዛን በማስመዘን ከጠዋቱ 12 ሰአት ጀምሮ የቀኑ ሙሉ ጸሀይ እየተፈራረቀበት እንደሚውል ተናግሯል።

‹ሚዛን በማስመዘን ሥራ በቀን ከ150 እስከ 200 ብር አገኛለሁ። አንድ መቶ ብር እቁብ እቆጥባለሁ። በተረፈው ምግቤን እና ሌላ ወጪ እሸፍናለሁ። ገንዘቡ ካልሞላ እስኪሞላ ድረስ መንገድ ላይ አሳልፋለሁ › ሲል ያለበትን ሁኔታ ያብራራል። ከሚያገኘው ገንዘብ ቤተሰብ መርዳት እንደሚፈልግም ሕፃን አማኑኤል ይናገራል።

ሌላኛው ሕፃን ምናሴ ምንታ የ13 እድሜ ሕፃን ሲሆን፤ ሚዛን በማስመዘን እና ማስቲካ በመሸጥ የቤተሰቦቹን የኑሮ ሸክም ለመደገፍ ትምህርት በመማሪያ እድሜው ቤተሰቡን እያስተዳደረ እንደሆነ ይናገራል።

ከሚኖርበት አካባቢ አክስቱ እንዲመጣ እንዳደረገችው እና ሚዛኑን በአንድ ሺህ 700 ብር እንደገዛችለት የሚናገረው ሕፃን ምናሴ ፤ ከአክስቱ ጋር የሚኖር ቢሆንም በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ በመሆናቸው ሚዛን በማስመዘን ከሚያገኘው ገቢ ላይ በቀን አንድ መቶ ብር እንደሚሰጣቸው ይናገራል።

ትምህርት መማር ብፈልግም አሁን ዓመቱ ስላለፈ በሚቀጥለው እየተማርኩ እሰራለሁ ሲል ዕቅዱን ነግሮናል።

እነዚህን እና መሰል ብዙ ቁጥር ያላቸውን ሕፃናት በመዲናዋ አውራ ጎዳናዎች ላይ ማየት የተለመደ ሆኗል። ለመሆኑ የአዲስ አበባ ሴቶች፣ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮ በጉዳዩ ላይ ምን እየሠራ ነው ስንል ጠይቀናል።

የአዲስ አበባ ሴቶች፣ ሕፃናትና ማህበራዊ ጉዳዮች ቢሮ የማህበራዊ ዘርፍ ኃላፊ ወይዘሮ ገነት ቅጣው እንደገለጹት፤ በከተማው ሰፊ ቁጥር ያላቸው ሕፃናት በጎዳና ላይ ይስተዋላሉ።

ይህም ልጆችን ከጎዳና የማንሳት እና በማቆያ በማስገባት ፤ካገገሙ በኋላ ወደ አካባቢና ቤተሰብ የመመለስ ሥራ ይሠራል። ወደ መጡበት የመመለስ ብቻ ሳይሆን የመማር መብታቸው ተከብሮ ወደ ትምህርት እንዲመለሱ በጥብቅ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ለዚህ የሕፃናት ፍልሰት ብዙ ሳቢ እና ገፊ ምክንያቶች ቢሮሩም ዋና ዋናዎቹ መካከል ህገወጥ ደላሎች መበራከት፣ሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ እና የማህበረሰቡ የተሳሳተ አመለካከት ይገኙበታል።

ከተማው ውስጥ ቤተሰቦቻቸው በልመና ላይ ያሉት ሕፃናት በአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ በኩል በተሰጣቸው እድል የምገባ እና መማሪያ ቁሳቁስ ተሟልቶላቸው የሚማሩ ሕፃናት እንዳሉ ወይዘሮ ገነት ጠቅሰው፤ የመስራት እንጂ የመማር ዓላማ የሌላቸው ሕፃናት እንዳሉም አስታውቀዋል።

እነዚህም በየጎዳናው በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ብሎም በልመና ላይ ተሰማርተው ይስተዋላል። በተለይም እድሜያቸው ከ5 እስከ 13 ያሉ ሕፃናት በስፋት አሉ። ቢሮውም ይህንን ለመቀነስ በዘንድሮ ዓመት ከ4 ሺህ በላይ ሕፃናትን ከጎዳና ላይ ማንሳት መቻሉንም አስታውቀዋል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታትም ከቢሮ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤትና ከከተማ አስተዳደርና ከክልል ቢሮዎች ጋር በመተባበር የሕፃናቱን ፍሰት ከመነሻው ለመቆጣጠር እየሠራ ነው። በአካባቢያቸው ከቤተሰብ ጋር የመኖር መብቶቻቸው እንዲከበር ወደየአካባቢ የመመለስ ሥራዎችንም በትኩረት እየተገበረ መሆኑን ወይዘሮ ገነት ገልጸዋል።

ሕፃናት የአንድ ሀገር ተረካቢ የወደፊት ተስፋና ሀብት ናቸው። ዛሬ ላይ ሀገር ተረካቢ ትውልዶች ላይ መስራት ነገ የበለጸገች ሀገር ለመገንባት መሰረት ነው። ለዚህም ደህንነታቸውንና መብቶታቸውን ማክበር እና ማስከበር



አስፈላጊ ነው።

የተባበሩት መንግሥታት የሕፃናት መብቶች ስምምነት ሕፃናት ከኢኮኖሚያዊ ብዝበዛ እንዲሁም አደገኛ በሆኑ ሥራዎች ወይም ከትምህርታቸው የሚያስተጓጉላቸው፣ ለጤናቸው፣ ለአካላቸው፣ ለአእምሯዊና ማህበራዊ እድገታቸው ጎጂ የሆኑ ሥራዎችን እንዳይሰሩ የህግ ጥበቃ ያደርጋል።

ነገር ግን በኢትዮጵያ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ሕፃናት በተለይም በአዲስ አበባ ከተማ ጎዳና ላይ ኑሮአቸውን ያደረጉ ወይም የተለያዩ የሥራ ዘርፎች ላይ ተሰማርተው በስፋት ይስተዋላሉ።

በተለይም ከአምስት ዓመት ሕፃናት ጀምሮ የብረት ቁርጥራጭ የሚለቅሙ፣ ሚዛን የሚያስመዝኑ፣ሎተሪ፣ሶፍት እና ማስቲካ የመሳሰሉትን የሚሸጡ ሕፃናት ያለማንም ጠባቂ እራሳቸውን ችለው ጎዳና ላይ ሲንቀሳቀሱ ማየት የተለመደ ሆኗል። በዚህም ለተለያዩ ሱስና በሽታዎች ተጋላጭ ከመሆናቸውም ባለፈ ለተለያዩ ጥቃቶች ሰለባ እየሆኑ እንደሆነ እሙን ነው።

በከተማዋ የሚስተዋለውን ወንጀሎች እና ፍልሰት ለመቆጣጠር እንደሀገር ሰፊ ግንዛቤ የመፍጠር ህጎችን የማዘጋጀት ተግባርን አጠናክሮ መቀጠል ይገባል።

## «ኤግዚቢሽኑ ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ የነበራትን ሚና የሚያሳይ በመሆኑ ወጣቶች ሊጎበኙት ይገባል»

- አምባሳደር ዘነበ ከበደ
  በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአውሮፓና አሜሪካ ጀነራል ዳይሬክተር

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- የዲፕሎማሲ ሳምንት ኤግዚቢሽን የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ ታሪክና በዓለም መድረክ የነበራትን ሚና የሚያሳይ በመሆኑ ወጣቶች ሊጎበኙት እንደሚገባ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአውሮፓና አሜሪካ ጀነራል ዳይሬክተር አምባሳደር ዘነበ ከበደ አስታወቁ።

በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአውሮፓና አሜሪካ ጀነራል ዳይሬክተር አምባሳደር ዘነበ ከበደ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሳይንስ ሙዚየም የተከፈተው የዲፕሎማሲ ሳምንት ኤግዚቢሽን የምንኮራበትን የኢትዮጵያ ታሪክ የሚዳስስ ነው።

የኢትዮጵያን ታሪክ የማያውቅ ዜጋ ካለ የሚያኮራ ታሪኩን ከዲፕሎማሲ ሳምንቱ ማየትና መማር አለበት ያሉት አምባሳደር ዘነበ፣ በተለይ ወጣቶች መጥተው ማየትና በሀገራቸው ታሪክ መኩራት እንዳለባቸው ገልጸዋል።

የዲፕሎማሲ ኤግዚቢሽኑ የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ ታሪክ ከፍታን የሚያሳይ ነው ያሉት አምባሳደር ዘነበ፤ ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ የነበራትን ሚና አጉልቶ የሚያሳይ በመሆኑ ወጣቶች ሊጎበኙት ይገባል። ወጣቶች የራሳቸውን ታሪክ ለመስራት ካለፈው መማር አለባቸው ብለዋል።

የዲፕሎማሲ ሳምንቱ ለወጣቶች የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ ጉዞ እና በዓለም የነበራትን ሚና የሚያስተምር ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ ኢትዮጵያ ከዓለም ጋር ጠንካራ የዲፕሎማሲ ግንኙነት ነበራት፤ ይህም የኢትዮጵያን ከፍታ ትልቅ ደረጃ አድርሶታል ብለዋል። አሁን ያሉ ወጣቶች የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ ታሪክ በማጥናት ከጥንት ጀምሮ በትውልድ ቅብብሎሽ የመጣውን የዲፕሎማሲ ሥራ ማስቀጠል እንደሚገባቸው ገልጸዋል።

ወጣቶች በአያቶቻቸውና በአባቶቻቸው ታሪክ መኩራት አለባቸው ያሉት አምባሳደሩ፤ ወደፊት ኃላፊነትን ለመወጣት የዲፕሎማሲ ሳምንቱን መጎብኘት አስፈላጊ ነው ሲሉም አጽንኦት ሰጥተዋል።

ወጣቶችና ኢትዮጵያውያን በሙሉ ኢትዮጵያ ያላትን የዲፕሎማሲ ጉዞ እንዲያውቅ ሚዲያዎች የማስተዋወቅ ሥራ መሥራት አለባቸው። እንደ አሁኑ ጊዜ ስልጣኔ ባልነበረበት ወቅት አያቶቻችንና ቅድመ አያቶቻችን የደምና የአጥንት ዋጋ ከፍለው ኢትዮጵያን አስከብረው ለዘላለም አኑረዋል። ይሄ በኢትጵያውያን ደም ውስጥ የሰረጸ ትልቅ ሀብት ነው ብለዋል።

በየትኛውም ጊዜና አቅጣጫ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚዳፈር ነገር ሲመጣ ልዩነቶችና የተለያዩ አስተሳሰቦች ቢኖሩም ሁሉም በአንድነት በመነሳት የሀገሩን ሉዓላዊነት ሲያስከብር መቆየቱን ገልጸዋል።

እንደ አምባሳደር ዘነበ ገለጻ፤ አሁን ያለው ወጣት አንድነትን በማጠናከር በልማት፣ በማህበራዊ ግንኙነቱና ኢትዮጵያን ወደ ከፍታ በመውሰድ የአባቶችን ታሪክ ሊደግሙ ይገባል። ይህን ለማድረግ ቀደምት አባቶች ሰርተው ያለፉትን ታሪክ ማወቅ ይኖርበታል።

እርስ በርስ መዋጋት ለማንም የማይጠቅም በመሆኑ አሁን ያለው ወጣት እርስ በርስ መዋጋትን ማቆም አለበት ያሉት አምባሳደር ዘነበ፣ አርቆ በማሰብና በማስተዋል ለሀገር አንድነትና ሉዓላዊነት መቆም ይገባል ሲሉም አሳስበዋል። ኢትዮጵያን ወደ ከፍታ ለመውሰድ ከታሪክ መማር እንደሚያስፈልግም ተናግረዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## በዓላት ትውፊታቸውን ጠብቀው እንዲከበሩ ለሰላም ትኩረት ሊሰጥ ይገባል!

ኢትዮጵያ የበርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሰራሽ ቅርሶች ባለቤት ነች። የተፈጥሮ ሀብቶቿ ከኤርታኢሌ እስከ ዳሎል፤ ከራስ ዳሽን እስከ ታችኛው ኦሞ ሸለቆ ድረስ የተዘረጉ ናቸው። ከእነዚህም መካከል አስደናቂ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የአየር ንብረት፣ ብርቅዬ የዱር እንስሳት፣ እንዲሁም የሰው ዘር መገኛ ስፍራዎች ተካተውበታል። ሃይማኖታዊ በዓላትም የኢትዮጵያዊነት መገለጫ ሆነው እና በዩኔስኮ ደረጃ ተመዝግበው ዛሬ የዓለም ቅርስ እስከ መሆን ደርሰዋል።

ለዚህ በዋነኛነት ሊጠቀስ የሚችለው ደግሞ የጥምቀት በዓል ነው። በክርስትና ጥምቀት አንድ ሰው ከኃጢአቱ ንስሐ እንደገባና በማንኛውም ሁኔታ ሥር የአምላክን ፈቃድ ለማድረግ እንደተስማማ በሰዎች ፊት ይፋ ለማድረግ የሚወሰደው ርምጃ ነው።

ኢትዮጵያ ዜና ጥምቀተ ክርስቶስን ከሰማችበት ከመጀመሪያው መቶ ክፍለ ዘመን አንስቶ በተለይም ከአጤ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት (6ኛው መ/ክ/ዘ) ወዲህ የጥምቀትን በዓል ዛሬ በሚታየው አኳኋን ስታከበር እንደ ቆየች የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ። በክብረ በዓሉ ከመንበረ ክብራቸው ወጥተው ወደ ባሕረ ጥምቀት የሚወርዱት ታቦታት በካህናቱ ሃሌታ፣ በምእመናኑ እልልታ እና በየአጥቢያ አብያተ ክርስቲያኑ በተቋቋሙ የሰንበት ት/ቤት ወጣቶች በመዝሙሮች ታጅበው በተመሳሳይ አኳኋን እንደሚመለሱ ይታወቃል።

የእምነቱ ተከታዮች አምረውና ደምቀው የሚታዩት በጥምቀት ነው። በጥምቀት የአርባ አራቱ ታቦት ፤ ሊቃውንት፣ ስመጥር የደብር አለቆችና ካህናት በሚያምረው ልብሰ ተክህኖ አምረውና ደምቀው ይታያሉ። በነጭ የባህል ልብሳቸው ላይ ጣል ከሚያደርጉት ጥቁር ካባቸውንና በራሳቸው ጥምጣም የሚታወቁት በጎንደር የቅኔ ፤ የመወድስና የአቋቋም ዝማሬ ሊቃውንት ባማረው አንደበታቸው የውዳሴ መዝሙር ጣዕመ ዜማ፣ ወረብና ሽብሸባውን በአደባባይ የሚያሰሙበት ልዩ አጋጣሚ ቢኖር ይህ የጥምቀት በዓል ነው። ሳይበረዝ፤ሳይከለስ የጥንቱ የጠዋቱ የጥምቀት በዓል የሚገኘውም ኢትዮጵያ ውስጥ ብቻ ነው።

የጥምቀት በዓል የአንድነትና የአብሮነት በዓል ነው።ሕፃን አዛውንቱ፤ሴት ወንዱ ብሔርና ቀለም ሳይለየው ታቦታቱን አጅቦ አደባባይ የሚገኝበት ነው። በዚህ የአደባባይ በዓል ላይ ኢትዮጵያውያን በባህላቸው ይደምቃሉ፤ በጭፈራቸው ይደሰታሉ፤ በአለባበሳቸው ይደምቃሉ፤ በሰላማቸው ይኮራሉ። ኢትዮጵያውያን በጥምቀት አንድነታቸው ይጸናል፤ አብሮነታቸው ይጎላል፤ ህብረብሔራዊነታቸው ያሸበርቃል።

ይህ ድምቀት ደግሞ ብዙዎችን ቀልብ ስቦ ከዓለም ዳርቻ ሁሉ ቀልብ እየሳበ ጥምቀትን ለመታደመ ኢትዮጵያ እንዲከትሙ ያደርጋል። ከዓለም ዳርቻ የተሰባሰቡት ቱሪስቶችም ያልተከለሰውንና ያልተበረዘውን የጥምቀት ትውፊት ተመልክተው ከልባቸው ረክተው ይመለሳሉ፤ ዳግም ለመምጣትም ቃል በመግባት ነገን በናፍቆት ይጠባበቃሉ።

ይህን ሁኔታ የታዘበውና ያጠናው የተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፤ የሳይንስና የባህል ጥናት ድርጅት (ዩኔስኮ) ጥምቀትን በዓለም ቅርስነት መዝግቦ የበለጠ እንዲያብብና ጥንታዊ ትውፊቱን ጠብቆ እንዲጓዝ አድርጓል።

ቦጎታ ኮሎምቢያ ውስጥ ድርጅቱ ስለ ቅርስ ጥበቃ በተነጋገረበት ስብሰባ ላይ በተላለፈው ውሳኔ መሰረት በዓሉ በዩኔስኮ የተመዘገበ አራተኛው የማይዳሰስ ቅርስ ሆኗል። ጥምቀት በወርሃ ጥር በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታዮች ዘንድ በአደባባዮች በድምቀት ተከብሮ የሚውል ሃይማኖታዊ በዓል ነው። የጥምቀት በዓል ከዋዜማው ጥር 10 ተጀምሮ እስከ ጥር 12 ቃና ዘገሊላም በድምቀት ይከበራል።

ጥምቀት የዓለም ቅርስ ሆኖ እንዲመዘገብ ያስቻለው አንዱ ገጽታው ሰላማዊነቱና ሕብረ-ብሔራዊነቱ ነው። ሰላም የጥምቀት በዓል ትውፊቱን ጠብቆ እንዲከበር ዋናው መሰረቱ ነው። ያለሰላም ጥምቀትን ማሰብ አይቻልም። ሆኖም ከበዓሉ ትውፊት ውጪ የጥምቀት በዓልን የፖለቲካ ማስፈጸሚያና የግርግር ምንጭ እንዲሆን የሚሹ አካላት ስላሉ እያንዳንዱ ምዕመን ለእነዚህ አካላት ጆሮ ሳይሰጥ በዓሉ በሰላም እንዲከበር የበኩሉን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል።

በተለይም የበዓሉ ዋነኛ ፈርጥ የሆኑት ወጣቶች በመጪው ቀናት የሚከበሩትን የከተራ እና የጥምቀት በዓላት በሰላም እንዲከበሩ እንደተለመደው ለሰላም ዘብ መቆም ይጠበቅባቸዋል!


**አዲስ ዘመን**
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

<u>የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ</u>
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

<u>ዋና አዘጋጅ</u>
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

<u>አድራሻ</u>
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

<u>የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ</u>
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

<u>የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር</u>
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

<u>የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች</u>
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

<u>የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል</u>
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

<u>የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ</u>
ስልክ - 011-1-26-43-39

<u>ማከፋፈያ</u> ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## መንፈሳዊ በዓላትን ለመንፈሳዊ መልዕክት ብቻ

ሚሊዮን ሺበሺ

ሃይማኖትና ፖለቲካ የተደበላለቀ ይመስላል። ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በሃይማኖት ቦታዎች ላይ ፖለቲካዊ መልዕክት፣ በፖለቲካ መድረኮች ላይ ሃይማኖታዊ መልዕክት መስማት እየተደጋገመ ነው። ይህ ድርጊት ሀገራችን የምትተዳደርበትን ሕገ-መንግሥት ጭምር የሚፃረር ነው።

ይህ መጥፎ ልማድ ነው። መጥፎ ልማድ ስለሆነም ነው ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ፖለቲከኞች ጦርነት ቀስቃሽ ንግግር ከሃይማኖት አባቶች እየጠበቁ ያሉት። አሁን አሁን አንድ የሃይማኖት አባት ስለ ሰላም ካወሩ ጦርነትን ከሚደግፉ ኃይሎች ከፍተኛ ውግዘትና እርግማን ይወርድባቸዋል።

የሚፈለገው « ! ቁረጠው! ፍለጠው! ግደለው ..ወዘተ» እንዲሉ ነበር ማለት ነው። እንዴት ከሃይማኖት አባት ይህን እንዲሉ ይጠበቃል? ፖለቲከኞች የሚሉት አይበቃም ወይ? የሃይማኖት አባት ይህን እንዲሉ ማድረግ የሃይማኖቱንስ ክብር መቀነስ አይሆንም?

የሃይማኖት ባህሪው ሰላምና መረጋጋትን ማበረታታት፣ ስለ ሰላም መጸለይ፣ ፀብን ማብረድ ነው። የትኛውም ሃይማኖት ጦርነትን እንደማይደግፍ ለየትኛውም ሰው ግልጽ ነው። ታዲያ በምን አግባብ ነው የሃይማኖት አባቶች ጦርነትን እንዲያበረታቱልን የምንጠብቀው?።

በባህላችን እንኳን ሰዎች የከረረ ፀብ ውስጥ ሲገቡና ነገሩን በቅርብ ሽማግሌዎች ብቻ መፍታት የማይቻል ሲሆን የሃይማኖት አባቶች እንዲገቡበት ይደረጋል። ግጭቶች ከግለሰቦች አልፈው አካባቢያዊ ከሆኑ በሽማግሌ ብቻ በቂ ስለማይሆን የሃይማኖት አባቶች እንዲገቡበት ይደረጋል።

ይህ የሚሆነው የሃይማኖት አባቶችን ስለሰላም እምቢ ማለት ስለሚከብድ ነው። እነርሱን እምቢ ማለት ፈጣሪን እንደመቃወም ስለሚታይ ነው። ለእነርሱ መታዘዝ ለፈጣሪ መታዘዝ ስለሆነ ነው። ታዲያ እነዚህ የሃይማኖት አባቶች ጦርነት ቀስቃሽና ግጭትን የሚያበረታታ ንግግር እንዲያደርጉ መጠበቅ ይህን ክብራቸውን መቀነስ አይሆንም? እንዴት የባህልና የሃይማኖታችን ክብር በፀብ አጫሪነት እንዲቀየር እናደርጋለን?

ይህን ነገር ሊያስቀሩት የሚገባው ራሳቸው የሃይማኖት አባቶች ናቸው፤ መጀመሪያውኑም ያስጀመሩት አንዳንድ የሃይማኖት አባቶች ናቸው። ጦርነት ቀስቃሽ ንግግር ሲያደርጉ ከአንዳንድ ወገኖች ድጋፍና አድናቆት ያገኛሉ። ከብዙ ወገኖች ግን ወቀሳ ነው የሚተርፋቸው። ደግሞስ ታማኝ መሆን ያለባቸው ለምድራዊ ደጋፊዎቻቸው ነው ወይስ ለፈጣሪያቸው ነው?

የሃይማኖት አባት በየትኛው ወገን ነው አድናቆት የማገኘው ብሎ ሊያስብ አይገባም። ይሄኛው ወገን ይወቅሰኛል ብሎም ሊፈራ አይገባም። የሚፈሩትም፣ የሚያከብሩትም ታማኝ ሊሆኑለት የሚገባም የሚያመልኩትን ፈጣሪ ብቻ መሆን ይገባል። አለበለዚያ ፖለቲከኛ ሆኑ ማለት ነው። ፖለቲከኛ ነው ደጋፊ እና ተቃዋሚን ታሳቢ አድርጎ የሚናገር፤ የሃይማኖት አባቶች መልዕክታቸው ስብከታቸው ሁሉ ሃይማኖታዊ መሆን አለበት።

አንዳንድ የሃይማኖት አባቶች ለአንድ የፖለቲካ ወገን ወግነው ሲናገሩ አማኙ ነው ሊገስጻቸው የሚገባው። «የሃይማኖት አባት ይገስጻል እንጂ እንዴት ይገሰጻል?» ይባል ይሆናል፤ ፖለቲከኛ ሆነው ከተገኙስ? የሃይማኖቱን ክብር የማይመጥን ንግግር ከሆነስ?።

ስለሰላም የሚያወሩ የሃይማኖት አባቶች በተቃዋሚዎች በኩል «የመንግሥት ካድሬ» የሚል ወቀሳ ይሰነዘርባቸዋል። አንዳንድ አባቶች ጦርነትን የሚያበረታታ ንግግር የሚያደርጉት ከዚያ ወቀሳ ለመዳን፤ ወይም ጦርነቱን በሚደግፉ ወገኖች ለመመስገን ይመስላል።

ሕዝብ የሚፈልገው ሰላም ነው፤ ከዚህ የተነሳም በሁለንተናዊ መልኩ ሰላም እንዲሰበክለት ይፈልጋል? ለራሱም ሆነ ለትውልዱ ለሰላም አጥንቶ ይቆማል ፤ ታዲያ ስለ ሰላም መስበኩ ከሕዝብም ከፈጣሪም ጎን መቆም የሚያስችል እድል አይደለም።

በየትኛውም አግባብ ይሁን፣ ከየትኛውም ወገን ይሁን የሃይማኖት አባት የእርስ በርስ ጦርነትን የሚያበረታታ ንግግር ካደረጉ ተወቃሽ ይሆናሉ። ከሁለት ዓመት በፊት በነበረው ጦርነት «ጦርነትን ደግፈዋል» የተባሉ አባቶች ብዙ ወቀሳ ደርሶባቸዋል።

ያ የሆነበት ምክንያት እንደ ሃይማኖት አባት «ተው» ማለት ሲገባቸው አበረታተዋል በሚል ነው። እንዴት ከዚያ ስህተት መማር አልተቻለም ? ለምን ችግሩን ቤተ ክርስቲያን በአደባባይ ማውገዝ ፤ወይም ምእመኑን ይቅርታ መጠየቅ ተሳናት?።

ከዚህ የሚከፋው በሃይማኖታዊ ክብረ በዓላት ላይ ከሃይማኖት አባቶች የሚደረግ ፖለቲካዊ መልዕክት ያለው ንግግር ነው። ንግግሮቹ ለምሳሌ፤ እንደ ጥምቀት ያሉ ብዙ ሕዝብ የሚገኝባቸው ደማቅ በዓላት ስጋት የተጫናቸው እንዲሆኑ ያደርጋል።

መንግሥት በዓሉ በሰላም እንዲከበር ካለው ኃላፊነት የተነሳ በበዓላቱ ላይ ብዙ ገደብ ሊያደርግ ይችላል፤ ብዙ ቁጥር ያለው የፀጥታ ኃይል ይሰማራል። እነዚህ ነገሮች ሕዝባዊ የነበረውን በዓል ሌላ መልክ ይሰጡታል።

ሌላው ችግር የሃይማኖት አባት የፖለቲካ ንግግር ሲያደርግ ደጋፊና ተቃዋሚ ይኖራል። በሚቃወሙት ወገን ብዙ እርግማን እና ከጨዋነት ያፈነገጠ ስድብ ሁሉ ይኖራል። ይህ ሆነ ማለት ለሃይማኖት አባት ይሰጥ የነበረው ትልቅ ክብር እና የነበረው አስፈሪ ግርማ ሞገስ ይሸረሸራል። ለዚህ ደግሞ የሃይማኖት አባትን በድፍረት መሳደብ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ያየነው መጥፎ ልማድ ነው። ልክ እንደ ፖለቲከኛ ሁሉ የሚሰደቡ እና የሚረገሙ እየሆኑ ነው።

ፖለቲካዊ ትግል ራሱን የቻሉ ሰዎች አሉት። የእነዚህ ሰዎች ትግል ሊሳካ የሚችለው በራሳቸው ጥረት እንጂ በሃይማኖት አባቶች ተደግፎ ሊሆን አይችልም። በራሳቸው ማሳካት ያልቻሉትን የሃይማኖት አባቶች እንዲቀሰቅሱላቸው ማድረግ የራስን ሃይማኖት ማቅለል ነው።

ሰው ናቸውና የሃይማኖት አባቶችም ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በፍፁም መሳተፍ የለባቸውም ሊባል አይችልም። ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ መናገራቸው አስፈላጊ ከሆነ ደግሞ ሌላ ዓለማዊ መድረክ መፈለግ ይጠበቅባቸዋል።

መንፈሳዊ በዓላት ላይ ፖለቲካዊ መልዕክት ማድረግ እንደ አንድ አባት ብቻ ሳይሆን እንደ ጠቅላላው የእምነቱ ተከታይ ሊታይ ይገባዋል። እዚያ መንፈሳዊ ቦታ ላይ የሄዱ ሰዎች ለንስሐና ለጸሎት እንጂ ብሽሽቅ እና እልህ ለሚበዛበት ፖለቲካዊ ጉዳይ አይደለም።

ፖለቲካ በባህሪው እልህ፣ ቁጣ እና ብሽሽቅ ያለበት ነው። ስለዚህ መንፈሳዊ ቦታ ላይ ሰዎችን ለእልህ፣ ቁጣ እና በቀል እንዲነሳሱ ማድረግ ሃይማኖታዊ ባህሪ አይደለም ?።

የሃይማኖት አባት፣ ጥፋተኛ የሚሉትን ወገን እንደ አባት መገሰጽና መቆጣት ሃይማኖታዊም ባህላዊም መሰረት ያለው ነው። ዳሩ ግን ጦርነት ቀስቃሽና እልህ የሚያስገቡ ንግግሮች ማድረግ ሃይማኖታዊም ሆነ ባህላዊ መሠረት የለውም።

በመንፈሳዊ በዓላትና በመንፈሳዊ ቦታ ሲሆን ደግሞ የበዓሉንም ክብር የማይመጥን ነውና አባቶችም የእምነቱ ተከታዮችም እንዲህ ዓይነት ድርጊቶችን ሊያወግዙ ይገባል!።

ፖስቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

**በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)**
fenote1971@gmail.com

## የሀገር ባለውለታው አንጋፋው ዲፕሎማት

አንድ አንጋፋ ጋዜጠኛ የልብ ወዳጄ፤"ከአፍሪካ መዲናነት እስከ ዓለም መድረክ"በሚል መሪ ሀሳብ ከጥር 2 ቀን 2016 ዓ.ም እስከ ጥር 24 ድረስ በሳይንስ ሙዚየም የተዘጋጀውን የኢትዮጵያ የዲፕሊማሲ ሳምንት አውደ ርዕይ ተመልክቶ ደወለልኝ። ለእይታ በቀረቡ ታሪካዊ ፎቶ ግራፎችና ሰነዶች መገረሙንና መደነቁን ነግሮኝ ሲያበቃ፤ ስለ ዕንቁው አምባሳደር ከተማ ይፍሩ በዚሁ ጋዜጣ"ነጻ ሀሳብ"ላይ ያስነበብሁትን መጣጥፍ ተመልክቶ ኖሮ ምነው ቀዩን እንቁ ዘነጋኸው አለኝ።

ወዳጄ የዓለማቀፍ ግንኙነት ተማሪም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቤተኛም ነውና፤ አመጣጡን ብጠረጥረም፤ ከእሱ ይምጣ ብዬ ደግሞ የምን ቀይ እንቁ አመጣህ ስለው፤ አሁን ማን ይሙት ጠፍቶህ ነው አለኝ፤ እኔም ካወቅሁት ለምን እጠይቅሀለሁ አልሁት፤ የዲፕሎማሲያችን የውሃ ልክና ምልክት፤ ዛሬ የተባበሩት መንግስታት ዓለምን ቁጭ ብድግ የሚያደርግበትን የጸጥታው ምክር ቤት ሀሳብ አፍላቂ፤ ጉምቱው ዲፕሎማት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አክሊሉ ሀብተወልድ ጠፍተውህ ነው አለኝ።

መልስ አልሰጠሁትም። ያው ስለ ዕንቁው አምባሳደር ካስነበብኹን አይቀር በነካ ብዕርህ ስለእሳቸውም አንድ በለን አለኝ። እሽ ከሽ ይበልጣል ብዬ እርስዎ አዝዘውኝ እምቢ አልል ብዬ ባይሆን ፈቃድዎ ከሆነ ርዕሱን እንዲህ ላሻሽለው። "የጸጥታው ም/ቤት አባት ቀይ እንቁ ዲፕሎማት፤" በሚል። ቃል በገባሁት መሠረት እነሆ ወዳጄ፣ እነሆ አንባቢዎች።

የቀድሞው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ (1904- 1967)፣ ለፈጸሙት በጎ ተግባር የ2013 ዓ.ም የበጎ ሰው ሽልማት ልዩ ተሸላሚ ነበሩ። ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ በተገኙበት በኢንተርኮንቲኔንታል ሆቴል በተከናወነው 9ኛው የዓመቱ የበጎ ሰው ሽልማት ላይ እንደተገለጸው፣ ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ለአገራቸው ዘርፈ ብዙ አገልግሎትን ሰጥተዋል:: ከተጠቀሱት አገልግሎቶቻቸው አንዱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሳሉ ከተመሠረተው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጋር የተያያዘ ነው:: በዚያን ጊዜ የ34 ዓመት ዕድሜ የነበራቸው አክሊሉ ከሌሎች ባልደረቦቻቸው ጋር አንድ ላይ ሆነው ወደ ሳንፍራንሲስኮ አቅንተው ነበር::

ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ በዚህ ጉባኤ ላይ የጸጥታው ምክር ቤትን (ሴኩሪቲ ካውንስል) የሚመለከት"አንድ አገር ጥቃት ሊደርስብን ይችላል ብሎ ቅሬታ ቢያቀርብ ሴኩሪቲ ካውንስል መሰብሰብ አለበት"ሲሉ አንድ ሐሳብ ያቀርባሉ:: ይህ ሀሳብ ግን በአሜሪካውያኑ ተቀባይነት አልነበረውም:: "...በምን ማስረጃ አውቀን ነው አገሮቹ ችግር ውስጥ ናቸው የምንለው" ሲሉ አሜሪካውያኑ የመከራከሪያ ሐሳብ ያቀርባሉ። እሳቸው ግን ጣሊያን በ1929 ዓ.ም. በኢትዮጵያ ላይ የፈጸመችውን ግፍና ለመንግሥታቱ ማኅበር ለሊግ ኦፍ ኔሽን አቤቱታዋን ባቀረበች ጊዜም ሰሚ አጥታ እንደነበር ታሪክን በማጣቀስ አስረዱ:: ሐሳቡ ተቀባይነት አገኘ:: ታሪክ የሚናገረውም የጸጥታው ምክር ቤት (ሴኩሪቲ ካውንስል) መሰብሰብ የጀመረው ከዚያ በኋላ ነበር::

በዚህና በሌሎች ተግባሮቻቸው ለክብር የበቁት ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉን ልዩ ሽልማትን ከፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ የተቀበሉት የወንድማቸው ልጅ ናቸው:: ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ የ1967 ዓ.ም. የመንግሥት ለውጥን ተከትሎ ወታደራዊው የደርግ አገዛዝ ኅዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም. ከገደላቸው 60 ሹማምንት አንዱ ነበሩ ይለናል በእለቱ የቀረበው ሀተታ ዘ አበርክቶ:: ስራቸው ከመቃብር በላይ ነውና እያነሳሳን እንዘክራቸዋለን።

ክቡር ጸሀፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ በፈረንሳይ የኢትዮጵያ ለጋሲዮን የፕሬስ አታሼ በመሆን ስራ ጀምረው በአገር ውስጥ በልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች በሚነስትርነትና በመጨረሻም ለ13 ዓመታት ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ለሀገራቸው ነጻነት፣ አንድነት፣ እድገትና ብልጽና ለ39 ዓመታት ያገለገሉ አስተዋይ መሪ ነበሩ:: ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ በምሥራቅ ሸዋ አስተዳደር በአድአ ወረዳ ልዩ ስሙ ደምቢ በሚባል ሥፍራ ከአለቃ ሀብተወልድ ካብቴነህና ከወይዘሮ ያደግድጉ ፍልፍሉ መጋቢት 5 ቀን 1904 ዓ.ም. ተወለዱ ይሉናል ጸሐፊውና የሰብዓዊ መብት ተሟጋቹ አቶ ደረጀ መላኩ።

ዕድሜያቸው ለትምህርት እንደደረሰ የአማርኛ ትምህርት በአዲስ አበባ በሚገኘው በቅዱስ ራጉኤል ቤተክርስቲያን፣ ዘመናዊ ትምህርት ደግሞ በዳግማዊ ምኒሊክ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲማሩ ከቆዩ በኋላ በ1917 ዓ.ም. ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ግብጽ ሀገር ተልከው በሊሴ አሌክሳን ድሪ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን ተከታትለው በ1923 የፈረንሳይን ባኩሎሪያ በማዕረግ ተመረቁ:: ከእዚያም ወደ ፈረንሳይ አገር ሄደው በሶርቦን ዩኒቨርሲቲ ከ1923- 1928 ዓ.ም. ድረስ ሲማሩ ቆይተው በመጨረሻ በሕግ ትምህርት ሊሳንስ (ኤል ኤል ቢ) አገኙ:: በተጨማሪም ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በፐብሊክ ሎው እና በኢኮኖሚክስ ዲፕሎማ ዶክትሬት፣ እንዲሁም በንግድና በፖለቲካ ሳይንስ ሰርተፊኬት ተቀብለዋል::

ክቡርነታቸው በሊሴ አሌክሳንደሪ በትምህርት ላይ በነበሩበት ጊዜ በግብጽ የኮፕቲክ ፓትሪያርክ በአቡነ ዮሐንስ ለትምህርት የተወሰዱት የኢትዮጵያ ተማሪዎች ችግር ላይ ስለወደቁ በጊዜው የኢትዮጵያ አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን አንደራሴ ከነበሩትና ከግብጽ ባለሥልጣኖች ጋር በመነጋገር ችግሩ እንዲፈታ አድርገዋል:: ፈረንሳይ ሀገር ሶርቦን ዩንቨርሲቲ በትምህርት ላይ እንዳሉ ኢትዮጵያ በፋሺስት ኢጣሊያ በመወረሯ በሊግ ኦፍ ኔሽን የኢትዮጵያ ዴሊጌሽን ዋና ጸሃፊ፣ ከዚያም በፓሪስ በኢትዮጵያ ሌጋሲዮን የፕሬስ አታሼ፣ ከ1928-1929 ዓ.ም. ደግሞ አንደኛ ጸሐፊና ከ1929 ዓ.ም.-1933 ዓ.ም. ጉዳይ ፈጻሚ በመሆን ሲሰሩ ኢጣሊያኖች በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ይፈጽሙት የነበረውን ግፍ ለመላው ዓለም በማሳወቅ በአደረጉት ትግል ኢትዮጵያ የአውሮፓውያንን ድጋፍ እንድታገኝ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል::

ኢትዮጵያ ነጻነቷን ከተቀዳጀች በኋላም ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ወደ እናት ሀገራቸው ተመልሰው፣ ከ1935 እስከ 1952 ዓ.ም. በጽህፈት ሚኒስቴር ም/ሚኒስቴር፣ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ም/ሚኒስቴር እንዲሁም ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆነው አገልግለዋል:: ከ1953 ዓ.ም. ጀምሮ እስከ 1966 ዓ.ም. ጠቅላይ ሚኒስትርና የጽህፈት ሚኒስትር ሆነው ከመስራታቸው በላይ በተደራቢነት በ1958 ዓ.ም. የአገር ግዛት ሚኒስቴር ሚኒስትር ነበሩ::

ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ለሀገራቸው ነጻነትና አንድነት ገና በትምህርት ቤት ሳሉና በዚያም በተከታታይ በኢጣሊያ ወረራ ወቅት ካደረጉት ትግል በተጨማሪ ለእደገቷና ለብልጽግናዋ የፈጸሟቸው ተግባራት በርካታ ቢሆኑም ለአብነት ያህል ጥቂቱ ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ ተመልክቷል:: እንግሊዞች ቀደም ብለው ይዘዋት የነበረውን ጋምቤላን፣ ፈረንሳዮች ጅቡቲ ጠረፍ አጠገብ ያለችውን ውሃ ያለባትንና ስትራቴጂክ የሆነችውን አፋምቦን እና እንግሊዞች ኦጋዴን ለቀድሞው ብሪትሽ ሶማሌ ላንድ የግጦሽ መሬት ብለው የያዙትን ሪዘርቭድ ኤሪያን እንዲሁም ለማስተዳደር ችሎታ የላችሁም ብለው የያዙትን የምድር ባቡር አስለቅቀዋል:: ኢጣሊያኖች ሲወጡ ከእንግሊዞች ጋር የነበረውን ስምምነት የእንግሊዞችን የበላይነት የሚያንጸባርቅ በመሆኑ የኢትዮጵያን መብት በሚያስከብር መልክ እንዲለወጥ የሀገሪቱ ወሰን ክልል (በሶማሊያና በሱዳን በኩል ያለው ሲቀር) ሌላው በሰላም ውሳኔ እንዲያገኝ አድርገዋል::

ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ ጠቅላይ ሚኒስትር በነበሩበት ወቅት የአንድ ሀገር አስተዳደርና እድገት ሊጎለብት የሚችለው የተጠናከሩ ድርጅቶች ሲኖሩት መሆኑን በመገንዘብ ለእነዚህ መሰረት የሆነው ሕገ መንግስት ተሻሽሎ እንደገና እንዲወጣ፣ ከዚያም የፍትሐ ብሔርና የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎች፣ የጠቅላይ ሚኒስትርና የሚኒስትሮች ስልጣንና ተግባር የሚወስን ሕግ፣ የዳኞች ሹመትና በፍርድ አሰጣጥ ነጻነት ሕግ፣ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ሕግ፣ የመንግስት ሰራተኞች የጡረታ ሕግ፣ አገር አገዛዝ ደንብ፣ የውትድርና አገልግሎት ሕግ፣ ሌሎችም የአስፈጻሚ መ/ቤቶች የሥራ ሂደት የሚያፋጥኑና ሥነ ሥርዓት የሚያስይዙ ሕጎች እንዲወጡ አድርገዋል::

በልማቱም መስክ የሁለተኛውና የሶስተኛው አምስት ዓመት ፕላን እንዲዘጋጅ፣ የሕብረተሰቡ የስራ ፍላጎት ከፍ እንዲልና የስራ ፈቱ ቁጥር እንዲቀንስ በሰጡት አመራርና በአደረጉት አስተዋጽኦ በመንግስትና በግል ክፍለ ኢኮኖሚ ይገኝ የነበረው ምርት የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ክምችት በማሳደግና የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በማርካት ረገድ የታየው ኢትዮጵያ አስተማማኝ አቅጣጫ እንደያዘች የሚያመለክት ነበር::

የዓለም አቀፍ ድርጅቶች በሀገር ውስጥ መቋቋም የኢኮኖሚ ጥቅምና ለአገር ክብር እንደሚያስገኝ እንዲቋቋምና ቻርተሩ እንዲፈረም ጽ/ቤቱም አዲስ አበባ እንዲሆን፣ የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ጽ/ቤትም አዲስ አበባ እንዲመሰረት አስተዋጽኦ አድርገዋል:: ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በፖለቲካ መስኮች በአገር ውስጥ አመራር በመስጠት በሚያካሂዱት የኃላፊነት ሥራ ብቻ ሳይወሰኑ በአያሌ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ስብሰባዎች ላይ እየተገኙ ታሪካዊና መሠረታዊ የሆኑ ተግባራት አከናውነዋል::

### ለአብነት ያህል፡-

ሀ/ ፓሪስ በተደረገው የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍጻሜ የሰላም ጉባኤ ላይ ኢትዮጵያ ከሌሎች መንግስታት ጋር በእኩልነት ተካፋይ እንድትሆን ባደረጉት ጥረት በአፍሪካ ውስጥ በቅኝ አገዛዝ ሥር የሚኖሩ አገሮች ነጻነታቸውን እንዲያገኙ፣ ኢጣልያ በቅኝ ግዛት የያዘቻቸውን ሀገሮች እንድትለቅና ለኢትዮጵያ 25 ሚሊዮን ዶላር የጦር ካሳ እንድትከፍል እንዲሁም ኢትዮጵ ውስጥ የሚገኘውን የጠላት ንብረት ኢትዮጵያ እንድትወስድ አስወስነዋል::

ለ/ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ቻርተር በአሜሪካን ሀገር በሳንፍራንሲስኮ ከተማ በ1937 ሲረቀቅ ኢትዮጵያ የመንግስታት ማህበር መስራች ሀገር እንድትሆን ከፍተኛ ጥረት አድርገው፣ይኸው በመሳካቱ ቻርተሩን በሚያዘጋጀው ጉባኤ ላይ ተካፍለው በመጨረሻ ቻርተሩን በኢትዮጵያ መንግስት ስም ፈርመዋል::

ሐ/ ከ1937-1945 አራቱ ታላላቅ መንግስታት የኤርትራን ጉዳይ ለመመርመር በአደረጉት ጉባኤና ከእዚያም በኋላ ለተባበሩት መንግስታት ጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ በታየበት ጊዜ ኤርትራ ከእናት ሀገሯ ጋር እንድትቀላቀል ተከራክረው በማሳመን አዎንታዊ የሆነ ውጤት አስገኝተዋል::

መ/ የስዊስ ካናል ችግር በደረሰ ጊዜ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ በመሆን በለንደን ጉባኤ ላይ ከተካፈሉ በኋላ ወደ ፕሬዚዳንት ናስር (የግብጽ መሪ የነበሩ ናቸው::) ከተላኩት አምስት ሀገሮች መልዕክተኞች አንዱ ሆነው ተመርተዋል::

ሠ/ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ አሥራ አምስተኛ ዓመቱን እስከ አከበረበት ድረስ የኢትዮጵያ መልዕክተኞች መሪ በመሆን በስብሰባው ላይ እየተገኙ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በኮሌክቲቭ ሴኩሪቲና በተባበሩት መንግስታት ላይ ያላቸውን ጽኑ እምነት ግንዛቤ እንዲገኝ አድርገዋል::

ረ/ የአፍሪካ ነጻ መንግስታት አራት ብቻ በነበሩበት ጊዜ የተባበሩት መንግሥታት በ1948 ዓ.ም. በአደረገው ጠቅላላ ጉባኤ በአንድ ድምጽ ምክትል ፕሬዚዳንት ሆነው ጉባኤውን መርተዋል:: በዚያን ጊዜ አንድ አፍሪካዊ ለዚህ ኃላፊነት ሲመረጥ እርሳቸው በታሪክ የመጀመሪያው ነበሩ::

ሰ/ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በአዲስ አበባ ውስጥ ባደረጋቸው የመሪዎች ስብሰባ ላይ አዘውትረው ተካፍለዋል። በተለይም ከግንቦት 14-17 ቀን 1955 ዓ.ም. በተደረገው የአፍሪካ መሪዎች ጉባኤ ላይ የሶማሊያ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት የጎሳ ጉዳይ አንስተው ባሰሙት ንግግር"የሶማሊያ ዜጎች በኢትዮጵያ፣ በፈረንሳይና በእንግሊዝ ግዛት ስር ይገኛሉ:: ኢትዮጵያ ያለ ሶማሊያ ሕዝብ ፈቃድ የሶማሊያን መሬት ነጥቃ ወስዳለች::" በማለታቸው ክቡር ጸሐፊ ትእዛዝ አክሊሉ የቀረበው ክስ መሰረተ ቢስ መሆኑን ጠቅሰው፤ ኢትዮጵያ ታሪኳ የታወቀና ነጻነቷን ከሶስት ሺህ ዘመን አንስቶ የሕንድ ውቅያኖስን የሚያካብብ ለመሆኑ ታሪክ እንዲመሰክርላት በታሪክ ውስጥ የሶማሊያ መንግስት የሚባል እንደሌለ በአደባባይ ሞግተዋል።

በ1942 ዓ.ም. ስለቅኝ ሀገሮች ጉዳይ ተከፍቶ በነበረው ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያን መንግስት በመወከል በመገኘትም፤ ሶማሊያ በተቻለ ፍጥነት ነጻነቷን ማግኘት አለባት በማለት እንደተከራከሩ፣ የአገር ጥያቄ ማንሳት የሚቻል ከሆነ ኢትዮጵያ ታሪኳ የሚፈቅድላትና የጂኦግራፊ አቀማመጥ ሁኔታዋ በሚመሰክርላት መሰረት ሶማሊያ ራስዋን ከኢትዮጵያ ግዛት እንደ አንዷ አድርጋ እንደምትጠይቅ፤ ሆኖም ኢትዮጵያ ከመሬቷ አንዲት ጋት እንደማትሰጥ ይህንንም አይነት ፈለግ አንደማትከተል አስረድተዋል።

በማናቸውም ሀገር ጉዳይ ውስጥ ማንም ጣልቃ እንዳይገባ፣ ጠቅላላ ወሰን እንዲከበር፣ አለመግባባቶች በሰላም መንገድ እንዲያልቁ፣ ለአፍሪካ አንድነት ጥረት እንዲደረግ ኢትዮጵያ አጥብቃ ስለምትጠይቅ የሶማሊያ መንግስትም በዚህ ዓላማ ተመርቶ እንዲሰራ ያላቸውን ምኞት በመግለጽ ሰፊ መልስ ሰጥተዋል::

**ሻሎም ! አሜን ።**

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

# ‹‹ኢትዮጵያ ከሱማሌላንድ ጋር ያደረገችው የባህር በር ስምምነት የሚገባትን ከፍታ ለመያዝ የሚያስችላት ነው››

- አምባሳደር ጥሩነህ ዜና

የቀድሞ ዲፕሎማትና የሰብዓዊ መብት ኮሚሽነር

አስቴር ኤልያስ

ኢትዮጵያ ሰሞኑን ራስ ገዝ ከሆነችው ሱማሌ ላንድ ጋር የባህር በር ማግኘት የሚያስችላትን ስምምት አድርጋለች:: ይህን ስምምነት ተከትሎ ብዙዎቹ ኢትዮጵያውያን ደስ የተሰኙ ሲሆን ጥቂቶች ግን በጥርጣሬ መንፈስ ሲያጤኑ ተስተውለዋል:: ከአገር ቤት ወጣ ሲባል ደግሞ ሶማሊያ ጉዳዩን ያወገዘችው ሲሆን፣ በተቃራኒው የሱማሌ ላንድ ሕዝብ ደስታውን በአደባባይ ሲገልጽ ለማየት ተችሏል:: እልፍ ሲል ደግሞ የተለያዩ አገራትና ተቋማት የየራሳቸውን መግለጫ በማውጣት ተጠምደው መሰንበታቸውም እሙን ነው:: ሁሉም የባህር በር ስምምነቱን አስመልክቶ እንደየጥቅሙና ስሜቱ የየራሱን ሐሳብ ይሰንዝር እንጂ ኢትዮጵያ የራሷን የከፍታ መንገድ መዳረሻ ይዛ እየተጓዘች ትገኛለች::

አዲስ ዘመን ከዚህ ከባህር በር ስምምነቱ ጋር ተያይዞ የየአገራቱ እና የየተቋማቱ መግለጫ የሚያመጣው ተጽዕኖ ምንድን ነው? ስምምነት ላይ መደረሱ ከኢትዮጵያ ምጣኔ ሀብት አኳያስ ያለው ፋይዳ ምንድን ነው? በሚሉትና በዲፕሎማሲው ዘንድ ያለውን ሁኔታ አስመልክቶ ከቀድሞ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ኮሚሽነር እና የቀድሞ ዲፕሎማት ከሆኑት አምባሳደር ጥሩነህ ዜና ጋር ያደረገውን ቃለ ምልልስ እንደሚከተለው አቅርበነዋል:: መልካም ንባብ::



ፎቶ፦ ኤዩብ ተፈሪ

**አዲስ ዘመን፡- ከለውጡ ወዲህ ያለውን የኢትዮጵያን የዲፕሎማሲ ጉዞ እንዴት ያዩታል?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው ረገድ ውጤት ያስመዘገበችበት እና ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያደረገችበት እንደ እኔ እምነት በ2015 ዓ.ም ላይ ነው:: በዚያን ዓመት ትልቅ ስኬት ያስመዘገበች ሲሆን፣ ይኸውም የብራዚል፣ ሩሲያ፣ ሕንድ፣ ቻይና እና ደቡብ አፍሪካን ያቀፈውን የብሪክስ አባል እንድትሆን የተረደረገበት ዓመት ነው:: ባሳለፈችው ዓመት በዲፕሎማሲው ረገድ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበችበት ጊዜ ነው ማለት ይቻላል::

ይህ ውጤት ለመገኘቱ ምክንያቱ ምንድን ነው? የተባለ እንደሆን በዋናነት መጥቀስ የምወደው ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል መሆን መቻሏ ቀላል ግምት የሚሰጠው አይደለም ነው:: ብዙዎቻችን ስለብሪክስ ብዙ ግንዛቤ ላይኖረን ይችላል:: ከዚያም አልፎ ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል አገር ሆነች ሲባል ጠቀሜታው ምንድን ነው? እንዴትስ አባል መሆን ተቻለ? የሚለውን የሚያውቀውም ሆነ የማያውቀው አካል በብዙ ለማጥላላት እና ለማናናቅ ሲሞክር ይታያል:: ይህ ውጤት እንዴት መምጣት እንደተቻለ ለሚያውቅ አካል ግን ጉዳዩ ትልቅ ስኬት የተገኘበት መሆኑን ይገነዘባል:: መጤን ያለበትም ከዚህ አኳያ ነው::

ኢትዮጵያ የብሪክስ አባል መሆኗ ትልቅ የዲፕሎማሲ ስኬት ነው ለማለቴ ምክንያቶች አሉኝ፡ አንደኛው ኢትዮጵያ ይህንን ብዙዎች የሚፈልጉትን እድል ማግኘት የቻለችው እውነቱን ለመናገር ከአገራችን በኢኮኖሚ በብዙ የሚበልጡ አገራት እያሉ መሆኑ የሚካድ አይደለም:: በኢኮኖሚያቸውም ከፍ ያሉና በፖለቲካው ዘርፍ የተሻሉ ናቸው የሚባሉ ከአፍሪካም ሆነ ከአህጉራችን ውጭ የሆኑ አገራት የብሪክስ አባል ለመሆን ጠይቀው እድሉን ያላገኙ አሉ::

ኢትዮጵያ ግን ይህንን እድል ለማግኘት ችላለች:: ይህ እድል የተገኘው ደግሞ ከበርካታ አገራት መካከል ለተመረጡ ጥቂት አገራት ብቻ እንደሆነ የሚታወቅ ነው:: ከአፍሪካ ከኢትዮጵያ በተጨማሪ ግብጽ እድሉን ያገኘች አገር ናት:: ከአፍሪካ እነ አልጄሪያና ሞሮኮም ጠይቀው ነበር፤ ኢትዮጵያን ከእነዚህ አገራት ጋር እንኳ ብናስተያየት በኢኮኖሚ ደረጃ እነርሱ ዘንድ ብልጫ መኖሩ ይታወቃል::

ይህን ስል ኢትዮጵያ በብዙ ፈተና ውስጥ ሆና ያገኘችው ስኬት መሆኑን ለመጥቀስ ነው:: በእርግጥ ኢትዮጵያ ጦርነቱ ባይደራረብባት ወደፊት መጓዝ የምትችል አገር ናት:: ፈተና እንዳያጣት የምዕራቡ ዓለም የራሱ የሆነ ጫና በየጊዜው የሚያሳድርባት እንደሆነም ግልጽ ነው:: ያን ተግዳሮት እየተሻገረች ይህን ድል ማስመዝገብ መቻሏ የማይታበል ሐቅ ነው:: ኢትዮጵያን ሲፈታተኗት የነበሩ ችግሮች እያሉ የብሪክስ አባል መሆን የሚያስችለንን ተቀባይነት አግኝተን አባል ሆነናል::

ሁለተኛው ምክንያት ብዬ የምጠቅሰው ባለፉት ሁለት እና ሶስት ዓመታት የደረሰብን ፈተና ግልጽ ነው:: እንዲህ አይነቱ ችግር ደግሞ ተመልሶ ቢመጣ እንኳ የብሪክስ አባል አገር በመሆናችን ሊያግዘን የሚችል ወዳጅ አገኘን ማለት ነው:: ስለዚህ የሚያጋጥመን ተግዳሮት ካለ አብሮ የሚሆን አካል ከጎን መኖሩ ችግሩን አቅልሎ ለማየት ምቹ ከመሆኑም በላይ ለመጋፈጥ አቅም እንዲኖረን የሚያደርግ ነው::

ሶስተኛው ምክንያት ደግሞ ይህ ስብስብ በአሁኑ ጊዜ ባለው ሁኔታ የዓለም አቀፍ ኢኮኖሚ ከ30 እስከ 40 በመቶ የያዘ ነው:: ይህን ቡድን መቀላቀል መቻል ትልቅ እድል ነው:: ከዚህ የተነሳም የቡድን ሰባት አባላት ከሚባሉ ስብስቦች ይልቅ ይህኛው የብሪክስ አባላት ስብስቦች ይበልጣል እየተባለም ይገኛል:: ይህንን የራሳቸው የመገናኛ ብዙሃን ጭምር እየተነተኑት ያለ ጉዳይ ነው::

እኛ ኢትዮጵያውያን በኢኮኖሚያችን በጣም ማደግ እንሻለን:: በጣም በከፍተኛ ደረጃ እየተነሳሳን ያለንበት ወቅትም ነው:: ስለሆነም የብሪክስ አባል መሆናችን ኢኮኖሚያችንን ለማሳደግ ለምናደርገው ሩጫ የሚጠቅመን ይሆናል ማለት ነው::

እንደሚታወቀው የብሪክስ አባል የሆኑ አፍሪካ አገሮች ከደቡብ አፍሪካ ውጭ ሁለት ነን:: አንዷ ግብጽ ናት:: ይህ የእኛ ለብሪክስ አባልነት መመረጥ አንድ የሚያሳየው መልካም ነገር አለ:: ይኸውም በሌሎች ዘንድ ያለን ግምት የተሻለ እና መልካም መሆኑን ነው:: ይህ የአገራቱ መልካም የሆነ አመለካከት ለወደፊቱም ቢሆን ከእኛ ጋር ተባብሮ ለመስራት ያላቸውን ፍላጎት እና ቁርጠኝነት የሚያመላክት ነው:: ይህን ጉዳይ አቅልሎ ለማየት የሚዳዳቸው አካላት ባይጠፉም ለእኛ ግን በጣም ትልቅ ነገር ነው:: ከዚህ አቅጣጫ አንጻር የብሪክሱ አባል መሆን በጣም ትልቅ ነገር ነው:: ዲፕሎማሲውንም ከፍ ያደረገ ጉዳይ ነው::

ይህ በየመንደሩ የሚወራው እና የሚነገረው አካሄድ አላዋቂነት ነው:: ጉዳዩን ለማጥላላት መሞኮር በፍጹም ውሃ የሚቋጥር ሀሳብ አይደለም:: ምክንያቱም ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ከፍ ብላ የታየችበት እና ውጤት ያስመዘገበችበት ወቅት ነበር ለማለት እወዳለሁ:: እንደዚያ ባይሆን ኖሮ በርካታ አገራት ቡድኑን መቀላቀል እየፈለጉ እድሉን አያጡም ነበር::

**አዲስ ዘመን፡- እርስዎ ባሳለፏቸው የኢትዮጵያ መንግስታት ዲፕሎማሲ ዋጋ የተከፈለበት ጊዜ ነው የሚሉት የትኛውን ወቅት ነው? የነበረውንስ ተግዳሮት በመሻገር ምን የተገኘ ውጤት ነበር?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** አንድ አገር በዲፕሎማሲው ዋጋ ለመክፈል ተዘጋጅቶ ‹‹ይህንን እና ያንን ባገኝ የሚመጣብኝ ሁሉ እችላለሁ›› ብሎ የሚንቀሳቀስበት ሁኔታ ይኖራል:: ምናልባት በእኔ እድሜ ከዚህ ጋር ተያይዞ ያጋጠመኝ አሊያም ያስተዋልኩት ነገር አለ::

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

ከገጽ 7 የዞረ

## ‹‹ኢትዮጵያ ከሱማሌላንድ ጋር ያደረገችው...



**ለምን እንደሆነ እስከማይገባኝ ድረስ በኢትዮጵያ ላይ በፊት ያልነበረባቸውን ባህሪ በማሳየት ላይ ያሉ አውሮፓውያን ሆነዋል**

እኤአ በ1970 አካባቢ አሊያም በ1967 ዓ.ም አካባቢ ከምዕራቡ ጋር ያለንን ግንኙት በማቋረጥ ወደ ምስራቁ አገር ሔደን አገራችንን ከሱማሊያ ወረራ ያዳንበት ውጤት የማይረሳ ነው:: በወቅቱ የገንዘብም፤ የመሳሪያም እርዳታ እናገኝ የነበረው ከአሜሪካ ነበር:: ነገር ግን በአብዮቱ ምክንያቶች አሜሪካውያን ጣል ጣል ያደርጉን ጀምረው ነበር:: ስለዚህ በዚያን ጊዜ የነበሩት መሪ ‹‹ሶሻሊዝምን እቀበላለሁ፤ እኔ የሶሻሊስት አገሮች ደጋፊ ነኝ›› ብለው ወደእዛ በመግባት ያንን ያህል መሳሪያ ማግኘት የቻሉበት ጊዜ ነበር:: ከዚህ ጋር ተያይዞ እንዲያውም በወቅቱ ኒዮርክ ታይምስ ‹‹ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ እንዲህ አይነት መሳሪያ በአውሮፕላን የተጓጓዘበት ጊዜ አልነበረም›› ሲል መዘገቡን አስታውሳለሁ::

በወቅቱ ሶቬዬት ኅብረት የሚባለው አገር ያንን ያህል መሳሪያ ልኮልን ጄኔራሎቻቸውም ጭምር መጥተው እንደነበር የማይዘነጋ ነው፤ እንዲሁም ወዳጃችን የሆኑት ኩባዎችም እንዲያግዙን አድርገው ከሱማሊያ ወረራ ባይታደጉን ኖሮ ኢትዮጵያ የምትባለው አገር አሁን ባለችበት ሁኔታ ላትቆይ ትችላለች የሚል ጥርጣሬ አለኝ::

ስለዚህ በዚያን ወቅት ከምዕራቡ ወደ ምስራቁ በመንጠልጠል አገራችንን አድነናልና ዲፕሎማሲው ምንም እንኳ ፈተና አጋጥሞት ቢሆንም ፈተናውን በድል መሻገር የቻልንበት ጊዜ ነበር ባይ ነኝ:: በወቅቱ ከፍተኛ ጫና የደረሰብን ቢሆንም አገራችንን ከመበታተን ማትረፍ የታቻለበት ወቅት እንደሆነ አስባለሁ:: የቱንም ያህል ኢትዮጵያ ዋጋ ብትከፍልም የደረሰችበት ውጤት አስደሳች ነበር::

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው ረገድ ስኬታማ መሆኗ ጥቅሙ ለራሷ ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም የሚተርፍ እንደሆነ ይነገራል፤ ከዚህ አኳያ ለቀጣናው ያበረከተችው ሚና የሚገለጸው እንዴት ነው?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** ኢትዮጵያ በአህጉራችን አፍሪካ በዲፕሎማሲው መስክ የተጫወተችው ሚና ከፍተኛ ነው:: በተለይ በምስራቅ አፍሪካም ሆነ በሌሎችም አካባቢ አስተዋጽኦ አበርክታለች:: በተለይም ደግሞ የቀጣናውን ሰላም በማስጠበቅ ረገድ እና አገሮችን በማስተባበሩ በኩል ሆነ በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ድምጻቸው እንዲሰማ በማድረግ ረገድ የተጫወተችው ሚና አለ:: ይህ ሚና ደግሞ እኛ ስለተናገርነው ሳይሆን በጉልህ የሚታይ ነው::

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግስት እኤአ በ1960ዎቹ አካባቢ የአፍሪካን አንድነት በኢትዮጵያ አዲስ አበባ ውስጥ እንዲመሰረት ማድረግ ተችሏል:: ይህም አፍሪካውያን ለመጀመሪያ ጊዜ የራሳቸው አቋም እንዲኖራቸው በማድረጉ በኩል የራሱ ሚና ያለው ሲሆን፣ እንዲሁም በአንድ ድምጽ መናገር እንዲሞክሩም አድርጓል:: ከዚህ በተጨማሪም አፍሪካውያን ችግሮቻቸውን በራሳቸው ጥረት መፍታት እንዲችሉ ያደረገው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የተቋቋመበት ጊዜ በመሆኑ ኢትዮጵያ የተጫወተችው ሚና እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው ማለት ይቻላል::

**አዲስ ዘመን፡- ከሰሞኑን በኢትዮጵያ እና ራስ ገዝ በሆነችው ሱማሌ ሳንድ መካከል የባህር በርን አስመልክቶ የተደረሰበት ስምምነት አለ፤ ይህ የባህር በር ለማግኘት የተደረገ ስምምነት ከዲፕሎማሲ አኳያ እንዴት ያዩታል?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** ከሱማሌላንድ ጋር የተደረሰው የባህር በር ስምምነት ጉዳይ ጥሩ ታስቦ በድፍረት የተደረገ ነገር ነው:: በነገራችን ላይ በደርግ ዘመነ መንግስት የሱማሌ ላንድ ከኢትዮጵያ ጋር በፌዴሬሽን አንድ ሆነን እንቀጥል የሚል ድምጽ ያሰማችበት ሁኔታ እና ኢትዮጵያ የጠየቀችበት ወቅት ነበር:: እኛ ግን በወቅቱ ድፍረቱ አልነበረንም:: የራሳችንን የውስጥ ችግር ሳንፈታ ሌላ ችግር አንጨምርም የሚል የፈሪ አመለካከት ነበር:: በኢህአዴግም ጊዜ አንዳንድ ሙከራዎች እንዳሉ ሰምቻለሁ:: ይሁንና ተፈጻሚነት ላይ አልደረሱም:: እንደዚያ የሆነበት ምክንያት ደግሞ ‹‹ከእከሌ ጋር ልጣላ እችላለሁ፤ እከሌ በዚህ በኩል ሊጎዳኝ ይችላል›› ከሚል ስጋት የመነጨ ሊሆን እንደሚችልም አስባለሁ:: በትክክልም እንዲዚያ የሚባል ነገር ነበር:: ነገር ግን ሁሌ በፍርሃት ውስጥ መሆን ዋጋ ስለሚያስከፍል ድፍረት አስፈላጊ ነው:: ሰሞኑን የተደረሰበት የባህር በር የማግኘት ስምምነት በትትክክለኛ ውሳኔ የታጀበ ድፍረት በመሆኑ መልካም ነው::

በተለይ አሁን እኛ ያለንበት አካባቢ የሚኖር መንግስት ወይም እንደ ኢትዮጵያ ያለ የሚገባኝን ከፍታ ይዣለሁ የሚል መንግስት በጠንቃቃ እና ልብ ባለው መንግስት የሚመራ ነው፤ መሆን ያለበትም አንደዚያ ነው:: ከዚህ አኳያ ኢትዮጵያ ከሱማሌ ላንድ ጋር ያደረገችው የባህር በር ስምምነት የሚገባትን ከፍታ ለመያዝ የሚያስችላት ነው:: ውሳኔዎችን በድፍረት መወሰን ማለት ደግሞ ዝም ብሎ የመጣ አካሄድ ሳይሆን ግራ ቀኝ ነገሮችን በማየት የተደረሰበት ነው:: ይህ ውሳኔ ሲደረግም ስለጉዳዩ አጥንቶ እና ከሌሎቹም ጋር ተመካክሮ መስራት የግድ አስፈላጊ ነው:: እንደዚያ ካልሆነ ግን ባለህበት እርግጥ ይሆናል::

ስለዚህም በባህር በር ጉዳይ ላይ የተካሔደው ስምምነት በጣም አስፈላጊ ነው:: የባህር በር ሲባል ወደብ ብቻ ማለት አይደለም:: ወደብ የሚያስከትለው ችግር አለ፤ አንድ ወደብ ያለው አገር ወደብ ለሌለው አገር ‹‹ወደብ ባይኖርህም እኔ አንተን አላስተናግድህም›› ሊል ይችላል:: ነገር ግን ይህንን የዓለም አቀፉ ሕግ ይከለክላል::

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንዳሉት፤ ትልቁን ስብራት አስቀምጠን ዝም ብለን መኖር የለብንም:: ትልቁን ስብራት አላየሁም ብሎ መቀጠል የሚቻል አይደለም:: ይህ ጅማሬ በአንድ ጊዜ በአንድ ወቅት መቆም ያለበት ነው:: ይህም እየተከናወነ እንደሆነ አስባለሁ::

የባህር በር ሲባል ከወደብ የተለየ ነው:: ባህር በር ሲኖረን ተጭኖ ወደአገራችን የሚገባ የትኛውም ሸቀጥ በሌሎች ቁጥጥር ስር የሚወድቅ አይሆንም:: በተለይም በሌሎቹ አካላት እንዳይጠለፍም ሆነ እንዳይጎዳ ያስችላል:: ሸቀጣችንን እኛው ራሳችን አጅበን የምናመጣበት ሁኔታ ይፈጠርልናል:: ከዚህ በተጨማሪ የባህር ኃይላችንን በስፍራው መገንባት ስለሚያስችለን ህልውናችንን ያረጋግጥልናል:: ወደምንፈልገውም ከፍታ ለመዝለቅ ያስችለናል::

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ እና በራስ ገዟ ሱማሌ ሳንድ የተሰደረሰውን የባህር በር ስምምነት ከምጣኔ ሀብቱ አኳያስ የሚገልጹት እንዴት ነው?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** ከምጣኔ ሀብት አኳያ ብዙ የተጻፈ ነገር አለ:: በዚህ ጉዳይ ላይ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በርካታ ጥናት አውጥቷል:: በትልቁ የሚጠቅሱት የባህር በር ያለው አገር እና የባህር በር የሌለው አገር እኩል ማምረት ቢችሉ እና በሌላ ሌላ ነገራቸው ተመሳሳይ ሁኔታ ላይ ቢሆኑ አንደኛው አገር የባህር በር ብቻ በማጣቱ እስከ ሁለት ወይም ሶስት በመቶ እድገቱ ሊቀንስ ይችላል::

ስለዚህ የባህር በር የሌለው አገር እንደ ጉዳተኛ ታይቶ እና ተቆጥሮ መረዳት፤ መታገዝ አለበት:: የተለየ እርዳታ ሊደረግለት ይገባል:: ለእነዚህ የባህር በር የሌላቸው አገሮች የተለየ እርዳታ የሚሰጣቸው በባህር በር እጦት ከእጃቸው ሊገባ ያልቻለውን እድገት የሚሸፍን መሆን አለበት:: ይህ እኔ ያልኩት ሳይሆን ዓለም አቀፍ የተቀበለው እውነታ ነው::

ለምሳሌ ጂቡቲ በብዙ መንገድ ከእኛ ጋር የተጣመረች አገር ናት:: እኛ ከእርሷ እንደምንወስድ ሁሉ እርሷም ደግሞ ከእኛ ትወስዳለች:: ሁሉም እንደሚያውቀው የወደብ አገልግሎት ከጂቡቲ እናገኛለን:: በዚህ ሁኔታ በተፈጠረው ግንኙነት አንጻር ጉዳቱ ላይኖር ይችላል:: ነገር ግን በአሁኑ ወቅት ያለምንም ችግር ከጂቡቲ ጋር እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴ ሰላማዊ ነው፤ ችግር የለበትም፤ ጉዳቱ ዛሬ የለም ማለት ግን ነገ አይኖርም ማለት አይደለም:: አይበለውና ነገ እኛ ከአንዳቸው አገር ጋር ብንጣላ የተጣላነው አገር ጂቡቲን ‹‹እኛ ብሩን እንሰጥሻለን፤ በሩን ዝጊ›› ቢሏትስ? ጂቡቲም የተባለችውን ሰምታ ጉዳዩን ብትፈጽምስ? ምን ሊመጣ ይችላል? የምንበላውን ጭምር ሊያሳጣን የሚችል ስለሚሆን በዚህ በኩል ማሰብም ብልኅነት ነው::

ስለዚህ እንዲህ አይነት ሁኔታ ምናልባት ሊፈጸም ይችላል ብሎ ማሰብ ከአንድ መንግስት በእጅጉ የሚጠበቅ ነው:: ሰሞኑን የተደረገው አይነት የስምምነት ርምጃ መውሰዱ ከዚህ አንጻር ተገቢ ነው:: ጠቅላይ ሚኒስትሩ በድፍረት የወሰዱት እርምጃ በጣም አስደስቶኛል:: መንግስት ማድረግ የሚጠበቅበትን ያደረገ ስለመሆኑ ያስመሰከረበት ውሳኔ ነው እላለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያስ ለሱማሌ ሳንድ የአገርነት እውቅና ለመስጠት የመጀመሪያ አገር መሆኗ የሚያመጣባት ጉዳት ይኖረው ይሆን?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** በመጀመሪያ አንድን አገር ማወቅ የሚያስከትለው ጉዳት ምንድን ነው? የሚለው አንድን አገር ማወቅ የአንድ ሌላ ነጻ የሆነ አገር ሉዓላዊ መብቱ ነው:: ለምሳሌ ታይዋን የምትባለውን አገር ቻይና ‹‹የራሴ ናት›› ትላለች:: ነገር ግን ‹‹እኔ አውቄያታለሁ›› ብለው በርካታ አገራት ደግሞ ከታይዋን ጋር ግንኙነት ነበራቸው፤ አሁንም አላቸውም::

በእርግጥ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እንደ አገር አልተቀበላቸውም:: ይሁን እንጂ የተለያዩ አገራት ከታይዋን ጋር የሚያደርጉት ዲፕሎማቲክ ግንኙነቱ ቀጥሎ እናያለን:: ልክ ማንኛቸውም ሁለት ነጻ አገራት እንደሚያደርጉት ሁሉ ታይዋንም ያንን ሁሉ ታደርጋለች፤ እያደረገችም ትገኛለች::

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት አባል መሆን አለመሆን ሌላ ጉዳይ ነው ማለት ነው:: እሱ የዚያ ድርጅት አባላት ውሳኔ የሚጠይቅ ነው:: ከዛ ባለፈ ግን ‹‹እኔ ይህችን አገር አውቄያታለሁ›› ለማለት የሚከለክል ሕግ በዓለም አቀፍ ደረጃ የለም:: ስለዚህ ይህችን አገር እንደ አገር የሚያስጠራትን እውቅና ሰጥቻታለሁ ለማለት የሚያግድ ምንም አይነት ሕግ የለም ማለት ነው::

**አዲስ ዘመን፡- የተለያዩ አገራት እንዲሁም ተቋማት ኢትዮጵያ ከሶማሌ ሳንድ ጋር ያደረገችውን የባህር በር ስምምነት ተከትሎ የተለያዩ መግለጫዎችን አውጥተዋል፤ ይህ አካሄዳቸው ኢትዮጵያ ላይ የሚያሳድረው ጫና ይኖረው ይሆን?**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** ሰዎቹ ወይም የተለያዩ ተቋማት ባወጡት መግለጫቸው እያሉ ያሉት ዳር ዳሩን ስንረዳ ‹‹እናንተ በምታደርጉት ሁኔታ እና ስምምነት የተነሳ የአካባቢው ሰላም እንዳይደፈርስ እና እንዳይናጋ ነው::›› የሚል ነው:: የአሜሪካ መንግስት መግለጫም ሆነ የተባበሩት መንግስታት ደርጅት መግለጫ እንዲሁም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በየመግለጫቸው ያሉት ነገር ቢኖር የአካባቢው ሰላም እንዳይደፈርስ ነው:: ኢጋድንም ያወጣውን መግለጫ ስንረዳ ከእነዚህ ጎራ ውስጥ ሊካተት የሚችል ነው:: ምንም የተለየ እና የሚከለክል ነገር የለውም::

ወደ አውሮፓውያኑ ስንመጣ ግን አንገታችንን ቀና እንድናደርግ የሚፈልጉ አይነት አይደሉም፤ ቀና እንዳንል እና አንገታችንን ወደመሬት እንድንደፋ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እያሳዩት ያለ ባህሪያቸው መሆኑን ልብ ማለት ይቻላል:: ለምን እንደሆነ እስከማይገባኝ ድረስ በኢትዮጵያ ላይ በፊት ያልነበረባቸውን ባህሪ በማሳየት ላይ ያሉ አውሮፓውያን ሆነዋል:: እኔ በስራ ምክንያት ቀደም ባሉ ዓመታት በአውሮፓውያኑ ዘንድ ቆይቻለሁ:: በወቅቱ አሁን የሚያሳዩት አይነት ባህሪ አልነበራቸውም:: ስለሆነም አሁን የእነርሱ ሁኔታ ትንሽ ጠንከር ያለ ነው::

ሌሎቹ ግን የቀጣናው አካባቢ ችግር እንዳይፈጠር ችግራችሁን እዛው ፍቱ ከሚል አመለካከት የተሰጠ መግለጫ ነው ብዬ አስባለሁ:: ስጋታቸውም ችግር እንዳይኖር ከሚል የሚመነጭ ነው:: ከዚህ የተነሳ ሁለቱ አገሮች ተስማምተው የሚያደርጉት ነገር ሰላም እንዳያናጋ ከሚል ፍራቻ እንጂ ‹‹ኢትዮጵያ እንዲህ እና እንደዚህ አድርጋለች ወይም ደግሞ ሱማሌላንድ እንዲህ እና እንዲያ አድርጋ የራሷን መሬት ለኢትዮጵያ አከራይታለች፤ ስለዚህ ይህን ማድረግ ወንጀል ነው፤ ከዚህ የተነሳ እናወግዛቸዋለን››› ብሎ የዘላበደ የለም:: በመሆኑም ኢትዮጵያ ይህን ስምምነት መፈጸሟ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታችን ላይ ሊያመጣ የሚችል አሉታዊ ተጽዕኖ የለም:: መንግስትም እያደረገ ያለው ብልኅነት የተሞላበት እንቅስቃሴ ነው:: ስለዚህ በኢትዮጵያ እና በራስ ገዟ ሱማሌ ላንድ የተደረሰው የባህር በር ስምምነት ስኬታማ ከሆነ እንደማንኛውም ነገር የራሱ የሆነ ጉዳትም ጥቅምም ሊኖረው ይችላል:: ጉዳት እና ጥቅሙ ምን ያህል ነው ብሎ የራስን ውሳኔ መወሰንና እርምጃ መውሰድ እና የተወሰደውን ርምጃ ደግሞ ማስፈጸም የአንድ መንግስት ትልቁ የቤት ስራ ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ::**

**አምባሳደር ጥሩነህ፡-** እኔም አመሰግናለሁ::

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ስኬታማው የሀገር በቀል ኩባንያዎች የኢንዱስትሪ ፓርኮች ተሳትፎ

**አንተነህ ቸሬ**

በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚገኙ 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮች በስራ እድል ፈጠራ፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ እያበረከቱ እና ኢትዮጵያ የአፍሪካ የማምረቻ መነኻሪያ (Manufacturing Hub) እንድትሆን የሚደረገውን ጥረት ለማቀላጠፍም ትልቅ እገዛ እያደረጉ ይገኛሉ::

የኢንዱስትሪ ፓርኮቹንና የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣናን (Dire Dawa Free Trade Zone) በበላይነት የሚያስተዳድረው የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን (Industrial Parks Development Corporation - IPDC) ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በምርት ስራዎች ላይ የሚሰማሩ ባለሃብቶችን ቁጥር ለመጨመርና ከኢንቨስተሮች ጋር ያለውን ትስስር ለማሻሻል አዳዲስ የሪፎርም ተግባራትን ጨምሮ በርካታ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል:: እነዚህ ተግባራትም ብዙ ባለሃብቶች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮቹና ነፃ የንግድ ቀጣናው እንዲገቡ ማድረግ ችለዋል:: በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ከሚገኙ 177 ሼዶች መካከል አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን እየጠበቁ ያሉት 20ዎቹ ብቻ ናቸው፤ 157 ሼዶች በባለሃብቶች ተይዘዋል:: አምስት ፓርኮች (አዳማ፣ ቦሌ ለሚ፣ አዲስ፣ ሰመራ እና ድሬዳዋ (የማኑፋክቸሪንግ ክፍሉ)) በመሙላታቸው አዳዲስ ኢንቨስተሮችን ማስተናገድ አይችሉም::

ኮርፖሬሽኑ ይህን ባለሃብቶችን ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች የማስገባት ጥረቱን ቀጥሎበት፣ ባለፈው ሳምንት ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ለማምረት ፍላጎት ካላቸው 11 ኩባንያዎች ጋር የስራ ስምምነቶችን ተፈራርሟል:: ከኩባንያዎቹ መካከል አብዛኞቹ ሀገር በቀል አምራቾች ሲሆኑ፣ ሦስቱ ድርጅቶች ባለፉት ሦስት ዓመታት ከስራ ውጭ ሆኖ ወደቆየው መቐለ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገቡ ናቸው::

ከ100 ሚሊዮን ዶላር በላይ የኢንቨስትመንት ካፒታል ያስመዘገቡት እነዚህ ኩባንያዎች፤ ወደ መቐለ፣ ጅማ፣ ቦሌ ለሚ፣ ባህር ዳር እና ቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በምርት ተግባራት ላይ ይሰማራሉ:: 31ሺ ካሬ ሜትር የማምረቻ ሼድ እና አራት ነጥብ አምስት ሄክታር የለማ መሬት ይረከባሉ:: በአግሮ-ፕሮሰሲንግ ዘርፎች የሚሰማሩት ኩባንያዎች ከ50ሺ በላይ ለሚሆኑ አርሶ አደሮች ዘላቂ የገበያ ትስስር ይፈጥራሉ:: ኩባንያዎቹ በሙሉ አቅማቸው ማምረት ሲጀምሩ ከአምስት ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል ይፈጥራሉ::

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈፃሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ ኩባንያዎቹ በአግሮ-ፕሮሰሲንግ፣ በአልባሳትና ጨርቃጨርቅ፣ በፋርማሲቲካልና በሌሎች የአምራች ዘርፎች እንደሚሰማሩ ጠቁመው፣ የስራ እድል ለመፍጠር፣ የወጪ ምርት ለመጨመር፣ ገቢ ምርት ለመተካት፣ ጥቅል ሀገራዊ ምርትን ለማሳደግ አዎንታዊ ሚና እንደሚኖራቸው ይገልፃሉ:: ኩባንያዎቹ ለስራ እድል ፈጠራ ከሚያበረክቱት አስተዋፅዖ በተጨማሪ፣ የምርት ተግባራት በቴክኖሎጂ የታገዙ እንዲሆኑ በማድረግ ለቴክኖሎጂና እውቀት ሽግግርን ከፍተኛ አስተዋፅዖ እንደሚያበረክቱና ይህም የምርት ስራዎች ቀልጣፋና ውጤታማ እንዲሆኑ እገዛ እንደሚያደርግ ይናገራሉ::

አቶ አክሊሉ ‹‹ከአስራ አንዱ ኩባንያዎች መካከል አብዛኞቹ ሀገር በቀል ኩባንያዎች ናቸው:: ባለፈው አንድ ዓመት በልዩ ሁኔታ ትኩረት ተሰጥቷቸው ከተከናወኑ ተግባራት መካከል አንዱ የሀገር ውስጥ ባለሀብቱን የማነቃቃት፣ የማበረታታትና ወደ አምራች ዘርፉ ገብቶ ውጤታማ ስራዎችን እንዲሰራ የማድረግ ስራ ነው:: በዚህ ሂደት የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ወደ አምራች ዘርፉ እንዳይገቡ መሰናከል የነበሩ ችግሮችን ለይተን መፍትሄ እየሰጠን እንገኛለን:: በ2016 ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከገቡ አምራቾች መካከል ከ70 በመቶ በላይ የሚሆኑት የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ናቸው›› በማለት የሀገር ውስጥ አምራቾች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች እንዲገቡ ትኩረት ስለመሰጠቱ ያስረዳሉ::

እሳቸው እንደሚሉት፣ ከዚህ ቀደም ለሀገር ውስጥ ባለሃብቶች የሚሰጠው ቦታ አነስተኛ ነበር:: በ2015 እና 2016 ዓ.ም የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች እንዲነቃቁ፣ ባለሃብቶቹ ያሉባቸውን የፋይናንስና ሌሎች ክፍተቶችን የሚሞሉ ተግባራት ተከናውነዋል:: በመሆኑም በ2015 እና ዘንድሮ ከተመዘገቡት ባለሃብቶች መካከል ከግማሽ በላይ የሚሆኑት የሀገር ውስጥ ባለሃብቶች ናቸው::

አንዳንድ ችግሮች ሲፈጠሩ ጓዙን ጠቅልሎ የሚሄድ የውጭ ኢንቨስትመንት ላይ ጥገኛ ሆኖ መቀጠል ተገቢ ስላልሆነና ተወዳዳሪ የሆነ የሀገር ውስጥ ባለሃብት ማሳተፍና መፍጠር አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት የተጀመረው ስራ ውጤት እያመጣ ይገኛል:: ሀገር በቀል ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በምርት ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያሳዩት ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱ፣ የኩባንያዎቹ የማምረት አቅም አድጎ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ተወዳዳሪ የመሆን አቅማቸውም ውጤት እያስመዘገበ መሆኑን ያመላክታል::

ስምምነት ከተፈራረሙት ኩባንያዎች መካከል ሦስቱ፣ ባለፉት ሦስት ዓመታት ከስራ ውጭ ሆኖ ወደቆየው መቐለ ኢንዱስትሪ ፓርክ የሚገቡ እንደሆኑ የሚናገሩት ዋና ስራ አስፈፃሚው፣ ስምምነቶቹ ፓርኩን ወደ ስራ ለመመለስ የሚደረገውን ጥረት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያግዙ ያስረዳሉ::

‹‹የሰላም ስምምነቱ ከተፈረመ በኋላ ፓርኩ ወደ ስራ እንዲመለስ ኮርፖሬሽኑ ኮሚቴ አዋቅሮ ሲሰራ ነበር:: በጦርነቱ ምክንያት ከስራ ውጭ የነበሩ የኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች ወደ ስራ እንዲመለሱ፣ በሞራልም በፋይናንስም እንዲጠገኑና አገግመው ወደ ስራ መንፈስ እንዲመለሱ ጥረት ተደርጓል፤ ያልተከፈላቸው ውዝፍ ደመወዛቸውም እንዲከፈላቸው አድርገናል›› ብለዋል::

እሳቸው እንዳብራሩት፤ በፓርኩ ውስጥ በምርት ስራዎች ላይ ተሰማርተው የነበሩ ባለሃብቶች ስራ አቋርጠው ወጥተው ስለነበር ወደ ስራ እንዲመለሱ ተደጋጋሚ ውይይቶች ተደርገዋል:: ፓርኩ በጦርነቱ ጉዳት ባይደርስበትም ውስን ጥገናዎች ተደርገውለት በሙሉ ቁመና ለስራ ዝግጁ እንዲሆን ተደርጓል:: በዚህ ውጤታማ ጥረት ነባር ኢንቨስተሮችን ወደ ስራ መመለስ ብቻ ሳይሆን፣ ከሦስት ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ሦስት አዳዲስ ኢንቨስተሮች ወደ መቐለ ኢንዱስትሪ ፓርክ ለመግባት የሚያስችላቸውን የስራ ስምምነት እንዲፈርሙ ማድረግ ተችሏል::

የኢንቨስትመንት ዘርፍን ለማሳደግ በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ጥራቱን የጠበቀና ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ያለው አገልግሎት እየተሰጠ እንደሚገኝ የሚናገሩት ዋና ስራ አስፈፃሚው አቶ አክሊሉ፤ የሀገር ውስጥና የውጭ ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው እንዲያመርቱ ኮርፖሬሽኑ በልዩ ትኩረት ክትትልና ድጋፍ እንደሚያደርግ ይናገራሉ:: ኮርፖሬሽኑ ካለፈው አንድ ዓመት ወዲህ ተግባራዊ ባደረጋቸው የሪፎርም ተግባራት አማካኝነት ለዘመኑ የሚመጥን እና ለኢንቨስተሮች ምቹ የሆነ የኢንቨስትመንት አመራርና አስተዳደር ለማስፈን ጥረት እያደረገ ይገኛል ይላሉ::

‹‹ግልፅ የሆነ የኢንቨስተሮች መመልመያ መስፈርት፣ ቀጥተኛ የዓለም አቀፍ የኢንቨስትመንት ፕሮሞሽን/ማስተዋወቂያ/ ዘዴዎች እና የሀገር ውስጥ ባለሃብቶችን የማበረታቻ ማዕቀፎች ዝግጅት፤ አዲስ የመዋቅር ጥናትና ትግበራ፤ የባለድርሻ አካላት ቅንጅታዊ ትብብር መፍጠሪያ እና የዲጂታል አሰራር ስርዓት ተግባራት ኮርፖሬሽኑ እየተገበራቸው ከሚገኙት የሪፎርም ስራዎች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው:: በእነዚህ ተግባራት አማካኝነት የባለሃብቶችን ቁጥርና የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን ምርታማነት ማሳደግ ተችሏል›› ሲሉም አስታውቀዋል::

‹‹ጽንኤል ኢንዱስትሪያል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር›› ከኮርፖሬሽኑ ጋር ስምምነት ከተፈራረሙ ኩባንያዎች መካከል አንዱ ነው:: ከ16 ሚሊዮን ዶላር በላይ የኢንቨስትመንት ካፒታል ያስመዘገበው ይህ ሀገር በቀል ኩባንያ፣ ቆርኪ በማምረት ላይ ተሰማርቶ ይገኛል:: ኩባንያው የምርት ስራውን በቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ በተረከበው 10 ሺ ካሬ ሜትር የማምረቻ ሼድ ላይ የሚያከናውን ይሆናል:: ምርቶቹን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ሀገራት ገበያዎች የማቅረብ እቅድ ያለው ይህ ድርጅት፣ ለ115 ዜጎች ቋሚ የሥራ እድል እንደሚፈጥርም ይጠበቃል::

የኩባንያው መስራችና ባለቤት ወይዘሮ ብርቱካን አበበ ድርጅታቸው ቆርኪ በማምረት ከ12 ዓመታት በላይ ልምድ እንዳለው ጠቁመው፣ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ጋር የተፈራረሙት ስምምነት የምርት ስራቸውን ለማስፋትና አቅርቦታቸውን ለመጨመር ትልቅ እገዛ እንደሚያደርግላቸው ይገልፃሉ::

በተሻለ አቅም ለማምረት የማምረቻ ቦታ እጥረት እንደነበረባቸው የሚናገሩት ወይዘሮ ብርቱካን፣ ከኮርፖሬሽኑ ጋር ያደረጉት ስምምነት ይህን ችግር እንደሚፈታላቸው ይገልፃሉ:: ‹‹ኩባንያችን የውጭ ምንዛሪ በማዳን ረገድ ትልቅ ሚና ባለው ተኪ ምርት የማምረት ተግባር ላይ የተሰማራ ቢሆንም የቦታ ችግር ነበረበት:: ከኮርፖሬሽኑ ጋር ያደረግነው ስምምነት ለዚህ ችግር መፍትሄ ይሆናል:: የማሽን ተከላ ስራዎችን በፍጥነት በማጠናቀቅ ስራ ለመጀመር እየተዘጋጀን እንገኛለን:: የመጠጥ ምርቶች ዘርፍ ትልቅ የገበያ ፍላጎት ያለው በመሆኑ ዘርፉ በሚፈልገው ጥራትና ብዛት ልክ ግብዓት ማቅረብ ብዙ ጥቅሞች አሉት:: ይህን ምርት ሀገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሪ ማዳን ከኤክስፖርት ያላነሰ ፋይዳ አለው›› ይላሉ::

የ‹‹ዶክተር ማርቆስ ኩባንያ›› ባለቤት ዶክተር ማርቆስ ገሰሰ በበኩላቸው፣ የሰላም ስምምነቱ የፈጠረውን መልካም አጋጣሚ በመጠቀም ወደ መቐለ ኢንዱስትሪ ፓርክ በመግባት የህክምና ቁሳቁስን በማምረት ስራ ላይ ለመሰማራት ማቀዳቸውን ይገልፃሉ:: እሳቸው እንደሚሉት፣ የህክምና ቁሳቁስ በከፍተኛ መጠን ተፈላጊ በመሆናቸውና ኢትዮጵያ እነዚህን ቁሳቁስ በብዛት ከውጭ የምታስገባ በመሆኑ በዘርፉ መሰማራት ለሀገርና ለህዝብ እጅግ አስፈላጊ፣ ለባለሃብቶችም አዋጭና አትራፊ ነው::

ቀደም ሲል በመቐለ ከተማ በህክምና ኢንቨስትመንት ተግባር ላይ ተሰማርተው እንደነበር የሚያስታውሱት ዶክተር ማርቆስ፣ ወደ መቐለ ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብተው የሚሰማሩበት ስራ ለ127 ዜጎች የስራ እድሎችን እንደሚፈጥር ይገልፃሉ:: በአምስት ሺ 500 ካሬ ሜትር ላይ ባረፈ አንድ ሼድ ውስጥ የሚከናወነው የዶክተር ማርቆስ ኩባንያ የምርት ስራ፣ ከስድስት ወራት እስከ አንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተጠናቅቆ ማምረት እንደሚጀምር ዶክተር ማርቆስ ገሰሰ ተናግረዋል::

> **ሀገር በቀል** ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው በምርት ስራ ላይ ለመሰማራት የሚያሳዩት ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱ፣ የኩባንያዎቹ የማምረት አቅም አድጎ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር ተወዳዳሪ የመሆን አቅማቸውም ውጤት እያስመዘገበ መሆኑን ያመላክታል

# ጎሜ

# ብሔራዊ ጥቅም - የሁላችንም ጉዳይ!

**አሲ ሴሮ**

ብሔራዊ ጥቅም በአስተሳሰብም ሆነ በድርጊት ለሀገርና ለሕዝብ ሲባል የሚከፈል ዋጋ ነው:: ዋጋው መስዋዕትነትንም የሚጨምር ነው:: ሀገር እና ሕዝብም የሚጸኑትና ከአሰቡትም ደረጃ መድረስ የሚችሉት ብሔራዊ ጥቅም ሲከበር ነው:: ብሔራዊ የጥቅሙን የማያስከብር ሀገር ሉአላዊነቱን ማስጠበቅ አይችልም:: ህልውናውም አደጋ ላይ የወደቀ ነው::

ሀገራት እንደነባራዊ ሁኔታቸውና በየወቅቱ እንደሚያጋጥማቸው ችግር የብሔራዊ ጥቅም አጀንዳን ይቀርጻሉ:: ይህን ብሔራዊ አጀንዳ ምንነትና አስፈላጊነት በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ መረጃ ይሰጣሉ፤ በሕዝቡ ዘንድ ቅቡል እንዲሆን ተግባቦት ይፈጥራሉ:: ይህ ሲሆን ወጣት አዛውንቱ፤ ሴት ወንዱ ያለምንን የቀለም፤ የብሄር፤ የኃይማኖት ሌሎች ልነቶች ሳይገድቡት ከብሔራዊ ጥቅሙ ጎን ይቆማል:: መከፈል ያለበትን መስዋዕትነት ይከፍላል:: እኛስ ?

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሉአላዊነቱ ቀናኢ ነው:: በየዘመናቱም ከውስጥና ከውጭ የተቃጡ ሉአላዊነትንና የግዛት አንድነትን የሚፈታተኑ ተግባራትን በጽኑ ታግሎ ሀገሪቱን ከነሙሉ ክብሯ ለአሁኑ ትውልድ አስረክቧል::

ኢትዮጵያውያን በሀገራችን ህልውና ለመጣ ቀልድ አናውቅም:: ቤቴ፤ ዕርስቴ፤ ሚስትና ልጆቼ ሳንል ሀገራችንን አስቀድመን እራሳችንን ለመስዋዕትነት እናቀርባለን::

በደምና አጥንታችንም ሉአላዊነታችን እናስከብራለን፤ ነጻነታችንንም እናረጋግጣለን:: አልፎ ተርፎም በኮርያ፤ በኮንጎ፤ በላይቤሪያ፤ በሶማሊያ፤ በሩዋንዳና ብሩንዲ እንዲሁም በሱዳን በመዘመት በግጭትና በጦርነት ውስጥ የገቡ ሀገራትን እናረጋጋለን፤ ወደ ሰላማቸው እንመልሳለን::

በአጠቃላይ በእናት ሀገራችን ለመጣብን ጨርቄን ማቄን ሳንል ህይወታችንን እንሰጣለን፤ አጥንታችንን እንከሰክሳለን፤ ደማችን እናፈሳለን:: እምቢ ለሀገሬ በማለት ብሔራዊ ጥቅማችንን እናስከብራለን::

ሆኖም አሁን አሁን የሚታዩ ዝንባሌዎች ይህንን ኢትዮጵያዊ ማንነት የሚገዳደሩና እየዋሉ፤ እያደሩ ከሄዱ የሀገርን የሕዝብ ጥቅም አደጋ ላይ የሚጥሉና ብሎም ሀገርንም የሚያፈርሱ ይሆናሉ:: ሰሞኑን ኢትዮጵያ ከሶማሌ ላንድ ጋር የባሕር በር ለማግኘት የተፈራረመችውን የመግባቢያ ሰነድ በተመለከተ የተሰሙ አንዳንድ ድምጾች አስደንጋጭ ናቸው:: አንዳንዶቹ አስተያየቶች ከአንድ ኢትዮጵያዊ ሊደመጡ የማይገባና ዜግነትንም ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ነው ::

የኢትዮጵያ ወደብ አልባ መሆንም ከስነ ልቦናዊ ቀውስ ባሻገር ለበርካታ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ጫና ሕዝቡ እንዲጋለጥ አድርጎታል:: የኢትዮጵያን ክብርና ዝና ዝቅ እንዲል ከማድረጉም ባሻገር በኢኮኖሚ ረገድም ተጎጂ እንድትሆን አድርጓታል:: ለበርካታ መሰረተ ልማቶችና ለድህነት መቀነሻ ልማቶችን ይውል የነበረውን ከ1 ነጥብ 6 ቢሊዮን ዶላር በላይ በየዓመቱ ለወደብ ብቻ በማዋል በድህነት ውስጥ እንድትማቅቅ አድርጓታል:: ኢትዮጵያ ወደብ አልባ በመሆኗ ለኪራይና ለመጓጓዣ ከፍተኛ ዶላር ስለምታፈስ የሸቀጦች ዋጋ እንዲንርና የኑሮ ውድነትም እንዲባባስ ምክንያት ሆኗል::

በዲፕሎማሲ እና በተጽዕኖ ፈጣሪነትም ረገድ የኢትዮጵያ ሚና አሽቆልቁሏል:: ኢትዮጵያ የምትገኝበት የአፍሪካ ቀንድ በዓለም እጅግ ተፈላጊ ከሆኑትና የሃያላን ሀገራትንም ቀልብ የሚስብ በመሆኑ እድገቷን የማይፈልጉ አካላት በተቀነባበረ ሴራ ከቀይ ባሕር እስኪያርቋት ድረስ ገናና እና በሁሉም ዘንድ ተፈላጊ ሆና ቆይታለች:: ሆኖም ሀገሪቱ ወደብ አልባ ከሆነች ጀምሮ ተፈላጊነቷ አሽቆልቁሏል::

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ወደብ አልባ ከሆኑት 16 ሀገራት አንዷ ብትሆንም ወደብ አልባ የሆነችባቸው አመክንዮዎች ግን ታሪካዊም ሆነ ሕጋዊ መሰረት የሌላቸው ናቸው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ 126 ሚሊዮን ደርሷል:: በአጠቃላይም በኢትዮጵያ የሚኖረው ሕዝብ የባሕር በር የሌላቸውን ሀገራት ሕዝብ 1/3ኛውን ይሸፍናል::

ይሄንን የሚያህል ሕዝብ ይዞ የባሕር በርና ወደብ የተነፈገ ሀገር የለም:: ሁለተኛው ጉዳይ ደግሞ ኢትዮጵያ በባሕር በር የተከበበች ሀገር ነች:: ከላይ እንደጠቀስኩት በሴራ እና በተሳሳተ ትርክት ከቀይ ባሕር እንድትርቅ ከመደረጓ በስተቀር በአፈጣጠሯ ለቀይ ባሕር የቀረበ ነው:: በሶስተኛ ደረጃ በታሪክም በቀይ ባሕር ላይ ለዘመናት የበላይ ሆና መቆየቷን የሚያሳዩ በርካታ ማስረጃዎች ያሏት ሀገር ነች::

ስለዚህም ኢትዮጵያ በግፍ ከይዞታዋ እንድትነቀል ከመደረጓ ውጪ ባለቤትነቷን የሚከለክላት አንዳችም ዓለም አቀፍ ሕግ የለም:: ኢትዮጵያ ወደብ አልባ የሆነችበትም ሆነ ከቀይ ባሕር እንድትወገድ የተደረገበት አካሄድ ምንም አይነት ሕጋዊ መሰረት የሌለው ነው:: ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር እንድትወገድና ወደብ አልባ እንድትሆን የተደረገው በ1900፤ 1902 እና 1908 ከቅኝ ገዢዎች በተደረጉ ውሎች አማካኝነት ነው:: እነዚህ ውሎች ደግሞ በተባበሩት መንግስታት መመስረቻ ቻርተር ሕጋዊነታቸውን አጥተዋል::

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሲቋቋም ካወጣቸው ድንጋጌዎች አንዱ ሀገራት የቅኝ ግዛት ውሎችን የመቀበል ግዴታ እንደሌለባቸው የሚደነግገው አንቀጽ አንዱ ሲሆን ኢትዮጵያ በቅኝ ግዛት ያልተገዛች ሀገር ካለመሆኗም ባሻገር በቅኝ ገዢዎች የተረቀቁትን የ1900፤ 1902 እና 1908 ውሎችን የመቀበል ግዴታም የለባትም::

ኢትዮጵያ የባሕር በር እንድታጣ ከሆነችባቸው ውሎች መካከል የቅኝ ግዛት ውሎች ተጠቃሾች ናቸው:: ከአጼ ሚኒሊክ ጀምሮ ኢትዮጵያ ከቅኝ ገዢዎች ጋር ያደረገቻቸው ስምምነቶች የባሕር በሯን አሳጥተዋታል:: የቅኝ ግዛት ስምምነቶች በባህሪያቸው ቅኝ ሲገዙ የነበሩ ኃይሎች በአስገዳጅ መልኩ ቀኝ ገዢዎች ላይ የፈጸሙት ደባ ነው:: ስለዚህም ውል ከማለት ይልቅ በጉልበተኛና በደካማ መካከል የተፈጸመ አስገዳጅ ስምምነት ነው ማለት ይቻላል:: እነዚህ ውሎች የቅኝ ገዢዎችን እንጂ የተገዢዎችን ሙሉ ፈቃደኝነት የያዙ አይደሉም::

ስለዚህም ኢትዮጵያ የፈረመቻቸው የ1900፤ የ1902 እና የ1908 ውሎች ገዢ ውሎች አይደሉም፤ ስለዚህም ተፈጻሚነት አይኖራቸውም:: እነዚህ ውሎች በተባበሩት መንግስታት ማቋቋሚያ ቻርተር ላይም ተፈጻሚነት እንደማይኖራቸው በግልጽ ተደንግጓል:: እነዚህንና ሌሎች አጋዥ ዓለም አቀፍ ሕጎችን በመንተራስ ኢትዮጵያ ዛሬ ፊቷን ወደ ባሕር በር አድርጋለች::

በኢትዮጵያ አዲስ የመንግስት ለውጥ ከመጣ ጀምሮ በትኩረት ከሰራባቸውና ለውጥ ካመጣባቸው ጉዳዮች አንዱ የባሕር በር ጥያቄ ነው:: መንግስት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ለዘመናት ቁጭት ፈጥሮ የነበረውን የባሕር በር ጥያቄ በመመለስና ስብራትን በመጠገን ታሪካዊ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል:: ለ27 ዓመታት ያህል ፈርሶ የቆየውን የባሕር ኃይል እንደገና በማደራጀት ኢትዮጵያ እንደገና የባሕር ኃይል እንዲኖራት አድርጓል::

ከዚሁ ጎን ለጎንም ኢትዮጵያ ከ33 ዓመታት በኋላ የባሕር በር የምታገኝበት አማራጭ ተገኝቷል:: ሰላማዊ አማራጭን ሲከተል የቆየው የኢትዮጵያ መንግስት ሰሞኑን ከሶማሌ ላንድ ጋር የባሕር በር የሚገኝበትን መግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) ተፈራርሟል::

ይህ ሲሆን ታዲያ በርካታ ዜጎች ተደስተዋል:: የኢትጵያን መበልጸግ የሚሹ ወገኖችም በሁኔታው በጣም ተገርመዋል፤ አድናቆታቸውንም ገልጸዋል:: ሆኖም ሶማሌ ሪፑብሊክ፤ ግብጽና አረብ ሊግ ተቃውሟቸውን ገልጸዋል:: የሶማሊያ ሪፐብሊክ የሚጠበቅ ሲሆን ግብጽና አረብ ሊግ ግን በማይመለከታቸው ጉዳይ መግባታቸው አስገራሚ ነው:: ከዚሁ ጋር ተያይዞ ግን አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ከግብጽና አረብ ሊግ እኩል የኢትዮጵያና የሶማሊ ላንድ የባሕር በር ስምምነትን እኩል ሲቃወሙ መስማት በእጅጉ ያሳምማል፤ ወዴት ነው እየሄድን ያለነው የሚለውን ጥያቄም ያጭራል::

በዚሁ ጉዳይ ላይ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ሚኒስትር ሬድዋን ሁሴን እንዳሉት‹‹ የአንዳንድ ሀገራት ተቃውሞ የሚጠበቅ ነው፤ የሚገርመው ግን ኢትዮጵያዊ የሆኑና የእኛ ያልናቸው ሰዎች የበለጠ ሲጮሁ መስማታችን ያስገርማል›› ብለዋል:: የእሳቸውም ንግግር ከላይ ያልነውን ሃሳብ የሚያጠናክር ነው::

ኢትዮጵያ በውስጥ ጉዳያቸው ቢለያዩም በብሔራዊ ጥቅምና በህልውና ጉዳይ ተለያይተው አያውቁም:: የባሕር በር ጉዳይ ደግሞ የህልውና ጉዳይ ጭምር ነው:: ጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አሕመድ በጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም ላይ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርበው ለኢትዮጵያ የባሕር በር ማግኘት “የህልውና ጉዳይ ነው” ሲሉ መናገራቸው የሚታወስ ነው:: እንደዚህ ከሆነ ደግሞ በሀገር ህልውና ላይ የተቃጣ አስተያየት ወይም ነቀፌታ መስጠት ሌሎችን ያስደስት እንደሆነ እንጂ እንደ ሀገር የሚሰጠው ጥቅም የለም፤ እንደውም በሀገር ብሔራዊ ጥቅም ላይ ተለያይቶ መገኘት ለጠላቶች በር ይከፍት እንደሆን እንጂ አንድነትን አያመጣም::

ሁኔታውን የበለጠ የሚያገዝፈው ደግሞ ይህንን የልዩነት አስተያየት የሚሰጡት ተማሩ፤ አወቁ የምንላቸው ሰዎች ሆነው መገኘታቸው ነው:: ከእነዚህ ሰዎች በሳል አመራርን፤ አብሮነትን፤ ሀገራዊ ጥቅምንና የሕዝብ ተጠቃሚነትን የሚያጎሉ ሃሳቦችና ምሁራዊ ትንታኔዎች መቅረብ ሲገባቸው በአንጻሩ በወደብና የባህር በር እጦት የሚንገላታውን ዜጋ የበለጠ ወደ ጨለማው የሚወስዱ አስተሳቦችን ማስረጽ ከአንድ ከተማረ ዜጋ የሚጠበቅ አይደለም::

የኢትዮጵያን ማደግ በማይፈልጉ ኃይላት ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር እንድትወገድ ተደርጓል:: ለዘመናትም ኢትዮጵያ ከቀይ ባሕር ምንም ድርሻ እንዳልነበራት ሆን ተብሎ በተሰራጨው ትርክት ኢትዮጵያና ቀይ ባሕር ተቆራርጠው ኖረዋል:: ከሕዝቡ ልብ ውስጥ ቀይ ባሕርን ማውጣት ባይቻልም ስለቀይ ባሕር ማሰብና ማውራት እንደ ሀጢያት ሲቆጠር ቆይቷል:: ባለፉት 30 ዓመታት ስለ ወደብና ባሕር በር ማውራትም ሆነ የኢትዮጵያን የባለቤትነት መብት መጠይቅ እንደነውር ከማስቆጠሩም በላይ ጸብ አጫሪ አስብሎም በነገረኛነት ያስፈርጅ ነበር::

ዛሬ ዕድሉ ሲከፈት ሁኔታውን መደገፍና አለፍ ብሎም ምሁራዊ አስተዋጽኦ ማበርከት ሲገባ ተቃዋሚ መስሎ መገኘት አግባብ አይደለም:: ጭራሹኑም አንዳንድ ምሁራን በፖለቲከኝነት እፈረጃለሁ በሚል ስጋት በወደብና በባሕር በር ዙርያ እንኳን መረጃ ለመስጠት ፍላጎት ሲያጡ ይታያል::

ጋዜጠኞች ለአንዳንድ ምሁራን ስልክ ደውለው መረጃ በባሕር በር ጉዳይ ስጡኝ በሚሉበት ጊዜ የሚያጋጥማቸው ተግዳሮት ‹‹ይህንን ብናገር በፖለቲከኝነት እፈረጃለሁ፤ የገዢው ፓርቲ አባል እባላሁ ወዘተ››የሚል ፍራቻ ነው:: ሆኖም የባሕር በርም ሆነ የወደብ ጉዳይ ከአንድ መንግስት ወይም ፓርቲ ህልውና ጋር በፍጹም ሊተሳሰር የማይችልና ሀገርና ዜጎች እስካሉ ድረስ የሚዘልቅ ነው:: ስለሆነም እራስን ለወቅታዊ ፍራቻ እያስገዙ መሄድና በምን ይሉኛል ስሜት ታጥሮ መጓዝ ከአንድ ምሁር የሚጠበቅ አይደለም::

ምሁራን ሕዝብ እና ሀገርን አስቀድመው የሚንቀሳቀሱ እውነት ፈላጊዎች ናቸው:: ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅም እውነተኛ ሃሳብ እስከያዙ ድረስ ‹‹እገሌ እንዲህ ይለኛል፤ በእዚህ እፈረጃለሁ›› በሚል ስጋት ከምሁራዊ ደረጃቸው ሊወርዱ አይገባም::

የዛሬ ምሁራን ትላንት በሕዝብ ሀብትና ገንዘብ የተማሩ ናቸው:: ስለዚህም ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅም ሃሳብ ላይ መሳተፍና የሕዝብን ጥቅም ማረጋገጥ አለባቸው:: በዚህም ላይ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ መረጃ የመስጠት የሞራል ግዴታ አለባቸው:: ጊዜ አይቶ መረጃ መስጠት እና መንፈግ የምሁራን ባህሪ አይደለም::

ይህ ችግር የምሁራን ብቻ አይደለም:: ይበልጡኑ የመንግስት ኃላፊዎችን የሚመለከት ነው:: የመነግስት ኃላፊዎች በወቅቱ መረጃ መስጠት ግዴታ እንዳለባቸው እየታወቀ ብዙዎቹ ዳተኛ ሆነው ይገኛሉ:: መንግስት ኃላፊዎች የሕዝብና የሀገር ጥቅምን የሚያስከብሩና ብሔራዊ ጥቅምን የሚያረጋግጡ መረጃዎችን ጭምር ለመስጠት የእናቴ መቀነት አደናቀፈኝ ሲሉ መስማት የተለመደ ነው::

ሆኖም ብሔራዊ ጥቅም ለአንድ ለተወሰነ የመንግስት መሪ ወይም ሕዝብ የሚተው ሳይሆን ሁሉም በሙያው፤ በእውቀቱ፤ በገንዘቡ፤ በፍላጎቱ ወዘተ ሊደግፈው የሚገባና መስዋዕትነትም የሚጠይቅ ከሆነ ይህንኑ መክፈል የሚጠይቅ ነው::

**ምሁራን ሕዝብ እና ሀገርን** አስቀድመው የሚንቀሳቀሱ እውነት ፈላጊዎች ናቸው። ለሀገርና ለሕዝብ የሚጠቅም እውነተኛ ሃሳብ እስከያዙ ድረስ ‹‹እገሌ እንዲህ ይለኛል፤ በእዚህ እፈረጃለሁ›› በሚል ስጋት ከምሁራዊ ደረጃቸው ሊወርዱ አይገባም

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

## መንገሳ ነው ባህላቸው ቾለሎቴ ዜማቸው

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ቋንቋቸው ጉራማይሌ ነው። ባህላቸውም የትየለሌ፤ የአይን ውበት፣ የማንነት ድምቀት ናቸው። በኢትዮጵያዊነት ልክ የተሰፉ የኢትዮጵያዊነት ሸማ ናቸው። የኢትዮጵያን ቱባ የባህልና ጥበብ ውበት ፍለጋ ጓዙን ሸክፎ ለወጣ ደመ ነብሱ ወደዚያች እጹብ ምድር ይመራዋል። ወደ ማዕከላዊቷ ኢትዮጵያ፤ ወደ ዛላዎቹ ምድር ያመራ ሰው ልክ እንጎደኔ እንዲህ ማለቱ አይቀርም።

ባጥቢያ ውበት በኦጎቴ፤
አዴ ጉባ . . .
ሚሽላ ሚሽላ ቾለሎቴ፤
በሴራችሁ ይሁን ሞቴ፤
ኢዮሲማ ሀራባኒ በማለቴ።
ነቅታችኋል በነቀታ፤ በመንገሳ፤
ስነቃሉ ብዙ ቢሆን የቱን ላንሳ፤
ኢዮሲማ ሲሉ ሰማሁ ኦሮሪማ፤
ሚዮሲማ ኦሮሪማ ሀላባኒ ቃራሪማ።
ዛላ እኮ ነው በርበሬያቸው፤
ያ ለምለሙ ምድራቸው፤
ሀመልማሎው ምግባቸው፤
ጥም ቆራጭ ነው ፍቅራቸው።
ቋንቋውቸውም ጉራማይሌ፤
ጭፈራቸው ቾለሎቴ ፤
ቃላ ቢሆን ሪብሪቦቴ፤
ሀላቢዮ ሀላብ ጎቴ።
አዴ ጉባ አዴ ሲሉት፤
አዬ ወዬ ሲባዬነት፤
ጥበብ ናቸው በጥበባት፤
በሙህባው ቅኔ ውበት።

በሀላባ ምድር፤ በሀላባውያኑ መንደር በባህልና ሥርዓት መኖር ምርጫ አይደለም። ፍቅርን ለብሶ በፍቅር ማጌጥ ባህል እንጂ ታይታ አይደለም። ከጥበብ ጋር ኖሮ ከጥበብ ጋር መሞት፤ ኪነ ጥበብን በየአይነቱ በየፈርጁ መስማትም ሆነ ማየት ከቶውን ብርቅ አይደለም። ስለ ኪነ ጥበብ ስላወቁና ስለተረዱ "ምን ልሥራ . . . እንዴት ልሥራ?" ብለው ሳይሆን የሚወዱትና የሚሳሱለት ያ ውብ ባህላቸው እራሱ ኪነ ጥበብ በመሆኑ ነው። ሀላባና ነዋሪዎቿን ብሎ የወጣ፤ እሩብ ጨረቃ መሳይ ዛላ በርበሬያቸውን ብቻም ሳይሆን ያልተሰሙና ያልታዩ የባህልና የኪነጥበብ ወንዞቻቸው በአራቱም አቅጣጫ ሲፈሱ ይመለከታል። የጥበብ ባለጸጋዎቹ ሀላባውያን የበርካታ ጥበባት ባለቤት ናቸው። እጅግ የሚያምሩ ፉከራና ሽለላዎች፣ የወንዶችና የሴቶች ሙዚቃዊ ጨዋታዎች፣ የስነ ግጥም ሀብቶቻቸው አጃኢብ የሚያስብሉ ናቸው። ከጥንት እናትና አባቶቻቸው ቃላዊ በሆነ የቅብብሎሽ መንገድ የመጡ ስነቃላዊ የባህል ትውፊቶቻቸው ናቸው። ባህሎቻቸውን የሚገልጹት ኪናዊ ለዛን በተጎናጸፈ መልኩ በመሆኑ ባህላቸውን ከኪነጥበብ ለመለየት አይቻልም። የእምቅ ጥበባት ባለቤት ናቸው። ከእነዚህም ስነቃላዊ ግጥሞቻቸው አንደኛው ነው። አብዛኞዎቹ በሙዚቃዊ ቅላጼ የሚዜሙ ቢሆኑም አንዳንዶቹ ግን የዜማ ሥርዓትን አይከተሉም።

"ቃላ" በሀላባ ሴቶች ዘንድ ብቻ የሚዜም ባህላዊ የሴቶች ዘፈን ነው። አዘውትሮ ከመጫወት ይልቅ ቃላ የራሱ የሆነ ጊዜና ቦታ እንዲሁም ሥርዓት አለው። ጀግናን ይበልጥ ያጀግኑበታል። ስመጥሮቹን በስም እየጠሩ ያሞግሱበታል። በዋናነትም አንድ ነገር አለ፤ በማህበረሰቡ የሴራ ሥርዓት መሠረት በአዋቂነቱና በዳኝነት የአስተዳደር ችሎታው ተመርጦ የመጨረሻውን የስልጣን ደረጃ ለሚሰጠው የማህበረሰቡ አውራ ለሆነው "ኢማም" እንዲሁም የኢማሙን ዘርና ጎሳ ለማወደስ ይጠቀሙበታል።

ኮራኮሮሔ ኖጋይ
ሀላቢ ኦ . . . ሶጋሔ
....

እያለች የዜማው መሪ የሆነችው ሴት ባማረ ቅላጼ ስታዜም፤ የቡድኑ አባላት ይህንኑ ግጥም በመድገም በእኩል ይሉታል። በሀላባ ማህበረሰብ ሁሉም የራሱ የሆነ ጥበባዊ የባህል ቅኝት አለው። ሴቶቹ በቃላ የሙዚቃ ስልት ጨዋታቸውን ሲያደሩ፤ ወንዶቹ ደግሞ በቾለሎቴና ሪብሪቦቴ ዜማዎቻቸው በህብራዊ ቃና የደስታን ማማ ይረግጡበታል። ታዳጊ ልጆችም ቢሆኑ ከጥበብ መንደር አይጎድሉም። ከዓመት ዓመት በልዩ ልዩ ጨዋታዎቻቸው ፍልቅልቅ ብለው ይኖራሉ፤ ከሁሉም ግን ወርሃ ጥር ወይንም በእነርሱ አጠራር የ"መንገሳ" ወር ከሁሉም ይለያል። ለእነዚህ ልጆችም ወሩ የተቀደሰና ዓመቱን ሙሉ በጉጉት የሚጠብቁት ነው። የራሳቸው የሆነ የዘመን አቆጣጠር ባለቤት የሆኑቱ፣ የሀላባውያኑ የዘመን መለወጫ



ወይንም "መንገሳ ሴራ" በዚሁ ወር ላይ ነው። የልጆቹን ልብ በጉጉት ቀጥ ማድረጉ ክብረ በዓልነቱ ብቻ ሳይሆን በዓሉን ተከትሎ ለልጆቹ የሚመጡ በርካታ ነገሮች በመኖራቸው ነው። የልጅነት ወግ ማዕረጋቸውን የሚያዩበት የተለየ ዓለማቸው ነው። የሚፈልጉት ሁሉ ይደረግላቸዋል። ልብስ ይገዛላቸዋል። በመንገሳ ያልተገረዙ ይገረዙበታል፤ የሚጠብቃቸውም ብዙ ነው። ተልከው ሲሮጡም ሆነ ከብቶቻቸውን ከሜዳ ግጦሹ ሲያሰማሩ ከእጃቸው ዋሽንት፤ ከአፋቸው ሙዚቃ አይጠፉም። በግልም ሆነ በጋራ "መንገሳ" የምትለዋን የባህል ዜማቸውን በናፍቆት ያዜማሉ።

የሀላባ ማህበረሰብ አልባሳቱ የባህሉ ጌጥ ናቸው። ውበቱን የሚያንጸባርቅበት በመሆኑ የተለየ ፍቅርና ክብር ለአልባሳቱ አለው። ሴቶቹ "ቆሜ" የተሰኘውን የባህል ልብሳቸውን ጨምሮ በልዩ ልዩ ዲዛይን በተሠሩ አልባሳቶቻቸው ማጌጥ የአንዳንድ ጊዜ ሳይሆን የሁሌም ልማዳቸው ነው። ወንዶቹም፤ መለያቸው በሆነው ባለ ቀለም ቆብና ባለ ዘርፉ ቁምጣ በሄዱበት ሁሉ መድመቂያቸው ነው። ሴቶች ሴትነታቸውን፤ ወጣቶች ወጣትነታቸው ለማሳየት ከአልባሳቱና ጌጣ ጌጡ በስተጀርባ ሁሌም ሙዚቃ ሁሌም ኪነ ጥበብ አለ። ከአመጋገብ እስከ አጊያጌጥ፤ ከባህላዊው ሙዚቃና ጭፈራ እስከ ልዩ ልዩ ትውፊታዊ ክንዋኔዎቻቸው ድረስ ከሴራ ባህላቸው ጋር የተቆራኘ ነው። በሀላባውያኑ የሴራ ክብረ በዓል ዕለት ዘንካታው ሶታ ጎረምሳ፤ የባህል አልባሱን ለብሶ፤ ጸጉሩን ክምክም ተስተካክሎ፤ ውሀ አጣጪውን ፍለጋ ይወጣል። ዕለቱ የትጭጭትም ጭምር ነውና። ከዚያ ሁሉ ሕዝብ መሀል በውበት ዛላ ደርበብ ብላ ከባህል ቀሚሷ በአንገቷ ጌጡን በእግር አልቦ የእጅ አንባሩን አጥልቃ እኔም አላገባሁም ምልክት ጸጉሯን ጋሜ ተሠርታ ሽቅርቅር የምትለዋን የሀላቢቾን ኮረዳ በአይኑ እያማተረ ይፈልጋታል። ሴራ እንደሆን ሀላባውያኑን ከልጅነት እስከ እውቀት እየመራ ሁሉን ማቃናቱ ልማዱ ነው። በሴራ ባህል መሠረተ በሰሞነ ሴራ ይገረዛል። በሴራ ተኮትኩቶ ያድጋል። በሴራ ዕለት ተጫጭቶ ደግሞም በሴራው ሥርዓት ከሴራው ክብረ በዓል አጥቢያ ያገባል። እንግዲህ በዓመቱ ሴራ ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ ይዞ ይመጣል። የአባቱ ልጅ ደግሞ ይቀጥላል። በሴራ መንገሳ መች ወጣቱ ብቻ ሆነና እናቶችም አሉ። ከላይ እስከ ታች በባህላዊ አልባሳቶቻቸው ውበትን ደፍተው ይወጣሉ። ለማግባታቸው ምልክት ከወገባቸው ላይ መቀነቱን ሸብ አድርገው ከበሮዎቻቸውን በመያዝ ሰብሰብ ብለው በያካና ቃላ የባህላዊ ሙዚቃዎቻቸው እየጨፈሩ ወደ አደባባይ ይወጣሉ።

ከልጅነት እስከ እውቀት ሴራ አለ። ከልጅነት እስከ እውቀት ኪነጥበብ አለ። ታዳጊዎች ወደ ወጣትነትና ከቤተሰቦቻቸው ሙሉ ኃላፊነትን ተቀብለው ለመሸከም ወደ ሚችሉበት የዕድሜ ክልል ሲሸጋገሩ የሚከወነው የ"ሁሉቃ" ሥርዓት ማሳያ ነው። ልጆች ገና ከህጻንነታቸው፤ በግርዛት ወቅት የሚጠቀሙት የዋሽንትን ድምጽ የሚሰጥ ሌማት፤ ወይንም ከቀርከሀ ዛፍ የሚሰራ "ኡሉሌ" የሚሰኝ የሙዚቃ መሳሪያ ይይዛሉ። የሚዘጋጀውም በራሳቸው ነው። ካደጉ በኋላም እንደ ሙዚቃ መሳሪያ የሚያገለግለውንና የማህበረሰቡ መገለጫ የሆነውን ፊሽካ ይይዛሉ። መነሻውን ኡሉሌ አድርጎ ዛሬም ድረስ የሀላባ የሙዚቃ መሳሪያ በመሆን ያገለግላል። የተለያዩ የባህል የኪነት ቡድኖች በተለያዩ ጊዜያት እስከ ጦር ግንባር ድረስ ሔደው ጀግናውን እያበረታቱና እያሞገሱ የሠራዊቱን ወኔ ቀስቅሰውበታል። በየሠርግና የደስታ ቦታዎች ሁሉ ከመጠቀምም ባሻገር በየዓመቱ የሴራን ክብረ በዓል ለማድመቅ ይጠቀሙበታል። ጭፈራ ባለበት ሁሉ ኡሉሌ አለ። ታዲያ ኡሉሌ ብቻውን አይደለም የላመውን የጎማ ከመነዳሪ ከእንስራ አፍ ላይ የተወጠረ፤ እንደ ከበሮ ያለው "ደንበሌሳ"ም አለ።

ድምጻዊ ኑረዲን ያሲን በሀላባ ማህበረሰብ እውቅ ድምጻዊ ነው። ከዚያም ባሻገር በማዕከላዊ ኢትዮጵያ የሀላባ ዞን የባህል አምባሰደርም ጭምር ነው። በሥራውም ነጠላ ዜማዎችንና "አባዲጋ" የተሰኘ አንድ አልበም እንዳለው አጫውቶኛል። ኪነጥበብና የሴራ ባህል ወዳጅነት የገዘፈ ነውና ይህን እያነሳ ስለ አንዳንድ ጉዳዮች እንዲነግረኝ በጠየቅኩት ጊዜ እንዲህ አለኝ፤ "ባህሉን ለማንጸባረቅ እንደ ኪነጥበብ ያለ የለም። በሀላባ ሴራ ውስጥ ከመነሻው ጀምሮ በኪነጥበብ የታጀበ ነው። በዚህ የሞቀው የሴራ በዓል ኪነጥበባዊ ክዋኔዎች ክብረ በዓሉን የደመቀ ለማድረግ ከመሀል የፈረስ ጉግስ ስለመኖሩም ላክልበት" አለ። ያክልበት፤ እሱስ ቢሆን መች ከኪናዊነት የራቀ ሆነና። ከእነዚህ የጉግስ ፈረሶች በስተጀርባ ሌላ ታሪክም ስለመኖሩ ኑረዲን አንስቶልናል።

እንደሚታወቀው አርበኞቹ አባቶቻችን በጣሊያን ወረራ፤ እንዲሁም በተለያዩ ጦርነቶች ሲጠቀሙ የነበሩት ታንክ የጫነ ዘመናዊ ተሽከርካሪ ሳይሆን ኮርቻና ግላስ የተሸከሙ ፈረሶችን ነበር። የሀገርን ታላቅነት በሚያወሳው ሙዚቃ ግለት እሳት ፍም ለብሰው፤ በግጥምና ዜማዊ ፉከራና ሽለላ በያዙት ጎራዴና ጦር ከልባቸው ውስጥ እሳቱን ለኩሰው በፈረሶቻቸው ወደ ጠላት መንደር ይገሰግሳሉ። ደርሰውም በያዙት ጎራዴና ጦር ከልባቸው እሳቱን እየለኮሶ የጠላትን ዘመናዊ የጦር ታንክ አመድ ያደርጉታል። ለምስክርነትም ሁለት የጠላት ታንኮች ዛሬም ድረስ በሀላባ ምድር ይገኛሉ። ይህ የሆነው በሂሊኮፕተር አልነበረም፤ በፈረስ እንጂ።

ኪነጥበብ ከስሜት ጋር ሲዋሀድ ከሰማይ ላይ እንደ አሞራ የሚበረውን የጦር ሂሊኮፕተር ከምድር ፈረስ ላይ ተቀምጠን እኛም እንደ አባቶቻችን ወደ መሬት እንጥለዋለን። የፈረስ ጉግሱም ከጉግስነት በተጨማሪ ይህንን ያስታውሰናል። የሀላባ ባህልና ኪነጥበብ፤ ኪነጥበብና ሴራ ተጋምዷቸው እንዲሁ በዋዛ የሚፈታ አይደለም"። በሴራ ጥበባት በየአይነቱ በየፈርጁ ይዘንባሉ። ግጥም 'ሴነሮ' . . . የእናቶች 'ቃላ' . . . ወጣቶቹ በሽለላና ፉከራ "እሪ!" እያሉ ወኔን ከውስጣዊ ስሜት ጋር ይቀሰቅሱበታል። ሀላባውያን በሴራ ኪነጥበብ ሀገር፣ ቤተሰብና እራሳቸውን ከመጠበቅ/ማስጠበቅም ባለፈ ያስከብሩበታል።

ድምጻዊ ኑረዲን ካነሳቸው ሀሳቦች መሀል ድንገት አንዲት ጥያቄ ሽው አለችና እንዲያው ግን የሀላባ ማህበረሰብ ለ7 መቶ ዓመታት ያህል የሴራን ሥርዓቶች ሳይቆራረጥና ሳይሸራረፈ ከትውልድ ትውልድ ተሸጋግሮ እዚህ ሲደርስ የሴራ ሥርዓት ከኪነጥበብ ጋር አንገት ለአንገት የተቃቀፈ ስለመሆኑ ማህበረሰቡ ልብ ብሎ ተመልክቶት ይሆን? የምትለዋን ጥያቄ ጣል በማድረግ ምላሹን ጠበቅኩኝ። "ይሄ የገባን ጥቂቶች ነን። ማህበረሰቡ ግን ጥንቱን በሴራ ሥርዓት ኪነጥበብን ለይቶ እንደ ዛሬው ለማጣፈጫነት ሳይሆን እራሱን ኪነጥበብን እየፈጠረ ባህሉ አድርጎት ነበር። በዚህ ምክንያትም ኪነጥበብ የማህበረሰቡ ባህል ማዳበሪያ ሳይሆን ባህሉ እራሱ ኪነጥበብ ነበር" የምትለዋን ምላሽ አስከተለ። ነገሩ እውነት ነው። ዛሬ ላይ የእውቀትን የዋንጫ ጽዋ በፊደል ስናነሳ ኪነጥበብን ከባህል ደም ስር ውስጥ ለይተን በማውጣት "ኪነጥበብ" የሚል የስም ቡልኮ ደርበንለት እንደ አዲስ ያገኘነው መሰለን እንጂ በጥንታዊያኑ የኛ አባቶች ዘንድ ስለዛሬው የኛ ኪናዊ ፍልስፍና ሳይጨነቁ ኪነጥበብ እራሱ እንደ ባህር አሳ ከባህሎቻቸው ተነጥሎ ለመኖር የማይችል ባህላቸው ነበር። ዛሬ ዛሬ ሳይንሳዊ እውቀታችን እየሰፋ ዘርፉን አንዘርፍፈን በየጎራው መለየታችን ድንቅ ቢሆንም፤ ነገር ግን ዘመኑ በጨመረ ቁጥር ከባህሎቻችን ራቅ እያለ ዛሬ ላይ ባይተዋርነት እየተሰማው ይሆን? የሚል ሌላ ጥያቄ ከአዕምሮዬ ቋት ሲወነጨፍ ተሰማኝ፤ ጥያቄው ግን ለድምጻዊው ሳይሆን ለራሴና ለውስጤ ብቻ ነበር።

በሴራ መንገሳው ዕለት ከህጻናት እስከ አዛውንቱ በቁሊቶ ከተማቸው አደባባይና ጎዳናዎች ላይ ፈሰው ከአልባሳትና ጌጦቻቸው ጋር ሲታዩ በንጉሥ ቤተ መንግሥት የተነሰነሱ አበባ መስለዋል። አይኔን አማትሬ ሁሉን ለመመልከት ብሞክር ያይን አዋጅ ሆነብኝ። ከአንደኛው አውራ ጎዳና ላይ በባህል ልብስ ያሸበረቁ በርከት ያሉ ወጣቶች ሰብሰብ ብለው በጭፈራ አቧራውን ያጨሱታል። ከሙዚቃው ስልት ጋር በቀኝ እግራቸው መሬቱን እየደቁ፤ ከበሮውን ይደልቁታል። ፊሽካውን ፒርር እያደረጉ ጭፈራውን ያደምቁታል። አለባበሳቸው አይንን፤ ዜማቸው ቀልብን ይስባል። ድንገት ከመሀል አንዱን ወጣት ጠርቼ ጥቂት አወራሁት። ለግላጋው ወጣት ራህመቶ መሀምድ እንደሚባል ከነገረኝ በኋላ፤ "ይሔ ጭፈራ ምን ይባላል?" ስል ጠየቅኩት። "ጭፈራውማ ቾለሎቴ ነው፤ ቀጥሎም ያካ ይኖረናል" ቋንቋችሁ ጉራማይሌ ነው፤ ከብዙ ቋንቋዎች ጋር የሚመሳሰል ይመስላልና ይሔስ ነገር እንዴት ነው? "ቋንቋችንም ከበርካታ የሀገራችን ቋንቋዎች ጋር ዝምድና አለው፤ ከዚህም ከዚያም የተወራረሰና በቃላት የተጋመደ ነው። ሀላባ የብዙ ብሔሮች መኖሪያና ብዙዎች በህብረትና ፍቅር ያቆሟት ናት። የሀላባን ባህል መጠበቅ ኢትዮጵያን መጠበቅ ነው" አለኝ። በርግጥም ልክ ነበር። ገና ያላወቅነው እንጂ አውቀን የጨረስነው ኢትዮጵያዊነት የለም። ገና ምኑንም ያላየነውና ያልሰማነው ኪናዊ የባህል ዳርቻ እንጂ "አይቼ፣ ሰምቼዋለሁ" ብለን በአራት ነጥብ የምንዘጋው የለም። ብንል እንኳን የኩሬ ታህል አትሆንም። ሀላባዎቹ በዩኔስኮ የማይዳሰሱ ቅርሶች ማህደር ውስጥ ለማስፈር በአሁኑ ሰዓት ላይ ታች እያሉለት ያለውን የሴራ መንገሳ ባህልን፤ እኔም ከባህሩ የኩሬ ያህሏን አየሁ እንጂ አይቼና አውቄ አልጨረስኩትም። የሀላባውያኑን ሴራ መንገሳ ከመሳሰሉት ውስጥ እንዲህ ያሉ ውብ የባህል እሴቶቻችን ይፈልቃሉ። እነርሱም እንደሚሉት ኪነጥበባችን ያለ ሴራ አይቆምም፤ ሴራችንም ያለ ኪነጥበብ አይኖርም።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## በሁሉም አገልግሎቶች ላይ የአካል ጉዳተኞችን አካታችነት ማረጋገጥ ይገባል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

እኤአ በ2011 የዓለም ባንክ እና የዓለም ጤና ድርጅት ባወጡት መረጃ መሰረት ከአለም ሕዝብ 15 በመቶ ያህሉ፣ በኢትዮጵያ ደግሞ ወደ 17 ነጥብ 6 በመቶው የሕብረተሰብ ክፍል የአካል ጉዳተኛ ነው። በዚህ በኢትዮጵያ 20 ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎች ከተለያየ ዓይነት የአካል ጉዳት ጋር እንደሚኖሩ ይታመናል።

ታዲያ በበቂ ሁኔታ አካል ጉዳተኞችን የሚመጥን የመሠረተ ልማት አውታር ግንባታ አለመኖር፤ እንዲሁም የአገልግሎት አሰጣጥ ጉድለት በርካቶችን ለከፍተኛ እንግልት እና የጤና ችግር እንደዳረጋቸው ይነገራል።

በእርግጥም በየህንጻው ተመጣጣኝ የመጸዳጃ አገልግሎቶች አለመኖር፤ በመጓጓዣ አገልግሎቶች ዘርፍ ለአካል ጉዳተኞች ትኩረት አለመደረጉ ችግሮቹን የሚያባብሱ ጉዳዮች መሆኑንም የአካል ጉዳተኞች በተደጋጋሚ ጊዜያት በምሬት ሲናገሩ ይደመጣል።

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የልዩ ፍላጎትና አካቶ ትምህርት ክፍል መምህር የሆኑት ዶክተር አበበ የኋላወርቅ እንደሚያነሱት፤ የአካል ጉዳተኞች አካታችነት ላይ ሕጎች ተፈጻሚ እንዳይሆኑ የግንዛቤ ክፍተት ትልቁ እንቅፋት ነው፡፡

ማንም ሰው በራሱ ምሉዕ ባለመሆኑ አንዱ ለአንዱ የሚኖረው አበርክቶ የተለያየ ቢሆንም እጅግ ጠቃሚ ነው፤ የአካል ጉዳተኞች የጉዳት መጠናቸው ከፍና ዝቅ ባለ ቁጥር የሚሹት የድጋፍ መጠን ይለያያል የሚሉት ዶክተር አበበ፤ ለአብነትም በአይኑ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሰው ጉዳቱ ከፊል የእይታ ችግር ከሆነ በመነጽር ሊስተካከል እንደሚችልና ነገር ግን ይህ የማይሆን ከሆነ የስነ ተግባቦት ሁኔታው የሚቀየር እንደሚሆን ያወሳሉ፡፡

እንደ ዶክተር አበበ ገለፃ፣ በኢትዮጵያ ያለው የአካል ጉዳተኞች ድጋፍ እራስ ቻይ ይሆናሉ በሚል መንፈስ ሳይሆን የበጎ አድራጎትን መሰረት ያደረገ መሆኑ ጠቃሚ አይደለም። እንዲሁም ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ አካል ጉዳተኞችን በመደገፍ ገነት ይገባል የሚል አመለካከት በመያዝ የእለት ጉርስ ማቀበል የተለመደ ሲሆን ፤ይህም



በመብት ላይ ያልተመሰረተና ሥርዓት ያልተበጀለት ሲፈለግ የሚሰጥ ሲፈለግ የሚከለከል ነው።

መንግሥት ትምህርትን በነፃ የማቅረብ ግዴታ ያለበት ሲሆን፤ ማንኛውም ሰው ደግሞ የመማር መብት ቢኖረውም አካል ጉዳተኞች ተገቢውን ድጋፍ ባለማግኘታቸው ከቅድመ መደበኛ ጀምሮ ያላቸው ተሳትፎ እየቀነሰ መምጣቱን መምህሩ ይጠቁማሉ።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት 95 በመቶ እድሜው ለአቅመ ሥራ የደረሰ አካል ጉዳተኛ ሥራ የለውም የሚሉት ዶክተር አበበ፤ በኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞች ድጋፍ ዝቅተኛ እንዲሆን ያደረገው አካል ጉዳተኞችን የሚመለከት የተቀናጀ ሀገራዊ ህግ አለመውጣቱ ነው። ስለዚህም ጊዜውንና የሰው ልጆችን እድገት የዋጀ ህግ ማውጣት አስፈላጊ መሆኑን ያነሳሉ።

ችግሩን ለማስተካከል ሁሉም በየደረጃው የሚመለከተው አካል በቅንነት መስራት አለበት። እንዲሁም የአካል ጉዳተኞችን ችግር የሚያቀሉ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን እንዲጠቀሙ ማድረግ፣ በህብረተሰቡ ውስጥ ስለ አካል ጉዳተኞች ያለውን የተዛባ አመለካከት ማስወገድ፣ አካል ጉዳተኞችን በመንግሥት የስልጣን እርከን ውስጥ ማሳተፍና ሌሎችንም የመፍትሔ እርምጃ መውሰድ እንደሚያስፈልግ መምህሩ ያወሳሉ።

በአካል ጉዳተኞች ዙሪያ የሚወጡ ህጎች ተግባራዊ



አለመሆን መንግሥትን ጨምሮ በሁሉም ደረጃ የሚገኙ አካላት ኃላፊነት አለባቸው የሚሉት የአዲስ አበባ ከተማ አካል ጉዳተኞች ማህበር ፕሬዚዳንት አቶ ገለታው ሙሉ ሲሆኑ፤ መንግሥት እንደ ሀገር የህግ፣ የፖሊሲና የአሰራር ሥርዓቶችን በማውጣት ተግባራዊ የማድረግ ሚናው የጎላ ነው ይላሉ፡፡

የመንግሥትም ሆነ የግል ተቋም የአካል ጉዳተኞችን ችግር የኔ ነው ብሎ ማሰብ እንዳለበት የሚያነሱት አቶ ገለታው፤ አካል ጉዳተኞች ላይ የሚደርሱ ማህበራዊ ችግሮች በተለይም የአገልግሎት አካታችነት ላይ የፖሊሲና አፈጻጸም ችግሮች የሚስተዋሉ በመሆናቸው በጋራ በመስራት ችግሮቹን መቅረፍ እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፡፡

በአካል ጉዳተኞች ላይ በስራ እንቅስቃሴ የተለያዩ ችግሮች እየገጠማቸው ሲሆን ለአብነትም መስማት የተሳናቸው ዜጎች በየተቋማት አገልግሎት ፈልገው ሲሄዱ የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ አለመኖር ተግዳሮት እየሆነ እንደሆነ አቶ ገለታው አንስተዋል፡፡

በዚህም ማህበሩ በአዲስ አበባ ነዋሪ በሆኑ አካል ጉዳተኞች የሚደርስባቸውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ዘርፈ ብዙ ችግሮችን በመለየት ከባለድርሻ አካላት ጋር የውይይት መድረኮችን በማዘጋጀት የመፍትሄ ሀሳቦች ላይ ለመድረስ ጥረት እያደረገ ነውም ይላሉ።

እንደ አቶ ገለታው ገለፃ፣ ማህበሩ ከአብዛኛው የመንግሥት ተቋማት ጋር ቅርብ የሆነ ግንኙነት በመፍጠር በጋራ እየሰራ ሲሆን፤ እንዲሁም ከአንዳንድ ተቋማት ጋር በሚኖሩ የስብሰባ፣ የወርክ ሾፕና የስልጠና መድረኮችን በመጠቀም ስለ አካል ጉዳተኞች አካቶ እየሰራ ነው፤ የፖሊሲና የአሰራር ክፍተቶች ሲፈጠሩ ወደሚመለከተው ተቋሚ በመሄድ ችግሮቹን ለመፍታት ይጥራል፡፡

መስማት የተሳናቸው ዜጎች በተለያዩ መንግሥታዊም ሆነ መንግሥታዊ ባልሆኑ ተቋማት እንደልብ አገልግሎቶችን ማግኘት እየቻሉ እንዳልሆነ የሚያነሱት ደግሞ አቶ አበበ ታምራት ናቸው።

አቶ አበበና ባለቤታቸው መስማት የተሳናቸው ሲሆኑ ባለቤታቸው ለምርመራና ለወሊድ ወደ ህክምና ተቋሚ ሲሄዱ አስተርጓሚ ባለመኖሩ ከህክምና ባለሙያዎች ጋር መግባባት እንዳልቻሉ አስታውሰው፤ በህክምና ተቋማት መገልገል ያለባቸው ጉዳት አልባዎች ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ሊገለገል እንደሚገባ ያነሳሉ፡፡

"ለአካል ጉዳተኞች ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት እና ለዘላቂ የልማት ግቦች ስኬት ትርጉም ያለው ትብብር" በሚል መሪ ቃል በኢትዮጵያ ለ31ኛ ጊዜ፤ በአለም አቀፍ ደረጃ ለ32ኛ ጊዜ የአካል ጉዳተኞች ቀን በመከበር ላይ ይገኛል።

# ዓለም አቀፍ



## ለጋዛ ሰብዓዊ ድጋፍ ለማቅረብ ስምምነት ተደረሰ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

እስራኤልና ሐማስ በሰብዓዊ አቅርቦት ዙሪያ ስምምነት ላይ መድረሳቸውን አደራዳሪዋ ኳታር አስታወቀች። ስምምነቱ ሰብዓዊ ድጋፍ ወደ ጋዛ በሚገባበት ሁኔታ ላይ ያተኮረ መሆኑንና በጉዳዩ ላይ ሲሰሩ ለነበሩ በርካታ አካላት እፎይታን የሰጠ ስምምነት መሆኑ ተገልጿል።

ከኳታር ሌላ በማደራደሩ ሂደት ፈረንሳይ ተሳትፎ እንዳላት ተነግሯል። በዚህ ስምምነት መሠረት በሐማስ ለተያዙ ታጋቾች አስፈላጊ መድኃኒት እንዲደርስ መግባባት ላይ ተደርሷል።

እስራኤል በምላሹ ደግሞ አስፈላጊ ሰብዓዊ እርዳታ ወደ ጋዛ እንዲገባ ትፈቅዳለች። ላለፉት ሦስት ወራት ያለማቋረጥ በቦምብ ጥቃት ሲፈጸምባት በቆየችው ጋዛ አሁን ያለው ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ የሚባል ነው።

አሜሪካ ድርድሩ ተጠናክሮ ቀጥሎ ታጋቾች የሚለቀቁበት ሁኔታ ይኖራል የሚል ተስፋ አለኝ ብላለች። የአሜሪካ ልዩ ልኡክ ይህን ለማሳካት ወደ ኳታር መላኳን የዋይት ሐውስ የደኅንነት ጉዳዮች ቃል አቀባይ ጆን ኪርቢ ማክሰኞ ዕለት ተናግረዋል።

"ድርድሩ ጠንካራና ጥልቅ ድርድር ነበር፤ ፍሬ ያፈራል ብለን ተስፋ እናደርጋለን" ብለዋል ጆን ኪርቢ። የኳታር ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቃል አቀባይ ማጂድ አል አንሳሪ ሰብዓዊ እርዳታን በተመለከተ ስምምነት ስለመደረሱ ቀደም ብለው አስታውቀው ነበር።

በዚህ ስምምነት መሠረት ሰብዓዊ እርዳታ ከዶሃ ተነስቶ ግብጽ ይደርሳል። ከግብጽ ደግሞ ወደ ጋዛ እርዳታው በተመሳሳይ ቀን እንዲደርስ ይደረጋል። ይህ የሚሆነው ግን ለታጋቾች አስፈላጊ መድኃኒት ሲደርሳቸው ነው።

የተባበሩት መንግሥታት የሰብዓዊ ድጋፍ ኃላፊ በጋዛ ያለው ሁኔታ 'ጊዜ የማይሰጥ' ብለውታል። ባለፈው ሳምንት የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አንተኒ ብሊንከን በጋዛ 90 ከመቶ የሚሆነው ሕዝብ በምግብ እጥረት ላይ መሆኑን የተባበሩት መንግሥታትን በመጥቀስ ተናግረው ነበር።

አክለውም ልጆች ተመጣጣኝ ምግብ በዚህ ጊዜ አለማግኘታቸው ሕይወታቸውን ሙሉ የሚከተላቸው ችግር ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ ሲሉ አስገንዝበዋል።

"ተጨማሪ ምግብ፣ ተጨማሪ ውሃ፣ ተጨማሪ መድኃኒት እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ ድጋፎች ወደ ጋዛ መግባት አለባቸው" ብለዋል ብሊንከን።

## የፈረንሳይ ሀገር ውስጥ ሚኒስትር በስም ማጥፋት ወንጀል ተከሰሱ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የፈረንሳይ የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ፈረንሳዊው የእግር ኳስ ተጫዋች ካሪም ቤንዜማ ስሙን ከሙስሊም ወንድማማቾች (ሙስሊም ብራዘርሁድ) ጋር በማያያዛቸው ተጫዋቹ በስም ማጥፋት ወንጀል ክስ መስርቶባቸዋል።


ባለፈው ጥቅምት ተጫዋቹ "ሴቶችን እና ህጻናትን የማይለይ ኢፍትሃዊ የቦምብ ጥቃት ሰለባዎች" ሲል ድጋፉን ለጋዛ ነዋሪዎች በኤክስ ከገለጸ በኋላ ነው የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትር ዤራልድ ዳርማኒን ተጫዋቹ ከሱኒ ሙስሊም እስላማዊ ቡድን ጋር "የሚታወቅ ግንኙነት" አለው ያሉት።

መስከረም ወር ላይ በሐማስ ለተገደሉት እስራኤላውያን ተመሳሳይ ሃዘኔታ አለማሳየቱን የገለጹት ዳርማኒን፤ ፈረንሳዊው አጥቂ "ከሙስሊም ብራዘርሁድ ጋር ግንኙነት እንዳለው ቀድሞውን የታወቀ ነው" ብለዋል።

ይህ ንግግራቸው ክብሩን እና ስሙን "ያጎድፋል" ሲሉ የቤንዜማ ጠበቃ ተናግረዋል። የእስልምና እምነት ተከታይ የሆነውን እና በሳዑዲ አረቢያ የሚጫወተው የ36 ዓመቱ ካሪም ቤንዜማ ውንጀላውን ውድቅ አድርጎ በሚኒስትሩ ላይ የስም ማጥፋት ክስ እንደሚመሰርት አስጠንቅቆ ነበር።

በፈረንሳይ መገናኛ ብዙኃን በሰፊው በተዘገበው ባለ 92 ገጽ ክስ "ከሙስሊም ብራዘርሁድ ጋር ግንኑነት ኖሮኝ አያውቅም፤ እስከማውቀው ድረስ የድርጅቱ አባል ከሆነ ሰው ጋርም ግንኙነት የለኝም" ብሏል።

ጠበቃው ሁጉስ ቪጊየር ለፈረንሳዩ ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ እግር ኳስ ተጫዋቹ "የፖለቲካ



ዤራልድ ዳርማኒን

መጠቀሚያ" እንደሆነ እና የሀገር ውስጥ ጉዳይ ሚኒስትሩን "በፈረንሳይ መከፋፈልን እየዘራ ነው" ሲልም ከሷል።

ዳርማኒን ቀደም ሲልም ካሪም ቤንዜማን ዒላማ አድርገው ነበር። የፈረንሳይን ብሄራዊ መዝሙር ለመዘመር ፈቃደኛ ባለመሆኑ እና "በማህበራዊ ድረ-ገጾች ላይ ሃይማኖትን መስበክን" ጨምሮ በሌሎች ምክንያቶች እንዳብጠለጠሉት ይታወሳል። ።

ይሁንና ተጫዋቹ ስሙ ከሙስሊም ብራዘርሁድ ጋር መያያዙን ተቃውሞ የከፈተው ክስ ሚኒስትሩ ላይ ከፍተኛ ጫና ፈጥሯል። የሙስሊም ብራዘርሁድ ግብጽ፣ ሩሲያ እና ሳዑዲ አረቢያን ጨምሮ በበርካታ አገራት ታግደዋል።

# ስፖርት





## የአፍሪካ ዋንጫው ከባድ ሚዛን ጨዋታዎች

ብርሃን ፈይሳ

ያልተጠበቁ ውጤቶችን እያስመለከተ የሚገኘው 34ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ዛሬ የምድብ ሁለተኛ ጨዋታዎች የሚደረጉ ሲሆን፤ ለዋንጫ ተጠባቂ የሆኑ ቡድኖች የሚገናኙባቸው የዛሬዎቹ ጨዋታዎች እጅግ ተጠባቂዎቹ ናቸው:: ከከባድ ሚዛን ምድብ ከሚካተቱት ቡድኖች መካከል፤ በተለይ መልካም አጀማመር ያልነበራቸው የግብጽና የጋና እንዲሁም የኮትዲቯርና የናይጄሪያ ግጥሚያዎች የእግር ኳስ ቤተሰቡ በጉጉት የሚመለከታቸው ናቸው::




ፈርኦኖቹ ከጥቋቁሮቹ ከዋክብት የሚያደርጉት የምድብ ሁለት፣ ሁለተኛው ዙር ብቸኛ ጨዋታ ከ11ሺህ በላይ ተመልካች በሚይዘውና አቢጃን በሚገኘው ፌሊክስ ሆፕሆት ቦግኝ ስታዲየም ይከናወናል:: በአፍሪካ ዋንጫው ምናልባትም የስፖርቱ አፍቃሪያን ሊመለከቱ ከሚናፍቋቸው ጨዋታዎች መካከል አንዱ ሲሆን፤ ቡድኖቹ ለመሸናነፍ የሚያደርጉት ፍልሚያም ተጠባቂ ነው:: የአፍሪካ ዋንጫን ለሰባት ጊዜ በማንሳት የበላይነቱን የወሰደችው ግብጽ ከሞዛምቢክ ጋር በነበራት የመጀመሪያው ጨዋታ ነጥብ ተጋርታ ከሽንፈት የዳነችው በተጨማሪ ሰዓት በተገኘ ቅጣት ምት መሆኑ የሚታወስ ነው:: ለአራት ጊዜ የውድድሩ ቻምፒዮን የሆነችው ጋናም በአፍሪካ ዋንጫው ተጠባቂ ትሁን እንጂ በኬፕ ቨርዴ ሽንፈትን በመከናነብ ነው የጀመረችው::

በመሆኑም ሁለቱ ቡድኖች ዛሬ ሶስት ነጥብ ለማሳካት ተጠናክረው ወደ ሜዳ መግባት ይጠበቅባቸዋል:: በሁለቱም ቡድኖች በኩል ተጫዋቾቻቸው በመልካም ጤንነት ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ በጉዳት ምክንያት ባለፈው ጨዋታ ያልተካተተው የዌስትሃም እና የጋና ቁልፍ ተጫዋች መሃመድ ኩዱስ በዛሬው ጨዋታ እንደሚሰለፍ ይጠበቃል:: በዚህ ውድድር ላይ ይደምቃሉ ተብለው ከተለዩ ተጫዋቾች መካከል ግብጻዊው የሊቨርፑል የፊት መስመር ተጫዋች መሀመድ ሳላህም ሀገሩ እንድታሸንፍ የሞት ሽረት ትግል ያደርጋል:: ለረጅም ጊዜ ሀገሩን በአፍሪካ ዋንጫ የወከለው ተጫዋቹ የዘንድሮው የመጨረሻው ሊሆን እንደሚችል ተገምቷል::

በኳታሩ ዓለም ዋንጫ ላይ ሀገሩን በአሳዛኝ ሁኔታ ማሳለፍ ካለመቻሉ ባለፈ ከሁለት ዓመት በፊት በካሜሩን በተካሄደው 33ኛው የአፍሪካ ዋንጫ ፍጻሜ ጨዋታ ዋንጫውን ማሳካት አለመቻሉ ይታወሳል:: በመሆኑም በዚህ ውድድር ፈርኦኖቹ እንዲሁም የ31 ዓመቱ ሳላህ ለዋንጫና ኮኮብ ግብ አግቢነት ይጠበቃሉ:: በሌላ በኩል እአአ ከ2017 ወዲህ በተካሄዱት ሁለት የአፍሪካ ዋንጫዎች ባልተጠበቀ ሁኔታ በጊዜ ከውድድሩ ለመሰናበት የበቁት ጥቋቁሮቹ ከዋክብት ዋንጫውን ወደ ሀገራቸው በመውሰድ ደጋፊዎቻቸውን መካስ ይገባቸዋል:: ለዚህ ደግሞ እንግሊዛዊው የፕሪምየር ሊጉ አሰልጣኝ ክሪስ ሂውተን የቤት ሥራውን ተረክበዋል::

ሌላኛው የእለቱ ተጠባቂ ጨዋታ ደግሞ በአፍሪካ ዋንጫው አዘጋጅ ሀገር ኮትዲቯር እና ናይጄሪያ መካከል የሚደረገው ነው:: በመጀመሪያው ምድብ ከተደለደሉትና ጠንካራ የሚባሉት ሁለቱ ቡድኖች ዛሬ የሚኖራቸው ጨዋታ በደረጃ ሰንጠረዡ የዝሆኖቹን የበላይነት የሚያረጋግጥ አሊያም የንስሮቹን እጣ ፋንታ አጣብቂኝ ውስጥ የሚከት ይሆናል:: ጊኒ ቢሳውን 2 ለምንም በሆነ ውጤት መርታት የቻሉት ዝሆኖቹ ዋንጫውን ሀገራቸው ላይ ለማስቀረት ፍላጎት ያላቸው እንደመሆኑ በደጋፊያቸው ፊት ቀላል ተጋጣሚ አይሆኑም::

ባለፈው ጨዋታ ከኢኳቶሪያል ጊኒ ጋር አንድ እኩል የተለያዩት ንስሮቹ የአፍሪካ ዋንጫውን ያነሳሉ በሚል ከሚጠበቁት ቡድኖች መካከል ይገኛሉ:: የአፍሪካ ዋንጫን ሶስት ጊዜ በማንሳት ከኮትዲቯር የተሻለች ትሁን እንጂ በካሜሮኑ የአፍሪካ ዋንጫ ግን ሩብ ፍጻሜውን መቀላቀል ተስኗት ነበር:: በመሆኑም የዛሬው ሶስት ነጥብ 16ቱን የመቀላቀል ተስፋቸውን የሚያለመልም ይሆናል:: በዚህ ውድድር ድንቅ ብቃታቸውን ያሳያሉ በሚል የሚጠበቀው ናይጀሪያዊው የናፖሊ አጥቂ ቪክተር ኦስሜን በዛሬው ጨዋታም ይጠበቃል:: የአፍሪካ የዓመቱ ምርጥ ተጫዋቾች ሽልማትን ያሸነፈው የ24 ዓመቱ ኦስሜን ሀገሩን ለዋንጫ ያበቃል የሚል ኃላፊነትም ተጥሎበታል::

በተያዘው መርሀ ግብር መሰረት የምድብ አንድ ሁለተኛው ጨዋታ በኢኳቶሪያል ጊኒ እና ጊኒ ቢሳው መካከል የሚደረግ ነው:: በመጀመሪያው ጨዋታ ባልተጠበቀ ሁኔታ ለናይጀሪያ ጠንካራ ተጋጣሚ በመሆን ነጥብ ተጋርታ የወጣችው ኢኳቶሪያል ጊኒ፤ በአዘጋጇ ኮትዲቯር ብልጫ የተወሰደባት ጊኒ ቢሳውን ለመርታት ወደ ሜዳ ይገባሉ:: ይሁንና ጊኒ ቢሳው ከምድቡ አልፎ 16ቱ ውስጥ ለመግባት የሚኖራትን እድል ሙሉ ለሙሉ ላለማጣት ወሳኝ በሆነው ጨዋታ ላይ ለተጋጣሚዋ ፈተና በመሆን ነጥብ ለማስመዝገብ ትጥራለች::

## አዲስ አበባ አስተዳደር

የባለንብረት ስም ካሊድአወል እና ሙክታር መሀመድ የሠሌዳ ቁጥር አአ 03-01-48415 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻንሲ ቁጥር JAMKP34G287P18918 የሞተር ቁጥር 4HF1-441298 ሞዴል NPR66 የሊብሬ ቁጥር 183617 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ1/5/2016 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የየካ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም በለጠ አበይ ፈለቀ የሠሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-01859 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር RM26CF15-6-2-23849 ሞዴል RM26 የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0266445 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ1/5/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የንፋስ ስልክ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም በላይነህ ተስፋዬ የሠሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-22456 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር LC99383L5E2KS8094 ሞዴል KS9380ASQ የሞተር ቁጥር Trailer የሊብሬ ቁጥር 0021810 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ30/4/2016 ዓ.ም አመልክተዋል። ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአ/ቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ወ/ሀዋርያት ካሣ የሠሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-09603 የተሽከርካሪው አይነት ተሳቢ የሻንሲ ቁጥር CT1314-06 ሞዴል MZE13/7.5/ የሞተር ቁጥር Trailer ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ30/4/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የአዲስ ከተማ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ማዶት ኮምፒውተር ሶሉሽን ሃላ/የተ/የግ/ማህበር
የሠሌዳ ቁጥር አአ 03-01-B64484 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል
የሻንሲ ቁጥር LFMCA1CX9N0005839 ሞዴል KPX10L-DHDNSC
የሞተር ቁጥር -ELEC*/ የሊብሬ ቁጥር 537777
ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ27/4/2016 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡
ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን።

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የቦሌ ቅ/ጽ/ቤት**

በከሳሽ ቪዥን ፈንድ ማይክሮ ፋይናንስ አ.ማ እና በተከሳሽ እነ ወ/ሮ ብዙወርቅ ሰይፉ
1. ወ/ሮ ብዙወርቅ ሰይፉ
2. አቶ አብርሀም ግርማ
3. አቶ አቤል ደመና
መካከል 1ኛ ፍታብሔር ስላለው ክስ ጉዳይ ተከሳሽ በ15/05/2016 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ3፡45 ሰዓት የመ/ደ/ፍ/ቤት የካ ምድብ 1ኛ ፍ/ብሔር ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀ/ደ/ፍ/ቤት**

በአመልካች ሰውዳ መሐመድ እና
በተጠሪ አቶ ነስሩ አህመድ
መካከል ባለው የባልና ሚስት የፍች ክርክር ጉዳይ ተጠሪ በ20/05/2016 ዓ.ም. ለሆነው ቀጠሮ ፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት 2ኛ ፍትሐብሔር ችሎት በ3፡00 ሰዓት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ሸሪዓ ፍ/ቤት**

## አማራ ክልል

ለ1. ምህረት ኃ/ሚካኤል
2. ክንፈ ዳኛው
3. እለኒ አበባው
ባሉበት
በከሳሽ ባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት እና በተከሳሽ እነ ምህረት ኃ/ሚካኤል 3 ሰዎች መካከል ስላለው የገንዘብ ክስ ክርክር ጉዳይ መከሰሳቸውን አውቀው ክሱን በመዝገብ ቤት በኩል ወስደው መልሳቸውን ለቀን 30/5/2016 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት ባ/ዳርና አካ/ከፍ/ፍ/ቤት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**በአ/ብ/ክ/መ ጠ/ፍ/ቤት የባ/ዳርና አካ/ከፍ/ፍ/ቤት**

ንብረትነቱ የአብዱ ሰይድ ይመር የሆነ ባጃጅ ተሽከርካሪ የሠሌዳ ኮድ 01-70158 አማ ሠሌዳ የጠፋ መሆኑን ባለንብረቱ በቀን 19/04/2016 ዓ.ም. በተፃፈ ማመልከቻ አመልክተዋል፡፡
በመሆኑም ይህን ሠሌዳ ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የደ/ወሎ ዞን ትራንስፖርት ተጠሪ ጽ/ቤት**

ንብረትነቱ የጫልቱ መሀመድ የሆነ ፒያጆ ተሽከርካሪ የሰሌዳ ኮድ 03-15454 አማ ሰሌዳ የጠፋ መሆኑን ባለንብረቱ በቀን 8/4/16 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ አመልክተዋል። ሰሌዳው ወድቆ ተሰርቆ ወይም በሌላ ግለሰብ እጅ ላይ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ እያሳወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን።

**የደ/ወሎ ዞን ትራንስፖርት ተጠሪ ጽ/ቤት**

## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም ገነት ደምሱ ወንድሙ የሠሌዳ ቁጥር 3-43727
የሻንሲ ቁጥር JT121LK2200038488 የሞተር ቁጥር 2L-4926410
የሊብሬ ቁጥር 0329033 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የፊት ሠሌዳ ጠፋብኝ ብለው በ14/3/2016 ዓ.ም አመልክተዋል ፡፡ ስለሆነም ሠሌዳውን ወድቆ፣ ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

**በሸገር ከተማ አስተዳደር የገላን ክ/ከተማ ትራ/ጽ/ቤት**

## ቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል

የባለንብረቱ ስም አብዱ የሱፍ የሠሌዳ ቁጥር ኮድ 1- 00535 ቤ/ጉ የሻንሲ ቁጥር KCY7B11ZDJC119279 የሞተር ቁጥር F8CL-232332 የሆነ ተሽከርካሪ ሠሌዳ የጠፋባቸው መሆኑን ለፖሊስ አመልክተው ባቀረቡት መሠረት ቅያሪ እንዲሰጣቸው ጠይቀውናል፡፡
ስለዚህ ሠሌዳውን ወድቆ ያገኘም ሆነ ከሰው እጅ ያየ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ 15 ቀን ውስጥ ሪፖርት እንዲያደርግ እያሳወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ግለሰብ ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጣቸው መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**የቤ/ጉ/ክ/መ የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ**